

## ከመሰረታዊው ፍሬ ነገር የመሸሽ አባዜ

በፕሮፌሰር መሳይ ከበደ

5

## ኢትዮጵያ ሙስናን በመዋጋት 126ኛ ተባለች


11

«ሪፖርቱ የኢትዮጵያን ገጽታ አያሳይም»

የፌዴራል ስነምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን

## በ2002 ምርጫ የኢትዮጵያን ዴሞክራሲ ማዳን ይቻላልን?

በፕሮፌሰር አለማየሁ ገ/ማርያም



3


# አውራምባ ታይምስ

ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ

2ኛ ዓመት ቁጥር 87 ጥቅምት 17 ቀን 2002 ዋጋ 3.50 ብር



# ለቴሌቪዥን የሚከፈለው 50 ብር ምንድነው?

ሀ. ግብር

ለ. አገልግሎት

ሐ. ፍቃድ ማደሻ

መ. መልሱ የለም






12



## የቴዲ አፍሮ የአውሮፓ ኮንሰርት እና ውዝግቡ

- በስታዲየም ያቀረበው ኮንሰርት በኢቴቪ መቅረቡ አነጋገሯል

15

## BBC

## ኢትዮጵያና

ዳግም የተጋረጠባት ከፍተኛ የምግብ እጥረት

13

### በውስጥ ገፆች

የጥፋት ባልደራሶች በዝምታ እየታለፉ፤ ስለ ልማት፣ እድገትና ፍትህ መደስኮር ስላቅ ነው!

«በደህናው ጊዜ ያበደ ፀደቀ»

ከሚድህ ዴሞክራሲ ለመውጣት ስንት አመት ይበቃናል?

'አንድነት' እና 'መድረክ'

የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት በይርጋ ቀሪ አይሆንም!

የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ምግቦች በገበያ ላይ ውለዋል

## ኤዲቶሪያል

# የጥፋት ባልደራሶች በዝምታ እየታለፉ፤ ስለ ልማት፣ እድገትና ፍትህ መደስኮር ስላቅ ነው!

ታዋቂው የታሪክ ጸሐፊ ጆን ግራሃም **Exploring Ethiopia** /ኢትዮጵያን ማሰስ/ በሚል ርዕስ ከዓመት በፊት ባሳተመው መጽሐፍ መግቢያ ላይ የአገራችንን ሁለት የተቃርኖ ጽንፍ ገጽታዎች ለንባብ አብቅቷል፡፡ ጸሐፊው ኢትዮጵያውያን ኩሩ ህዝቦች ናቸው ብለው ይጀመራሉ፡፡ ወደኋላ ሶሶት ሺህ ዘመን በሚከነዳ የመንግስትነት ታሪካቸው የተነሳም ምዕራባውያንን በታሪክ ምዕራፍ ውስጥ የቅርብ ጊዜዎች ይሉናል ካለ በኋላ አሉታዊ መገለጫዎችን እየደረደረ በጥያቄ ይሞግታል፡፡ ኢትዮጵያውያን ጥልቅና የበለፀገ ባህል (ታሪክ) እያላቸው እንዴት ድሃና ኋላቀር ሆኑ? አገሪቱ በለም መሬቶችና በጥቅጥቅ ደን እንዲሁም በጠፍ በረሃማ አካባቢዎች ድርቅ የምትመታበት ውዥንብራዊ ሁነት እንዴት ተፈጠረ? ወዘተ… እያለም ይቀጥላል፡፡ አላማችን የታሪክ ጸሐፊውን መድብል መዳሰስ አይደለም፡፡ እንዴት? ለምን? እያልን በምንጠይቃቸው የሁለት ተቃርኖ ጽንፎች አጣብቂኝ ውስጥ መሆናችንን ለማስታወስና የኩሩ ሕዝብነት መገለጫችንን በማያጎናጽፉን የመፍትሔ አማራጮች ላይ እንድንረባረብ ለመጠየቀ ነው፡፡ ከተረባረብን እንወጣዋለን በሚል ወገናዊ ትምክህት ነው፡፡

ሶስት ሺህ ዘመን ወደኋላ ተመልሰን የዘመናዊ ስልጣኔ ፊር ቀዳጅ ክንውኖች ስለሆኑት መንግስታዊ የአስተደደር ስልቶች፣ የረቀቁ የምህንድስናና የንግድ ጥበቦች፣ ተቆጥረው የማያልቁ የስነ ጥበብና ኪነጥበብ ትውፊቶች በዳሰስን ቁጥር ለዚያ እመርታ ምክንያት የሆኑ ትውልዶችንና በርብርብ የገነቡትን አንፀባራቂ ዓለም እናገኛለን፡፡ ከሶስት ሺህ ዓመት በኋላ ዛሬስ? ብለን ስንጠይቅ ደግሞ ባላቸው እውቀት፣ አቅምና ሐብት አገራቸውን ለመገንባትና ሕዝባቸውን ለመጥቀም ሌት ተቀን የሚታትሩ ዜጎችን በአንድ በኩል፤ ሳይማር ያስተማረ ወገናቸውን ለመበዝበዝ፣ የመልካም አስተዳደርና ፍትህ ጥማቱን ለመቀልበስ፣ በአጠቃላይም በግለኝነት መሰረት ላይ ተደላድለው አገርንና ትውልድን የመግደል አላማቸውን ተግተው የሚያራምዱ አፍራሾች በሌላ በኩል የተሰለፉበት የተቃርኖ አሰላለፍ ተደቅኖብናል፡፡

እነዚህ ሁለት የተቃርኖ ጽንፎች በታሪክ ድርሳናት ሰፍረው የሚገኙ ናቸው፡፡ ተጽእኖ የማሳረፍ አቅማቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚለዋወጥ ቢሆንም ዛሬ ባለንበት ነባራዊ ሁኔታ ግን የአፍራሾች ክንድ እየበረታ፣ ስልታቸው ውስብስብና አድቃቂ እየሆነ፣ የገንቢዎችን ሚና ትርጉም አልባ እያደረገ ነው ብለን እናምናለን፡፡ አገራቸውን ለመገንባት ሌት ተቀን ይታትራሉ ያልናቸው ዜጎች ተግባር እንዴት ይገለፃል? ብለን

እንጠይቅ፡፡ እነዚህ ዜጎች አገርን መገንባት የዕለት ተዕለት ተግባር ነው ብለው በማመን የሚያከናውኑት የስራ አይነት ወይም ያላቸው ኃላፊነት ምንም ይሁን የሚጠበቅባቸውን በሐቀኝነትና በትጋት ይፈጽማሉ፡፡ መምህራን ከሆኑ ለነገውን ትውልድ ኃላፊነትን መሸከም የሚያስችለውን የጽንሰ ሃሳብም ሆነ የተግባር እገዛ ያለመሰልቸት ይሰጡታል፡፡ የጤና ባለሙያዎች ተገቢውን ህክምና ሰጥተው ነፍስን ይታደጋሉ፡፡ የአስፈፃሚ አካላት ህግ እንዲከበር ይተጋሉ፡፡ የህግ ተርጓሚዎች ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ብቻ እና በህሊና ዳኝነት ብይን ይሰጣሉ፡፡ ነጋዴዎች በህዝባዊ ወገንተኝነት ስሜትና በጤናማ የንግድ ስርአት ማዕቀፍ ውስጥ አገልግሎታቸውን ያበረክታሉ፡፡ እንደ ሕዝብ አገርን የመገንባት እሳቤ ደግሞ የመብትና ግዴታ ምልአቶችን ጠብቆ ተገቢውን ግብር መክፈልን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ የተመለከትናቸውን መስፈርቶች በማሟላት ቅዱስ ተግባራቸውን የሚያከናውኑ፣ አገራቸው ያለባትን በርካታ አሉታዊ መገለጫዎች ለማጥፋት የሚጥሩ፣ የሚግሩ ክቡራን ዜጎች እንዳሉ እናምናለን፡፡ መልዕክታችንም በርቱ፣ ጠንክሩ ከጐናችሁ ነን የሚል ነው፡፡

ውጫዊውን የአፍራሽነት ተልዕኮ ትተን በወገናቸው ላይ የተተከሉትን የጥፋት ባልደራሶች ማንነትና እያደረሱ ያለውን ውድመት መመልከቱም ተገቢ ይሆናል፡፡ አሁንም እነዚህ የአገር አፍራሽነት ሚና መገለጫዎች ምንድናቸው ብለን እንጠይቅ፡፡ ያሉበት ኃላፊነት ምንም ይሁን፣ በየትኛውም የስራ ዘርፍ ይሁን የሚጠበቅባቸውን ካለመወጣት አንስቶ ግላዊ ስግብግብነትን መሰረት ባደረጉ አሉታዊ ተግባራት ላይ መሰማራት ናቸው፡፡ ዜጎች ፍትህን ይሻሉ፤ፍትህን የማግኘት መብትም አላቸው፡፡ አፍራሾች ግን በህግ ስርአቱ መሰረት ሳይሆን ከግል እምነታቸው ወይም ካሉበት ፖለቲካዊ ድርጅት አስተሳሰብ በመነሳት ፍትህን ያጓትታሉ፣ ይቀለብሳሉ፡፡ የሕዝብ አስተዳደር ጉዳዮችን በማያመች አኳኋን ይመራሉ፡፡ በስልጣናቸው ይነግዳሉ፤ በዚህም ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስተጋብሮች በአደገኛ ሁኔታ ይቃወሳሉ፡፡

ይህ በሕዝብና በአገር ላይ የሚፈፀም ወንጀል ተዋናዮች ማንነት ደግሞ የችግሩን ስር መስደድ፣ ለመከላከልም ጊዜ የሚጠይቅና ፈታንነቱን የሚያመለክት ሲሆን ጥልፍልፍ መዋቅር ያለው ነው፡፡ ሁኔታውን ይፋ ከሆነ መረጃ በመነሳት መገምገም ይቻላል፡፡

ለ2002 ዓ.ም የበጀት አመት 64 ቢሊዮን ብር ተመድቦ የነበረ ሲሆን በጀቱ የሚሸፈነው በፌዴራል ኤጀንሲዎች፣ ሌሎች የአገር ውስጥ ምንጮች ገቢና ግብር፣ 15 በመቶ ያህሉ ደግሞ በውጭ እርዳታና እዳ ስረዛ እንደነበር የገንዘብና ልማት ሚኒስትር መግለፁ ይታወሳል፡፡ እንደ ሚ/ር መ/ቤቱ ገለፃ የውጭ እርዳታ ላይ የተጣለው ተስፋ በመዘግየቱ ለብሔራዊ ግምጃ ቤት ጉልህ አስተዋጽኦ ያላቸው ተቋማት የመታደግ እርምጃ እንዲወስዱ ጥሪ አቅርበው ነበር፡፡ በተለይ እንደ ንግድ ባንክ ቴሌ ኮሙኒኬሽንና የልማት ድርጅቶች ያሉ ተቋማት ከፍተኛውን ድርሻ ይወጣሉ ተብሎ ቢጠበቅም በበጀት ዓመቱ የመጀመያ ሁለት ወራት ገቢ ማድረግ የቻሉት 2.4 ቢሊዮን ብር ብቻ እንደነበር ይፋ ሆኗል፡፡ የኢኮኖሚ ቀውሱን ለመታደግ የቀረበውን ጥሪ ተከትሎ ገቢ የሚሆነው

የገንዘብ መጠን በአገር ማፍረስ ላይ የተሰማሩ ወገኖች ከሚመዘብሩት መጠን ጋር ስናነፃጽረው ምን ያህል አሳሳቢ ችግር ውስጥ እንዳለን ያመለክታል ብለን እናምናለን፡፡

በስንት ተማጽኖና የአገር መገንባት ሚናቸውን ታትረው በሚወጡ ዜጎች ተሰብስቦ የሚመደበው ዓመታዊ በጀት፤ የበጀት እቅድ አፈፃፀም ላይ ኃላፊነታቸውን ያለአግባብ በመገልገል፣ በመመዝበር፣ እምነት በማጉደልና በመሳሰሉት ወንጀሎች በተሰማሩ አፍራሾች ይበዘበዛል፡፡ በ2000 ዓ.ም የበጀት አመት በዚህ ወንጀል ተጠርጥረው ህጋዊ አልባት ያገኙ 296 ግለሰቦች ብቻ ከሁለት ቢሊዮን 180 ሚሊዮን ሶስት መቶ ሺህ ብር በላይ የአገርና የሕዝብ ብር መዝብረዋል፡፡ ይህ አሃዝ የያዝነውን ዓመት በጀት ለመሸፈን ተቋማት ፈጣን ምላሽ እንዲሰጡ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሁለት ወራት ውስጥ /እስከ መስከረም ወር መጨረሻ/ ማስገባት የቻሉትን ያህል ማለት ነው፡፡ ይህን ያህል መጠን ያለውና ስር የሰደደ ምዝበራ ተሸክመን፤ ጥልቅና የበለፀጉ ኢትዮጵያዊ ማንነቶቻችን በተነሱ ቁጥር ክብራችንን የሚያዋርደውንና የሚያሸማቅቀንን የድህነት፣ የድርቅ፣ የርሃብና የስደት ገመና እንደምን ታሪክ ማድረግ ይቻለናል? እጃቸውን ለልመና የሚዘረጉ ህፃናትንና አቅም ደካሞችን በምን መላ ተስፋ እንፈነጥቅባቸዋለን? አበክረን እንጠይቃለን፡፡

በምሳሌነት ያነሳነውና የተጣለባቸውን ህዝባዊ አደራ ለግል ጥቅም በማዋል በአገር ላይ ደባ ፈጽመው በህግ እልባት ያገኙ ግለሰቦች ጉዳይ የአገር ማፍረሱን መጠን ይገልፀዋል ማለት አይደለም፡፡ እልባት ያላገኙ፣ በይደር የተያዙ ስፍር ቁጥር የሌላቸው መሰል ጉዳዮች አሉና፡፡ ከዚህም ይልቅ ደግሞ ባላቸው ስልጣንና ኃላፊነት ተከልለው የህዝብና የአገር ሃብትና ንብረትን የሚዘርፉ፣ የሚያጭበረብሩ፣ በዝምድና፣ በጎሰኝነት፣ በፖለቲካ ወገንተኝነትና በሃይማኖት ትስስር የግል ካዝናቸውን የሚሞሉ ህግና ስርአትን መሳለቂያ የሚያደርጉ ጫፋቸው ያልተነካ ወገኖችን በየስፍራው እየተመለከትን ነው፡፡ በአንዳች ሁኔታ የተጠየቀ ሚዛኑ ካላረፈባቸው በስልጣናቸው ብርቱ ክንድ ራሳቸውን እየገነቡ አገርን እያፈረሱ ይቀጥላሉ፡፡ ትናንት ሰባራ ስንጥር የሌላቸው ዛሬ እነሱ እንኳ መጠኑን በማያውቁት ሐብት ውስጥ ሲዋኙ አገሬ፣ ህዝቤ የሚለው ሁሉ ተስፋ መቁረጡ አይቀርም፡፡

የእድገታችን ፊታውራሪዎች የምንላቸው ተቋማት ባሌስትራን ወርቅ የሚሉ ሹሞች ሲኖሯቸው፣ ከፈጣሪ በታች ፍትህ ያሰፍናሉ ተብለው የሚጠበቁት በዘፈቀደ ሲበይኑ፣ ወይም ፍርድ ሲገመድሉ ለአገሬ ርዕይ አለኝ፣ ለወገኔ ተስፋ ሰንቄያለሁ የሚለው ሁሉ መበርገጉ፣ ብዥታ ውስጥ መግባቱ አይቀርም፡፡ ይህም የተስፋው እንጥፍጣፊ ሳያልቅ ሰደድ እሳቱን ተረባርበን ማጥፋት እንዳለብን የሚያሳስበን ይሆናል፡፡

ሌላም በእጅጉ አሳሳቢ የሆነ ችግር አለ፡፡ ይኸውም አጥፊዎቹ ለወራት ወይም ለዓመታት ያሻቸውን ሲፈጽሙ፣ ሕዝብ ሲያስለቅሱ፣ ፍትህን መደቃደቂያ ሲያደርጉና በሃብት ላይ ሃብት ሲያካብቱ የሚጠይቃቸው ያለመኖሩ ነው፡፡ መጠን የለሽ ጉዳት ከደረሰ በኋላ በጣም የተወሰኑት ብቻ በተጠየቅ ስርአት ወደፍትህ አደባባይ ይወሰዳሉ፡፡ ስንት ህይወት ጠፍቷልኮ፡፡ ስንት አገር ወዳዶች፣ ልማቷንና እድገቷን የሚናፍቁ ተስፋ

ቆርጠዋልኮ:: ወይም ከእነዚህ የተወሰኑት በሸፍጥ የሚመጣው ሃብትና ዝና አማሏቸው በማዕበል ተወስደዋል:: ይህም የዘገየ ፍትህ ጦስ ነው:: የዘገየ ፍትህ ደግሞ እንደተከለከለ ይቆጠራል::

በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ብቻ እንኳ በአዲስ አበባና በኦሮሚያ በ95 የምርመራ መዝገቦች ከአንድ ቢሊዮን 149 ሚሊዮን 140 ሺህ ካ.ሜ በላይ የከተማ ቦታና መሬት በህግ ወጥ መንገድ በመቸብቸቡ እንደታገድ መደረጉ ይፋ ሆኗል:: ይህን የሚያደርጉትም የመሬት አስተዳደርና ልማት ኃላፊዎች ናቸው:: አፈፃፀሙም በአንድ ጀንበር ያለመሆኑ ይታወቃል:: በጠራራ ፀሐይ ሲፈፀም የቆየ ነው:: ይህ ለምን ሆነ? ስንል ይህን የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለባቸው በየደረጃው ያሉ አካላት አንድም ተግባራቸውን አልተወጡም ሁለትም የጥቅሙ ተጋሪዎች ነበሩ ማለት ነው:: በዚህ መጠን በተንሰራፋው የተጠያቂነት መጥፋት ከፍተኛ ውድመት ከደረሰ ዜጎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ጥሪታቸውን አሟጠው ህገ ወጦቹን የማይደፈር የመሰለ ሃብትና ሃይል ካጎናፀፉ በኋላ የሚወሰደውን ህጋዊ እርምጃ ፍትህ ተበየነ ለማለት እንዴት ያስችላል? የጠፋው ህይወት አይመለስም፣ የባከነው ንብረት አይገኝም እንዲሁም የሰፈነው አሉታዊ ስነ ልቦና በምንም አይካስም:: ስለዚህ እርምጃው ግብታዊና የዘገየ በሆነ ቁጥር ውጤቱ ደካማ ግቡም መሰረቱን የለቀቀ ይሆናልና ብርቱ ጥንቃቄ የሚሻ ነው::የኩሩ ሕዝብነት ክብራችንን መመለስ እንችላለን:: ከእኛ የሚጠበቀው መረባረብ ብቻ ነው::

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!**

# Verbatim

«እኔን እና የመጀመያውን የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን የአንድነት ፓርቲ አባላት ሊያነጋግሩን እንደፈለጉ ተነገረን:: በጥሪው መሰረት ጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ.ም ስንሄድ ተሰብስበው ጠበቁን:: «አንድነት ውስጥ ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል እንድታጠናክሩ በአክብሮት እንጠይቃለን::» አሉን:: ስለሆነም ጥያቄው ቀርቦልኛል::»

**አቶ ስዬ አብርሃ/ የቀድሞው መከላከያ ሚ/ር/**

**«የአንድነት ፓርቲ አባላት ፓርቲያቸውን እንዲቀላቀሉ ጠይቆዎታል ይባላል?» በሚል ከአዲስ አድማስ ጋዜጣ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ::**

«የኢህአዴግ ችግር ግለሰባዊ ሳይሆን መዋቅራዊና ተቋማዊ ነው:: መፍትሄውም መዋቅራዊ ነው:: ተሃድሶ ብሎ ነበር:: ነገር ግን ይብልጥ አምባገነን ሆኖ ነው የመጣው:: መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት አለበት:: ሌሎችም ዜጎችና ፓርቲዎች የተሳተፉበት፣ ነፃነት የሚነግስበት፣ ተጠያቂነት የሚሰፍንበት፣ ግልጽነት የሚስፋፋበት ሁኔታ ነው መዋቅራዊ ለውጥ::»

**አቶ ገብሩ አስራት / የአረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ለሉአላዊነት ሊቀ መንበር**

***«የኢህአዴግ አመራሮች ኃላፊነትን ለማስረከብ ዝግጁ ነን እያሉ ነው:: እንዴት ያዩታል?» በሚል ሳምንታዊው «ዳጉ ኢትዮጵያ» ጋዜጣ ጠይቋቸው ሲመልሱ::***

*«...ሲጀመር ቦብ ማርሊ ፖለቲከኛ አይደለም:: ግን የፖለቲካ ነጥቦችን ሊያነሳ ይችላል:: ፖለቲካ እኮ ይህን ያህል የሚፈራ ነገር አይደለም:: ህይወታችን ነው ጉዞአችን ነው:: ስሙ ፖለቲካ ሆነ እንጂ የየዕለት ማህበራዊ ህይወታችን ጉዞ ነው:: በዚህ ጉዞ ውስጥ ቴዲ ይህንን ህይወት በዘፈኑ ውስጥ ጠቅሶት አላለፈም ሊባል አይችልም:: ይህ እውነት ነው::»*

**አርቲስርት ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ)**

***«...ስለአንተ የወጡ ጽሁፎችን ስንመለከት አርበኛ፣ የህዝብ ድምጽ የሚያሰማ፣ የማሕበራዊ ጉዳዮች ሂሰኛ እንደቦብ ማርሊ ፖለቲካዊ አቋም እና ስሜት ያላቸው ዘፈኖች የሚዘፍን ይሉሃል አንተ ምን ትላለህ?» ተብሎ ከሸገር ኤፍ ኤም ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠው ምላሽ::***

# ዜናዎች

# የቴዲ አፍሮ የአውሮፓ ኮንሰርት እና ውዝግቡ

- ***በስታዲየም ያቀረበው ኮንሰርት በኢቴቪ መቅረቡ አነጋግሯል***

*ከአንድ ወር በኋላ በአውሮፓ የተለያዩ ከተሞች ኮንሰርት ለማቅረብ በዝግጅት ላይ የሚገኘው አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) በስዊድን፣ በኖርዌይ፣ በሆላንድ እና በጀርመን የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በኮንሰርቱ ላይ እንዳይገኙ በየአገሮቹ ያሉ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባላት እና ተቃዋሚ ወገኖች አዲስ የቅስቀሳ ዘመቻ ጀምረዋል::*

*እንደነዚህ ወገኖች መግለጫ ከሆነ «ድምፃዊው ከእስር እንዲለቀቅ ከፀሎት ጀምሮ በሰላማዊ ሰልፎች ድምጻችንን እንዳላሰማን ዛሬ ከእስር ሲለቀቅ በየአገራቱ ያሉ ለገዢው ፓርቲ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ኮንሰርቱን ለማዘጋጀት ከድምጻዊው ጋር መፈራረማቸው እጅግ አሳዝኖናል» ብለዋል::*

*በኦስሎ ኖርዌይ የሚገኙ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባላት በበኩላቸው «በኖርዌይ ለምትገኙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ!!» በሚል ርዕስ በድረ ገጾች ባሰራጩት መግለጫ ድምፃዊው ህዳር 19 ቀን 2002 ዓ.ም የኖርዌይ ርእሰ ከተማ በሆነችው ኦስሎ*

ኮንሰርቱን ለማቅረብ የተፈራረመው ከአቶ ደስታ ወ/ስላሴ እና ሌሎች ጋር መሆኑን አውስተው ግለሰቡ በኖርዌይ የገዢው ፓርቲ ተጠሪ በመሆናቸው ኢትዮጵያውያን በኮንሰርቱ ላይ ሊገኙ አይገባም ሲሉ የተማጽኖ ጥሪ አቅርበዋል።

ይህንኑ በማስመልከት አውራምባ ታይምስ በስልክ ጥያቄ ያቀረበላቸው አንድ በኖርዌይ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ አባል በበኩላቸው «ድምፃዊው የሁሉም ኢትዮጵያዊ ሐብት ነው ብለን ከተቀበልን የኮንሰርቱ አዘጋጆች የፖለቲካ አቋም በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የውዝግብ ርዕስ የሚሆነው ለምንድነው?» ካሉ በኋላ ኮንሰርቱን ለማዘጋጀት የተፈራረሙት ግለሰቦች ኮንሰርት የማዘጋጀት ብቃት ካላቸው የገዢው ፓርቲም ሆነ የተቃዋሚ ደጋፊ መሆናቸው ርዕስ ሊሆን አይገባም። ይህ ድምፃዊው ከፈለገው ወገን ጋር ውል የመዋዋል መሰረታዊ መብቱን መጣስ ነው።» ሲሉ አስተያየት ሰጥተውናል። በዚህ ጉዳይ ላይ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁንም ሆነ ማናጀሩ አቶ አዲስ ገሰሰ አስተያየት እንዲሰጡ ለማድረግ ዝግጅት ክፍላችን ያደረገው ሙከራ ለጊዜው አልተሳካም።

በተያያዘ ዜና ገብተው ዝግጅቱን ከታደሙት ይበልጥ ትኬት አጥተው የተመለሱበትና ፣ በልመና የሚተዳደሩ ወገኖችን መልሶ ለማቋቋም ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የተሰበሰበበት፤ የአዲስ አበባ ስታዲየም ደማቅ ኮንሰርት የፊልም ቀረፃ ሁኔታ አነጋጋሪ ሆኗል።

በዕለቱ በርካታ ካሜራዎች የዝግጅቱን ሁነት በምስል መቅረጫቸው ላይ ለማስቀረት ከመድረክ ፊት ለፊት ተሰትረው ነበር። ከእነዚህም መሀከል የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና የአዲስ አበባ መስተዳደር ቴሌቪዥን ጣቢያ ካሜራዎች ይገኙበት የነበረ ሲሆን ቴዲ በሁለቱ ጣቢያዎች ዘፈኖቹ እንዳይተላለፉ ደብዳቤ መጻፉንና ደብዳቤ የፃፈበት ምክንያት ደግሞ የኮንሰርቱን ዝግጅት ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በዲቪዲ እና በቪሲዲ አሳትሞ ገበያ ላይ ለማዋል ከስምምነት ላይ ደርሶ እንደነበር የአውራምባ ምንጮች ገልጸዋል።

ይህንኑ ጉዳዮ በተመለከተ የቴዲ ጠበቃ ለሆኑትን አቶ ሚሊዮን አሰፋ ከዝግጅት ክፍላችን ጥያቄ የቀረበላቸው ሲሆን በሰጡን ምላሽ «ቴዲ አፍሮ ለኮንሰርት ስራ ከተጓዘበት ከውጪ አገር ሲመለስ ተነጋግረን አድርግ የሚለኝን አደርጋለሁ። በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ነገር ልናገር አልችልም» በማለት ተጨማሪ መረጃ ከመስጠት ተቆጥበዋል።

በሌላ መልኩ ደግሞ አውራምባ ታይምስ ያነጋገራቻቸው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የመዝናኛ ክፍል ኃላፊ አቶ ሺበሺ «ውሸት ነው የገባ ምንም አይነት ደብዳቤ የለም» ብለዋል።

የአዲስ አበባ መስተዳድር የቴሌቪዥን ጣቢያ ባልደረባ ቴዲ አፍሮ በጠበቃው አማካኝነት ዝግጅቱ እንዳይተላለፍ የሚል የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ማስገባቱን ለአውራምባ ታይምስ ገልጸዋል። አክለውም «አቶ ሚሊዮን በሚባሉት የህግ አማካሪው አማካኝነት «ጉዳዩ የህግ ማስጠንቀቂያ ስለ መስጠት፣ የቴዲ ኮንሰርት ላይ ተገኝታችሁ ሙሉ ቀረፃ ማከናወናችሁን ደንበኛዬ ገልጾልኛል። ደንበኛዬ ደግሞ የኮንሰርቱን ዝግጅት ከሌሎች

ድርጅቶች ጋር በቪሲዲና ዲቪዲ ለመሸጥ የተዋዋለ ስለሆነ በምንም መልኩ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ አየር ላይ እንዳይውል እንጠይቃለን፡፡ ይህ ሳይሆን ቢቀር በሕግ ሊያስጠይቃችሁ እንደሚችል እናስታውቃለን» የሚል መሆኑን አስታውሰው በዚህ ምክንያት «ውዝግብ ውስጥ መግባት ስላልፈለግን ቀረጻውን አየር ላይ ከማዋል ተቆጥበናል» ብለዋል፡፡

# የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ምግቦች በገበያ ላይ ውለዋል

## «ችግሩን የመከላከል እቅድ ነድፈናል፡፡»

*/የኢትዮጵያ የጤናና ስነ-ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት/*

ኤልያስ ገብሩ

የኢትዮጵያ የጤናና ስነ-ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተቋሙ የ2001 ዓ.ም የስራ ክንውን ሪፖርትና የ2002 ዓ.ም ዕቅድ ዙርያ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጠ፡፡

በጋዜጣዊ መግለጫው ወቅት ዶ/ር ፀሀይነሽ መለሰ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር፣ ዶ/ር አምሃ ከበደ የምርምርና ቴክኖሎጂ ም/ዳይሬክተርና ዶ/ር ዳዲ ይልማ የፐብሊክ ጤና ማናጅመንት ዋና ሓላፊ በሚመለከታቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ አጠር አጠር ያሉ ሪፖርቶችን አቅርበዋል፡፡

ዋና ዳይሬክተሯ ዶ/ር ፀሀይ ኢንስቲትዩቱ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የስነ ምግብ ችግሮችን ተደራሽ ያደረጉ ችግር-ፈቺ ምርምሮችን በማካሄድ፣ ለድንገተኛ የህዝብ ጤና ችግሮች ትንቢያ በመዘጋጀት፣ በመከላከልና በመቆጣጠር፣ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው የላብራቶሪ ስርዓት በመገንባት የህብረተሰቡን የጤና መጠበቅና የማሳደግ ተልዕኮ እንዳለው ገልፀዋል፡፡

በ2001 ዓ.ም የቢ.ፒ.አር ትግበራ በመጋቢት ወር ላይ እንደተጀመረ ተናግረው በህዝቡ የጤና ችግር ዙሪያ ብዙ ተግባሮች እንደተከናወኑ፣ በአዲሱ ጉንፋን፣ በማጅራት ገትር፣ በወባ፣ በእንስሳት ቆዳ በሽታ፣ በዕብድ ውሻ ክትባት፣ የላቦራቶሪ ስራ፣ በቲቢ፣ በሳንባ ነቀርሳ፣ በአተትና በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የህዝቡን ጤና ለማበልፀግ የቅኝት፣ የምርምርና ተግባራዊ ስራዎች እንደተከናወኑና በቀጣይም በፊት ከነበረው በተሻለ ብዙ የተጀመሩና አዳዲስ ስራዎችን እንደሚሰሩ አብራርተዋል፡፡

ዶ/ር ዳዲም በህብረተሰቡ የጤና አደጋ ቁጥጥርና የምርምር ቴክኖሎጂ ሽግግር ዋነኛ የስራ ሂደቶች ሆነው በወረርሽኝ መልክ ያሉ በሽታዎችን፣ የምግብ እጥረት (malnutrition) እና በተፈጥሮ አደጋ የሚፈናቀሉ ዜጐችን ለመርዳት ከሚመለከታቸው አካላትና ክልሎች ጋር በጋራ እንደሚሰሩ ጠቁመዋል፡፡ ዶ/ር አምሃም የምርምርና ቴክኖሎጂ የስራ ሂደት በ5 ዳይሬክተሮች ተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች፣ በባህላዊና

ዘመናዊ መድሃኒቶች፣ በስነምግብ ምርምር፣ በክትባትና ምርምር እንዲሁም በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ትኩረት በማድረግ 95 በመቶ የምርምር ስራ የህብረተሰቡን ችግር በሚፈቱ ጉዳዮች ላይ እንደሚሰሩ ሪፖርታቸውን አቅርበዋል፡፡

በመጨረሻም ከተለዩ የመንግስትና የግል ጋዜጠኞች ጥያቄ ቀርቦላቸው ምላሽ የተሰጠ ሲሆን አውራምባ ታይምስም የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ምርቶች በተለይም ጣፋጭነት ያላቸው የብስኩትና ቸኮሌት አይነቶች በመዲናችን አዲስ አበባ በተለያዩ ቦታዎች በጎዳና ላይ እየተሸጡ እንደሚኙና በተጠቃሚው ህብረተሰብ ላይ የሚያስከትሉትን የጤና ችግርች እንዴት ታዩታላችሁ? የተመሪማሪዎች በአንድ ቦታ ላይ ፀንቶ ያለመስራት ሁኔታና ችግር መፍትሄው ምንድን ነው? በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ዶ/ር ፀሀይነሽና ዶ/ር ዳዲ ሲመልሱ በተነሱት ጉዳዮች ላይ ችግሮች እንዳሉ ገልፀው የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ምርቶች ከሚመለከተው የመንግስት አካላት፣ ከጤና ጥበቃና ከአቅራቢዎች ጋር በቀጣይ ተቀናጅተው የመከላከል ዕቅድ እንዳላቸውና በተመራማሪዎች በኩል ያለው ሁኔታ ኢንስቲትዩቱ አስተምሮ ካሰለጠናቸው በኋላ ለተወሰነ አመት ኢንስቲትዩቱን ለማገልገል የሚገቡት ውል እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ ነገር ግን ማንኛውም ሰራተኛ የፈለገበት ቦታና የተሻለ አማራጭ ሲያገኝ ሄዶ የመስራት መብት እንዳለው ጠቁመዋል፡፡

## ልዩ ዘገባ

# ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ድርጅት የሚከፈለው 50 ብር ምንድነው?

**ሀ. ግብር**
**ለ. አገልግሎት**
**ሐ. ፍቃድ ማደሻ**
**መ. መልሱ የለም**

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት (ኢሬቴድ) በተለየ ባሳለፍነው ዓመት መጨረሻ አካባቢ ከፍተኛ ቅስቀሳ ላይ ነበር፡፡ «ቴሌቪዥናችሁን አስመዝግቡ፤ ዓመታዊውን ክፍያ ፈጽሙ፡፡» በከፍተኛ የቅስቀሳ ስትራቴጂም በጥቂት ወራት ውስጥ ከአዲስ አበባ ነዋሪዎች ብቻ 50 ሚሊዮን ብር መሰብሰቡ ተነገረ፡፡ 50 ብር መጣም ቀረ እምብዛም የማያስጨንቀው ሰው ይኖራል፡፡ በዚያው ልክም የምንዱባን አገር ነንና የ50 ብር ጉዳይ የሚያሳስበንም ሞልተናል፡፡ ይሁንና ግን የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ከገንዘብ መጠኑ ጋር ንክኪ የለውም፤ የኢትዮጵያ ህዳሴ መበሰርንም አይቃወምም፡፡ ይልቁንስ ድርጅቱ

በየዓመቱ የሚሰበሰበው 50 ብር (በነፍስ ወከፍ) መሠረቱ ምንድነውና በተያያዥ አዋጆችስ አግባብነት አለው ወይ የሚለውን ይመለከታል።

ሁሉም ማለት ቢቻልም፣ አብዛኛው ህዝብ እንደሚያስበው ይህ ክፍያ ከግብር ጋር ተያያዥነት ይኖረው ይሆን? ወይንስ ለሚሰጠን አገልገሎት የሚጠበቅብን የአገልግሎት ክፍያ ነው? በየዓመቱ መክፈላችን ከፈቃድ እደሳ ጋር የሚያገናኘው መንገድ እንዳለስ? አነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ማዛናዊነትን ለማሟላት የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ድረስ መሄድ ሳያስፈልገን ከድርጅቱ በላይ የሆነውን፣ ድርጅቱን ያቋቋመውን አዋጅና ተያያዥ ሕጐች መሠረት በማድረግ ብቻ የሚከተለውን ዳሰሳ ልናቀርብ ተገደናል።

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመው በደርግ ዘመነ መንግስት በትእዛዝ ቁጥር 50/1960 አማካኝነት በ1960 ዓ.ም ነው። ከዚያም የድርጅቱን ሥልጣን ለመወሰን «የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልገሎት ድርጅት አዋጅ ቁጥር 15/1967» የተሰኘውን ሕግ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደሩ ምክር ቤት በጥር ወር 1967 ዓ.ም አፀደቀ። ቀጥሎም በተመሳሳይ ዓመት ነሐሴ ወር ላይ ተመሳሳዩን አዋጅ ለማስፈፀም በወቅቱ የማስታወቂያ ሚኒስትር በነበሩት ሜጀር ያቆብ ገብረ እግዚአብሔር ፊርማ «የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት ደንብ ቁጥር 20/1967» ወጣ።

የደርግ ዘመነ መንግስት አበቃ። እናም የሽግግር መንግስቱ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅትን በአዲስ መልክ በማዋቀር የድርጅቱን የሥራ እድገትና ቅልጥፍና በተሻለ መንገድ እንዲራመድ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በማመኑ ከሃያ ዓመታት በኋላ በሕገመንግስት ጉባኤ የመሸጋገሪያ ውሳኔ መሠረትና በወቅቱ የሽግግር መንግስቱ ፕሬዝዳንት በነበሩት በአቶ መለስ ዜናዊ ፊርማ በ1987 ዓ.ም አዲስ አዋጅ ታወጀ። ይህ አሁን በሥራ ላይ የሚገኘው አዋጅ «የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 114/1987» ይሰኛል። ኋላ ላይ የምንመለስበት ቢሆንም፣ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ተፈፃሚነት ስለሚኖራቸው ሕጐች ሲያወሳ አስቀድመን የጠቀስናቸው የደርግ ዘመነ መንግስት ሕጐች፣ ማለትም አዋጅ ቁጥር 15/1967 እና ደንብ ቁጥር 20/1967 <u>እንደ አግባቡ</u> በድርጅቱ ላይ ተፈፃሚነታቸው መቀጠሉ ልብ ይባል፤ የተሰመረበት ቃልም እነደዚያው። ከዚህ በኋላ ይህንን ማቋቋሚያ አዋጅ ለማሻሻል በ1989 ሌላ ሕግ የወጣ ቢሆንም ከርዕሰ ጉዳያችን ጋር ተያያዥነትን እንደሌለው በማረጋገጣችን ለዛሬ ተነሺነት አይኖረውም።

የ50 ብሯ ጉዳይ ከነዚህ አዋጆች አታልፍምና እንድንከፍላት መጠየቃችን ለግብር ይሁን ለሚሰጠን አገልግሎት፣ አልያም ለፈቃድ ማደሻ የሚለውን ወደማወቁ እናምራ።

## ግብር

እሩቅ ከመሄዳችን በፊት የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅትን በአዲስ መልክ ባዋቀረው የ1987 አዋጅም ሆነ የ1967 አዋጅ እና ደንብ ውስጥ «ግብር» የሚለው ቃል እንዳልተጠቀሰ እናስታውሶ:: ሆኖም ለድርጅቱ የሚከፈለውን ገንዘብ ግብር ከመሰብሰብ ጋር ለሚያያይዙት ሰዎች ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ አንድ ግለሰብ ንብረት (ቴሌቪዥን) ስላለው ብቻ ግብር እንደማይጠየቅ ማስገንዘብ ግድ ነው::

አንድ መንግስት ዋናው የበጀት ምንጩ ከህዝብ የሚሰበሰበው ግብር ነው (ወይም ሊሆን ይገባል):: ማንኛውም ዜጋ በመቀጠርም ሆነ በመነገድ ከሚየገኘው ገቢ ለመንግስት ግብር ሊከፍል ይገባዋል:: እንዲሁም ንብረቱን በማከራየትም ሆነ በሌላ መንገድ ለሚያገኘ ው ገቢ ግብር መክፈል ሲጠበቅበት ንብረቱን በመጠቀሙ ግን የሚከፍለው ሳንቲም አይኖርም:: ለምሳሌ ቤታችን ያለውን፣ በገንዘባችን የገዛነውን ወንበርና ጠረጴዛ በመጠቀማችን ክፍያ የሚጠይቀን አይኖርም፤ ወንበርና ጠረጴዛው ባለቤትነቱ የሌላ ሰው ሆኖ በኪራይ የምንጠቀምበት ካልሆነ በቀር:: ቴሌቪዥንም ከሌሎች ንብረቶች የሚለይበት ጽኑ ምክንያት ባለመኖሩና ባለቤትነቱ የግለሰቡ በመሆኑ ግለሰቡ ቴለቪዥኑን አከራይቶ ወይም ሸጦ ገቢ (ትርፍ) እስካላገኘበት ድረስ ግብር አይጠየቅም::

ጉዳዩን በሌላ መልኩ ስንቃኘው፣ በፌደራሉ የመንግስት አወቃቀር (ኢሬቴድ በፌደራል መንግስቱ ስር በመሆኑ) ግብር የመሰብሰብ ስልጣን ለየትኛው የመንግስት መሥሪያ ቤት የተሰጠ ነው? የፌደራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሥራው ምንድነው? ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ወደ ኢፌዴሪ ሕገመንግስት በማምራት የፌዴራል መንግስቱንና የክልል መስተዳደሮችን የግብር አሰባሰብ ሥልጣን ስንመለከት ንብረትን በመጠቀም ግብር የሚከፈልበት ሁኔታ ባይጠቀስም በንብረት አማካኝነት ከሚመነጭ ገቢ ግብር የመሰብሰብ ሥልጣን እንኳን ለክልል መስተዳደሮች የተሰጠ ነው:: (አንቀጽ 96 እና 97 (6) ይመልከቱ::)

እንዲሁ አጽንኦት ለመስጠት ፈልገን እንጂ ከላይ የጠቀስነው በቂ ነበር - በሦስቱም ሕጎች ስለግብር አልተነሳም፤ ሊነሳም አይችልም:: ስለዚህ ለኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን የሚከፈለው 50 ብር ግብር አለመሆኑንና ከነጭራሹ ከግብር ጋር የተያያዘ አለመሆኑን ህብረተሰቡ እንዲገነዘብ እንፈልጋለን::

# አገልግሎት

የ1987 የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ የድርጅቱን ሥልጣን እና ተግባር በሚዘረዝርበት አንቀጽ 3 (10) ድርጅቱ «ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል፤ እንደአስፈላጊነቱ በከፊል ወይም በሙሉ ከክፍያ ነፃ ያደርጋል» ሲል ይደነግጋል:: ከዚህም የሚሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ ከድርጅቱ የበጀት ምንጮች አንዱ እንደሆነ ተገልጿል::

አዋጁ «የአገልግሎት ክፍያ» ማለቱ ድርጅቱ ለሚያሰራጫቸው ፕሮግራሞች ሊከፈለው የሚገባ ክፍያን ከሆነ ከብዙ ነባራዊ እውነታዎች ጋር የሚጋጭ ይሆናል::

የመጀመሪያውና በሁላችንም ዓይምሮ ውስጥ የማከሰተው ጥያቄ «ድርጅቱ የሚያሰራጫቸው ፕሮግራሞች ነፃ አይደሉም እንዴ?» የሚለው ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ መነሻው የድርጅቱ ፕሮግራሞች «በሳተላይት ዲሽ» ነፃ ፕሮግራሞች ተብለው ያለክፍያ ከሚታዩት ውስጥ መመደባቸው ነው፡፡ በርግጥ በቴሌቪዥን አንቴና ተጠቅሞ ፕሮግራሞቹን የሚከታተል ሰው የፕሮግራሞቹን በነፃ መተላለፍ አይገነዘብ ይሆናል፤ ባለመገንዘቡ ግን ክፈል ሊባል አይገባውም፡፡ አልያም ደግሞ በሳተላይት ዲሽ ለሚመለከቱ ነፃ፣ በቴሌቪዥን አንቴና ለሚመለከቱ በክፍያ ልንል ነው፡፡

የድርጅቱ ፕሮግራሞች ነፃ ስለመሆናቸውና ህዝቡ የሚከፍለው 50 ብር የአገልግሎት ክፍያ አለመሆኑን ለማሳየት በሳተላይት ዲሽ ነፃ ተብለው መሰራጨታቸው ማረጋገጫ ወይም ማሳመኛ አይሆንም ከተባለ ደግሞ ወደሚቀጥለው እንቀጥል፡፡ ከአገልግሎት ጋር በተያያዘ ሌላ አገልግሎት ሰጪ የመንግስት ተቋምን እንደምሳሌ እናንሳ - የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን፡፡

ቴሌ የስልክ መስመሮችን በመዘርጋት ከዘመድ አዝማዶቻችን ጋር እንድንገናኝ ያደረገበትን አገልግሎት ይሰጠናል፡፡ ይሄን ያህል አገልግያችኋለሁ ሲለን ይሄን ያህል እንከፍለዋለን፡፡ ቴሌ አገልግሎት እንዲሰጠን፣ እኛም የአገልግሎት ክፍያውን በአግባቡ እንድንፈጽም የሚያደርገን ወይም የሚያስገድደን አንድ ነገር በመካከላችን አለ - ውል (Contract)፡፡ ውል በተዋዋዮቹ መካከል እንደ ሕግ ይሰራልና የሚጠበቅብንን ካልከፈልን ወይም የሚጠበቅበትን ካላገለገለን እኛና ቴሌ ፍርድ ቤት እንቆማለን፤ ተፈቃቅደን የተዋዋልነው በመሆኑም በውላችን መሠረት እንዳኛለን፡፡ ታዲያ እኛና የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት አገልግሎት ለመስጠትና ለመቀበል የተዋዋልነው ውል አለን? የተዋዋለ ካለ በውሉ መሠረት የአገልግሎት ይክፈል፡፡ ያልተዋዋል ሰው ግን አሁን በዓመት 50 ብር እየከፈለ የሚገኘው የአገልግሎት ክፍያ አይደለም፡፡

እሺ፣ ቴሌስ የደወልንበትን ቦታና ደቂቃ አስልቶ ይህን ያህል ክፈሉ ይለናል፣ 24 ሰዓት የኢሬቴድ ፕሮግራሞችን የኮመኮመው እና «አል ጃዚራን» ወይም በዲቪዲ አማካኝነት የሆሊውድ ፊልሞችን መመልከት የመረጠው በምን ሂሳብ ነው እኩል 50 ብር የሚጠየቁት፡፡ ክፍያው አገልግሎት ነው ከተባለ በተገለገልነው መጠን መክፈል አይገባንም ነበር?

አንዳንድ ጊዜ ያለውል በግዴታ (ወይም በውዴታ ግዴታ) የምንቀበላቸውና የምንሰጣቸው አገልግሎቶች አሉ፡፡ ለሀገርና ለህዝብ ጥቅም ሲባል የብሔራዊ አገልግሎት (ውትድርና) መስጠት ሊጠበቅብን ሲችል በሌላ መልኩ ደግሞ ወረርሽኝም ሆነ ሌላ በሽታን ለመከላከል የክትባት አገልግሎት ሊሰጠን ይችላል፡፡ የያዝነው ርዕሰ ጉዳይ ግን ከሁለቱም ወገን አይመደብም፡፡

ሌላ ምሳሌ፣ ለዘመኑ ምስጋና ይግባውና «ቲቪ ካርድ» - በኮምፒዩተር ቴሌቪዥን መመልከት የሚያስችል፤ እንዲሁም ተንቀሳቃሽ ስልክ ሆኖ ቲቪ ቻናል ያለው ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅሞ የድርጅቱን ፕሮግራሞች የሚከታተል ሰው የአገልግሎት አለመጠየቁ 50 ብሯ የአገልግሎት አለመሆኗን ያስረዳል፡፡

ይህ «የአገልግሎት ክፍያ» ሲል ያስቀመጠው የ87 አዋጅ ክፍያው 50 ብር ስለመሆኑ፣ በምን ስሌት እንደሚቀመርም ሆነ በስንት ጊዜ እንደሚከፈል የገለፀው ነገር የለም:: ታዲያ እቺ 50 ብር ከየት መጣች ቢባል ከ1967 የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት ደንብ ቁጥር 20/1967 መሆኑን እንመለከታለን:: እዚህ ላይ ከወደላይ ያስመርንባትንና ኋላ እንመለስባታለን ያልናትን «እንደ አግባቡ» የተሰኘችውን የ87 አዋጅ አንቀጽ 14 ቃል ልናነሳት ነው፤ ወደኋላም እንደ አግባቡ እንጠቀማታልን::

የ1967 ሕጐች ተፈፃሚነታቸው «እንደ አግባቡ» ነው ስንል በ87 አዋጅ ላይ ከተቀመጡ ድንጋጌዎች ጋር የሚስማሙና በአዲሶቹ ድንጋጌዎች ንፍቀክበብ ውስጥ የሚገኙ፣ እንዲሁም ለአዲሶቹ ድንጋጌዎች አተገባበር አስፈላጊነታቸው ጉልህ የሆነ አንቀፆቻቸው አልተሻሩም፣ አሁንም በሥራ ላይ ናቸው ማለታችን ነው:: ስለዚህ «የአገልግሎት ክፍያ» የሚለውን የ87 አዋጅ ድንጋጌ መነሻ በማድረግ በ67 ሕጐች ውስጥ እንደ አግባቡ ተፈፃሚ የሚሆኑ አንቀፆችን እንፈልግ፤ በዚያውም የ50 ብርን ምንጭ እንመልከት::

በደርግ ዘመነ መንግስት ድረጅቱ በአዋጅ ቁጥር 15/1967 አንቀጽ 3 (4) ላይ «ለሚሰጠው ፈቃድና በቴሌቪዥንና በራዲዮ ፕሮግራም ውስጥ ለሚሸጠው ጊዜ የአገልግሎት ዋጋ ለመወሰንና ለመሰብሰብ» ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር:: በሚቀጥለው ርዕስ የምንመለከተው የፈቃድ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት ድርጅቱ በቴሌቪዥን የመጠቀም ፈቃድ እንዲሰጥ ሥልጣን ስለተሰጠው ከአየር ጊዜ ሽያጭ በተጨማሪ ፈቃድን አስመልክቶ ክፍያ እንደሚሰበስብ ይህ ድንጋጌ ያስረዳል:: ይህ አንቀጽ ስለ ሁለት ክፍያዎች ብቻ ስለማውራቱ ልብ ይሏል::

የ50 ብር ነገር ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ የተነሳው ግን ይህንን የአዋጁን አንቀጽ ለማስፈፀም በተደነገገው የደንብ ቁጥር 20/1967 አንቀጽ 5 (3) ላይ ነው:: ይሁንና ይህ ድንጋጌ 50 ብሩ ፈቃድ የመስጠት አገልግሎትን የተመለከተ እንጂ የፕሮግራም ስርጭትን እንዳልሆነ ይነግረናል፡- «ማንኛውም የቴሌቪዥን ባለቤት ወይም ባለይዞታ ፈቃድ ሲሰጠው ሃምሳ (50) ብር የአገልገሎት ዋጋ በየዓመቱ ለመዝጋቢው ባለስልጣን ይከፍላል::» እናም በዚህ ጉዳይ ላይ የ67 ሕጐችን ተፈፃሚ ልናደርጋቸው አይቻለንም:: በዚህ ምክንያት ለድርጅቱ እየከፈልን የምንገኘው የአገልግሎት ሊሆን አይችልም::

ስለዚህም የድረጅቱ የፕሮግራም ስርጭት ነፃ በመሆኑ፣ ከድርጅቱ ጋር አገልግሎትን በተመለከተ የተዋዋልነው ውል ባለመኖሩ፣ እንዲሁም በ67 ሕጐች መሠረት ቢሆን እንኳን 50 ብሩ የሚከፈለው ፈቃድን አስመልክቶ በመሆኑ በየዓመቱ እንድንከፍል የሚጠበቅብን ገንዘብ የአገልግሎት አይደለም:: ታዲያ አሁን በሥራ ላይ የሚገኘው የ87 አዋጅ «የአገልግሎት ክፍያ» ሲል ፈቃድ የመስጠት አገልግሎት ይሆን?

## ፈቃድ

የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት በ1960 በትዕዛዝ ከተቋቋመ በኋላ በ1967 ሥልጣኑን ለመወሰን አዋጅ ቁጥር 15/1967 እንደወጣለት ከላይ ተመልክተናል:: እናም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 (1) መሠረት የቴሌቪዥን ባለቤትነትን ወይም ባለይዞታነትን የመመዝገብና ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር:: ከሁሉም በላይ ደግሞ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር 20/1967 በአንቀጽ 7 ላይ «ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ካልያዘ በቀር በቴሌቪዥን <u>መጠቀም</u> አይችልም::» ይላል:: /መስመር ተጨምሯል/

ነገር ግን የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በ1987 በአዲስ መልክ ሲቋቋም በአስራ ሁለት ንዑስ አንቀፆች የተዘረዘሩ ሥልጣንና ተግባራት በአዋጅ የተሰጡት ሲሆን ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን አልተካተተም:: አሁን በሥራ ላይ በሚገኘው በ87 አዋጅ የድርጅቱን ሥልጣንና ተግባር የሚዘረዝረው አንቀጽ ከጅማሬው «ድርጅቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል» ሲል ሥልጣንና ተግባሮቹ የተዘረዘሩት ብቻ ወይም «exhaustive» መሆናቸውን ያመላክተናል:: ከነዚህ ውጪ ሥልጣንም ተግባርም የለውም::

ይሁንና ግን የ1967 ሕጎች እንደ አግባቡ ተፈፃሚ ስለመሆናቸው በዚሁ አዋጅ ላይ መደንገጉ ክፍተትን የሚያመቻች ስለሚመስል በነዚህ ሕጎች ተሰጥቶት የነበረው ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን አሁንም እንደሚቀጥል ተደርጐ በስህተት ሊወሰድ ይችላል:: ሆኖም ከላይ ለማብራራት እንደሞከርነውም፣ የ67 ሕጎች የድርጅቱን ሥልጣንና ተግባር በተመለከተ ተፈጻሚነታቸው እንደ አግባቡ ወይም በ87 አዋጅ ከተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባሮች በተያያዘ ብቻ ነው:: ይህንን ካስገነዘብን፣ ድርጅቱ በቴሌቪዥን ስለመጠቀም ፈቃድ የመስጠትም ሆነ የፈቃድ ማደሻ ገንዘብ የመቀበል ሥልጣኑ ከ1987 ዓ.ም በኋላ ቀርቷል:: ማለትም 50 ብሩ ከፈቃድ እደሳ ጋር አይገናኝም:: ሆኖም «የ1967 ሕጐች ተፈፃሚነት አላቸው» ቢባል እንኳን ድንጋጌዎቹ የሕግነት መርህን ያልተከተሉ መሆናቸውን፣ በዚህም ምክንያት የተሸሩ መሆናቸውን ማስገንዘብ ተገቢ ነው::

በቴሌቪዥን ለመጠቀም ፈቃድ ማግኘት ከሚጠይቀው የደንብ ቁጥር 20/1967 ድንጋጌ እንጀምር:: «ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ካልያዘ በቀር በቴሌቪዥን መጠቀም አይችልም::» ይላል:: እዚህ ላይ ድንጋጌው በቴሌቪዥን መጠቀምን ወይም የቴሌቪዥን ባለቤት መሆንን አልከለከለም፤ ነገር ግን በቴሌቪዥን ለመጠቀም ፈቃድ ማግኘትን ይጠይቃል::

ከድንጋጌው መንፈስና ሕጉ ከወጣበት ዘመን አንፃር «መጠቀም» የሚለው ቃል ምንን ያመለክታል? በዚያን ወቅት ቪሲዲ፣ ዲቪዲ፣ ሳተላይት ዲሽ የመሳሰሉት የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለመታደም ባለመታደላችን ሳይሆን አይቀርም ቴሌቪዥን ያለው ሰው ቴሌቪዥኑን የሚጠቀምበት በኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት የሚሰራጨውን ፕሮግራም ለመመልከት ብቻ እንደሆነ አድርጐ ቅድመ ግምት (presumption) ይወስዳል፤ ይህ ቅድመ ግምት በጥቂት ዓመታት ውስጥ ውድቅ ሊሆን ቢችልም:: እናም ያን ጊዜ ድርጅቱ ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን የተሰጠው የደርግ

ሥርዓት ሆነና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞቹን በመከታተል ረገድ ብቻ እንጂ በአሁኑ ዘመን ያሉትን የቴሌቪዥን ጥቅሞች እንደማይመለከት መረዳት ይቻላል።

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በሬዲዮ አማካኝነት ለሚሰራጨው ፕሮግራሙ ፈቃድ እና ክፍያ ለምን አልጠየቀም? ለዚህ ትክክለኛው ምላሽ ህዝቡ ቀድሞውኑ በሬዲዮ የድርጅቱ ያልሆኑ ፕሮግራሞችን ይከታተል ስለነበር ነው። የወቅቱ ሕግ ለሬዲዮ አጠቃቀምም ፈቃድ ቢጠይቅ ኖሮ የድርጅቱ ላልሆኑ ፕሮግራሞችም ድርጅቱን ፈላጭ እና ቆራጭ ማድረግ ስለሆነበት ነው።

ታዲያ በዚህ በሰለጠነና ህዳሴውን በምናበስርበት ዘመን የቴሌቪዥን ጥቅሙ የድርጅቱን ፕሮግራሞች ማሰራጨት ብቻ ይመስል ስለምን ፈቃድ እንድንይዝ እንጠየቃለን? ቀድሞውኑ ይህንን የሚለው ሕግ ለረጅም ዘመን የማስተዳደር ብቃትን ባለመላበሱ የሕግነት መርህን ከመቃረኑ በላይ አዳዲስ ሁኔታዎች በሚከሰቱበት ጊዜ እርሱ ተሽሮ ሌላ አስተዳዳሪ ሕግ ሊተካለት ይገባ ነበር። በእኛ አመለካከት በ1987 ድርጅቱን በአዲስ መልክ ያቋቋመው አዋጅ በቴሌቪዥን ስለመጠቀም ፈቃድ የጠቀሰው ነገር ያለመኖሩ ዋነኛው ምክንያት ያ ይመስለናል።

በመሠረቱ «ፈቃድ» ምንድነው፣ ለምንስ ያስፈልጋል? አንዳንድ ነገሮችን የሚሰራ ወይም የሚጠቀም ሰው ለሦስተኛ ሰው የሚሰጠውን ግልጋሎት ለመቆጣጠር (ጤና ጥበቃ የሚሰጠው ዓይነት ፈቃድ)፣ ሕጋዊነትን ለመቆጣጠርና ተገቢውን ግብር ለመሰብሰብ (የንግድ ፈቃድ)፣ እንዲሁም ለአጠቃቀሙ እውቅና ለመስጠትና ፀጥታ ለማስፈን (ጦር መሳሪያ የመያዝ ፈቃድ) ከመንግስት ፈቃድ ማግኘት ይጠበቅበት ይሆናል። አንድ ግለሰብ በወንበሩ ለመጠቀም ግን ፈቃድ መጠየቅ አያስፈልገውም፤ በቴሌቪዥን መጠቀምም ከዚህ አይለይም። ግለሰቡ ቴሌቪዥን 24 ሰዓት ሙሉ መጠቀሙ ከሰፊው በንብረት የመጠቀም መብት አንዱ ተግባራዊ መሆኑ ነው። ይህንን ስንመለከት በርግጥ የ1967 ሕጐች መሻር ይገባቸው ነበር ያስብለናል። ከዚህም በላይ ድርጅቱ ፈቃድ የሌለውን ቴሌቪዥን ባገኘ ጊዜ ባለቤቱ በሦስት ወር ውስጥ የሚከፈለውን ካልከፈለ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በሐራጅ የመሸጥ መብት የሚያጐናፅፈውን የ67 ሕግ ስንቃኝ ለመሻሩ እርግጠኞች እንሆናለን።

በዚህ በኑሮ ውድነት ከጥራጥሬ እስከ ፍራፍሬ፣ ከቤት እቃ እስከ ቢሮ እቃ፣ ከመለዋወጫ እስከ ነዳጅ የሁሉም ነገሮች ዋጋ በእጥፍና በሦስት እጥፍ ጨምሮ እቺ 50 ብር ግን ለ35 ዓመታት ንቅንቅ አለማለቷ ምክንያቱ ምን ይሆን? ምክንያቱ እንድና አንድ ነው - የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት እንኳንስ ዋጋ የሚጨምርበት ቀርቶ 50 ብሯን የሚያስከፍልበት የሕግ መሠረት አልነበረውም።

ሆነም ቀረ አሁን በሚሰራው የ1987 አዋጅ መሠረት ድርጅቱ ፈቃድ የመስጠትም ሆነ 50 ብር የመቀበል ሥልጣን አልተሰጠውም፤ የ1967 ሕጐችም ተፈፃሚነት አግባብ የሌለው ነው። ታዲያ በየዓመቱ የሚከፈለው ወይም እንዲከፈል የሚጠበቀው 50 ብር ግብር ካልሆነ፣ የአገልግሎት ካልሆነ፣ አልያም የፈቃድ እድሳት ካልሆነ የምንድነው? እኛ «መልስ የለውም» ብለነዋል። ከመግቢያችን ላይ እንደገለፅነው 50 ብር በዝቶ ወይም

አንሶ አይደለም፤ የሕግ አግባብ ፈልገን አጣንለት እንጂ፡፡ ጉዳዩን እኛ በዚህ መልኩ ተመልክተነዋል፤ ይህ ድምዳሜም የእኛና የእኛ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ነገሩን አጢነውት ምላሽ ቢሰጡበት ምኞታችን ሲሆን ህዝቡ ለሚከፍለው ገንዘብ ምክንያቱ ሊነገረው ይገባል ስንል እንደመድማለን፡፡

## መጣጥፎች

# «በደህናው ጊዜ ያበደ ፀደቀ»

**«አንዳንድ የሕብረተሰብ ክፍሎች» የተናገሩት ንግግር**

**በአቤ ቶኪቻው**
abeto2007@yahoo.com

እጅግ የምናደንቀው፣ እጅግ የሚኮረኩረን እና እጅግ የሚያስቀን ተስፋዬ ካሳ በአንድ ወቅት ያጫወተን ጨዋታ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ሴትየዋ ለበዓል በግ መግዛት ፈልገው ገበያ ይወጣሉ (በቅንፍ ከተስፋዬ ጨዋታ ወደ እኔ ማብራሪያ እንሂድ ለበዓል እንጂ ለባል አይደለም በግን ያኽል ነገር እንደዋዛ ለባል ለውሽማ ተብሎ መገዛት ከቀረ ከርሟል፡፡ ነብሱን ይማርና ተስፋዬ ካሳ እንኳ ከተለየን ስንት ጊዜው?!) እናም በበዓል በግ መግዛት ፈልገው «ባለ በግ ይሔ ስንት ነው?» ብለው ይጠይቃሉ፡፡ አይናቸው ያረፈበትን በግ ሽንጥ እየደባበሱ፡፡ (በጣም ማጋነን ብንፈልግ የበግ ሽንጥ ድሮ ቀረ የዛሬ ግዜ በግ ገበያ ሲወጣ ሽንጡን ቤቱ አስቀምጦ ነው፡፡ ስለዚህ ሽንጥ እየዳበሱ ይሔ ስንት ነው ማለት ከቀረ ስንተ ጊዜው ... ማለት እንችላለን ግን ማጋነን ምን ያደርጋ?!) እና ይህንን ማለቱን ትተን ሴትየዋ የበጉን ሽንጥ እየደባበሱ ዋጋውን ጠየቁ ብለን እንቀጥላለን፡፡ ነጋዴው «አምስት መቶ ብር» አላቸው (አሁን እንኳ ምንም ማጋነን ሳያስፈልገን ስለ አምስት መቶ ብር የቅንፍ ወሬያችንን እናቀልጠዋለን፡፡ (አምስት መቶ ብር ድሮ ብዙ ቀዳዳዎችን ይደፍን ነበር፡፡ ዛሬ ግን አምስት መቶ ብር እንኳንስ ቀዳዳ ሊደፍን ይቅርና ራሱ ቀዳዳ የሆነ ይመስል በሌላ አምስት መቶ ብር ካልተደፈነ አይሰራም ብንል ያስማማናል፡፡) ወደ ተስፋዬ ጨዋታ ስንመለስ የኔ አምስት መቶ ብር የተከበረ ከመሆኑ የተነሳ እንደዋዛ ለአንድ ሽንጣም በግ አምጡ ሲባል ያስደነግጣል፡፡ ስለዚህ ሴትየዋ የበጉ ዋጋ አምስት መቶ ብር ሲባሉ ደነገጡ፡፡

«እኮ አምስት መቶ ብር ለአንድ በግ?!» ብለው ነጋዴውን መልሰው ጠየቁት፡፡ ነጋዴው ኮስተር ብሎ «አዎን!» አላቸው፡፡ «አልበዛም?» አሉ ገገርዋ ተስፋ በቆረጠ ድምጽ፡፡ ይሔን ጊዜ ነጋዴው ዝም አላቸው፤ በምትኩ ግን አንድ የአዕምሮ ህመምተኛ ሰው «እማማ አምስት መቶ ብር ምን አላት ግዙት!» አላቸው (ይህንን ተስፋዬ ሲለው እንዴት ያምራል መሰላችሁ?! የሴትየዋን መልስማ ሲያሰማን በሳቅ ያፈርሳል፡፡) «አንተ

ምን አለብህ በደህናው ጊዜ አብደሃል!» አሉት ይለናል ተስፋዬ ካሳ። (እርሱም በደህናው ጊዜ አርፏልና ነብስ ይማርልን)

ዛሬ ተስፋዬ አልፏል የበግ ዋጋ መጠየቅም አልችል። እንኳንስ የበግ ቀርቶ የመሰረታዊው ምግብ ጤፍ ዋጋ መክፈሉ ሳይሆን መጠየቁ ብቻ ለራስ ምታት መንስኤ እየሆነ መምጣቱን የገበያ ሳይንስ ምሁራን ደርሰውበታል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሰሞኑን ከወዳጆቼ ጋር አንድ ሁለት እያልን ስንጨዋወት (አንድ ሁለት ያልነው ጨዋታውን ነው እንጂ እነ ቢራን መስሏችሁ እንዳትሳሳቱ እሱን እሱን ትተናል) እና ስንጨዋወት አንዱ «ድሮ የጉጃም ነጭ ጤፍ የጌቶች ምሳ ይባል ነበር አሁን ግን እንኳን ማኛ ማንኛውም ጤፍ የጌቶች ምሳ ሆኗል» ሲል ተናገረ። እኔ እና ሌሎች ስለ ሀገራችን መልካም ገጽታ የምንጨነቅ ሰዎች ዝም አልን፤ ሌሎቹ ሳቁ። ሌላው ወዳጃችን «እዚህ ላይ ማስተካከያ አለኝ» አለ። እሺ አልነው። (ምናልባት ደግ ቢናገር ብለን።)

«ወዳጃችን ማንኛውም ጤፍ የጌቶች ምሳ ሆነ ይላል፤ እኔ ግን እላለሁኝ ማንኛ ውም ምሳ ራሱ የጌቶች እንጂ የእኛ አይደለም።» አለ። አሁንም ሌሎች ሲያውካኩ እኛ «መቻቻል» በሚለው ስትራቴጂ ችለን ዝም አልናቸው።

ቆይ ቆይ ወዳጄ ነገራችን ያዝ ለቀቅ እንዳይሆንብን ከተስፋዬ ቀልድ ጋር የጀመርነውን እንጨርስ እና ወደሌሎች ጨዋታዎች እናሳልጣለን።

አንድንድ የህብረተሰብ ክፍሎች እንደሚሉት ከሆነ (ወዳጄ አጀማመሬን አልወደዱትም? ስም ሳይጠቅሱ አንዳንድ የሕብረተሰብ ክፍሎች እያልን ሃሳባችንን ካልገለጽን እኮ ታፍነን መሞታችን ነው። ዘንድሮ እንደሆነ ስጋ ሲጠፋ ስጋት በብዛት ሆኗል። ይህንንም አንዳንዶች እንዳሉት ይቆጠርልኝ) እናም አንዳንድ የሕብረተሰብ ክፍሎች እንደሚሉት ከሆነ ዛሬ እንደተስፋዬ ካሳ በኑሮ ላይ የሚቀልዱ ኮሜዲያን የሉንም እናም ኑሮ ራሱ ኮሜዲያን ሆኖብናል። ያስቀናል ያሳስቀናል  ያሳቅቀናል .... (ዛሬ ቅንፍ አበዛሁብዎ ወዳጄ ይቅርታ የመጨረሻዋን «ያሳቅቀናል!» የምትለዋን እንደ ታይፕ ግድፈት ይቁጠሩልኝ) እና ኑሮ ያስቀናል ያሳስቀናል... የምትለውን ብቻ በልብዎ ይያዙልኝ ዳሩ እየተናገሩ ያሉት አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች በመሆናቸው ማንም ተጠያቂ የለም። የሆነ ሆኖ በኮሜዲያን እጥረት እና በኑሮ ውድነት መሳቅ እና መሳቀቅ ተምታቶብን አለን (ይላሉ።) አንዳንድ የሕብረተሰብ ክፍሎች። በነገራችን ላይ አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍል መሆን መታደል ነው። እንዳሻዎ ለመናገር ባሻዎ ቦታ እና ጊዜ የመሰልዎትን አስተያየት ለመስጠት የአንዳንድ ህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት ተጠቃሚ ይሆኑ! (ከማስታወቂያው ስንመለስ) በተስፋዬ ካሳ ቀልዱ ላይ የምናገኘው አዕምሮ ህመምተኛ በዛን ጊዜ በግ አምስት መቶ ብር ሲገባ አልተደነቀም። አልተሳቀቀም። አልተደናገጠም። ለምን? በደህናው ጊዜ አብዷል እና «አምስት መቶ ብር ምን አላት?» አለ። ዛሬ በየ ጊዜው የምናያቸው የዋጋ ጭማሪዎች ያስደንቃሉ! ያሳቅቃሉ! ያስደነግጣሉ! በዚህ ዋጋ ጭማሪ የማይደነግጥ ካለ እርሱ በደህናው ጊዜ ያበደ ነው እና ፀድቋል።- በማለት አንዳንድ የሕብረተሰብ ክፍሎች እየተናገሩ ነው።

ይህ አይነቱ ንግግር የሀገሪቱን መልካም ገጽታ ጥላሸት ለመቀባት ሆን ተብሎ በክፉ ልቦና በመነሳሳት የተሸረበ የተገመደ የተጐነጐነ የተጠለፈ የተሴረ ሴራ ነው:: እንጂ አሰቃቂም ሆነ አስደናቂ የዋጋ ጭማሪ የለም:: እርግጥ ነው የነዳጅ ዋጋ እና የትራንስፖርት ዋጋ እና የአንዳንድ ሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ በዓለም ነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ምክንያት በየ አስራ አምስት ቀኑ ጭማሪ እያሳየ ነው:: ቢሆንም ያን ያህል አይደለም:: ምንም እንኳ አንዳንዶቹ የዓለም ነዳጅ ዋጋ በበርሜል መቶ አርባ ዶላር የነበረ ጊዜ ያልታየው የነዳጅ ዋጋ ዛሬ በሰማኒያ ዶላር ጊዜ ከየት መጣ? እያሉ ቢጠይቁም መልሱ «መ» ነው (መልሱ የለም) ብለን መልሰን ከመንግስት ራይት አግኝተንበታል:: ስለዚህ እባካችሁ እናንተ አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች ስለ ኑሮ ውድነት፣ ስለ ዋጋ ጭማሪ እያወራችሁ መልካም ገጽታችንን አታበላሹ:: (የቱን መልካም ገጽታ?! ብሎ ያሽሟጠጠ ወይም ለማሽሟጠጥ ያሰበ በአዲሱ አዋጅ ወዬውለት ያስብላል!) በነገራችን ላይ በርካታ አዲስ አዋጆች በበርካታ ጉዳዮች ላይ በተለይ ባለፈው ጉደሎ አመት ሁለት ሺህ አንድ (አመቱን ጉደሎ ያልኩት ቁጥሩን እንጂ የአዋጆቹ መውጣት ላይ ቅሬታ ተፈጥሮብኝ እንዳይመስልና ከደህናዎቹ ሰዎች እንዳልቀያየም ደህናዎቹን ሰዎች አደራ እላለሁኝ) እናም በጉደሎው ዓመት በርካታ አዳዲስ አዋጆች ታውጀዋል:: ታዲያ ሳናውቅ እንዳንጥሳቸው ይረዳን ዘንድ በህግ ላይ የምትጽፉ እና የምታስተምሩ ወዳጆቼ እባካችሁ ግንዛቤ አስጨብጡን:: ኋላ «እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው» ተብለን ከምንጨበጥ ከወዲሁ ግንዛቤ ጨብጠን ጠንቀቅ ብንል ጥሩ ነው:: ለምሳሌ ያለፈው ሳምንት አውራምባ ታይምስ «በአዲሱ ሕግ ውሸት 10 ዓመት አመት ዛቻ እስከ ሞት ሊያስቀጣ እንደሚችል ያውቃሉን?» በሚል የህግ የበላይነት አምድ ላይ የወጣችውን ግንዛቤ ማስጨበጫ ወድጃታለሁኝ:: ከዛ በኋላ ይኸው ውሸት የለ! ዛቻ የለ! እውነት እውነቷን እያወሩ ብቻ አንገት ደፍቶ መኖር::

(ውሸትና ዛቻስ ለማን ይጠቅማል?!) እኔ የምለው ወዳጄ ሰሞኑን «የከተሞች ቀን» እየተከበረ እንደሆነ ሰምተዋል? (መቼም እንደ አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች «እዚህ ሀገር በተለያዩ ነገሮች ቀኑን እያከበርን እኛ ደግሞ በተለያዩ ችግሮች እየተቀበርን መኖር ብርቃችን ነው እንዴ?» ብለው እንደማያሽሟጥጡኝ ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ::) የሆነ ሆኖ የሀገራችን ከተሞች ቀን እየተከበረ ነው:: በኤግዚቢሽን ማዕከል በተለያዩ የሀገራችን አቅጣጫዎች ያሉ ከተሞች ድንኳናቸውን ደኩነው አንዱ ከተማ ለአንድ መልካም ገጽታውን እያስተዋወቀ ይገኛል:: አንዳንድ ግለሰቦች «መልካም ገጽታማ መልካም ነው ተረዳድተን እንድናድግ የቸገራቸውን ጉዳይ ቢያዋዩን የተሻለ ነበር እንጂ?» ሲሉ ተሰምቷል:: ነገር ግን እኛ ባየነው ኤግዚቢሽን ከተሞቻችን ችግር የሚባል ነገር የማያውቁ አይመስሉም:: ከባለ ሃምሳ አመቷ ከተማ እስከ ሶስት ሺህ አመቷ ከተማ ድረስ በተለይ ከሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ሶስት አመተ ምህረት በኋላ ጥጋብ በጥጋብ፣ ልማት በልማት፣ ህንፃ በህንፃ፣ ፕላን በፕላን፣ መንገድ በመንገድ፣ ቀለበት በቀለበት ማሳለጫ በማሳለጫ ወዘተ በወዘተ መሆናቸውን አይተናል:: እሰይ እንኳንም እዚሁ ድረስ በመንግስት ወጪ  መጥተው የከተሞቻችንን ደህንነት አይን እንዲህ የሚያደርግ

መንግስት እግር እስኪነቃ ቢሄድ የት ይገኛል! እያልን ለወዳጆቻችን ስንመሰክርላቸው ወዳጆቻችን አንዴ «ጽንፈኛ ሆናችሁ ኑሩ!» ተብለዋልና፡፡

«እውነታችሁን ነው ከተሞቻችን እንዲህ በመንግስታችን ወጪ እየመጡ ካልጐበኙናቸው እኛ ወደ እነርሱ እንሂድ ብንል እንኳንስ እነጐንደር እና አክሱም ድረስ ይቅርና እዚች ቅርባችን ደብረ ዘይት ቢሾፍቱ ለመድረስ የትራንስፖርቱን ዋጋ በግለሰብ ደረጃ የሚቻል አልሆነም» ሲሉ አለ ቅጥ አማረዋል፡፡

እኔ የምለው እውነት ግን አዲሱን አስራ አምስት ቀናዊ የታክሲ ዋጋ እንዴት አዩት? አንዳንዶች ዛሬ ለታክሲ የምንከፍለው ዋጋ ድሮ ከመቶ ሺህ በላይ የሚባሉ ነጋዴዎች ለታክስ ከሚከፍሉት ጋር ይስተካከላል፡፡ እያሉ ነው፡፡ እኔ በበኩሌ የእነርሱን ያህል ባላማርርም የመጀመርያ ጊዜ ለመካከለኛ ጉዞ ከሁለት ብር በላይ ሳንቲም ሲመልስልኝ «ምነው አልበዛም እንዴ?!» ብያለሁኝ፡፡ ይቅር ባዮች ይቅር በሉኝ፡፡ ህግ አዋቂ ወዳጆቼ በአዲሱ አዋጅ «ምነው አልበዛም እንዴ?!» ማለት ምን ያህል ዓመት ያሳስራል?! ወደ ዛቻ ይጠጋ ይሆን?

ወዳጄ ለመሆኑ ይሔንን ሁሉ ቀደዳ ስቀድ ይሔንን ሁሉ ቶክ ስቶከቱክ ሰላም ብዬዎታለሁኝ? አሁን ሰላም ለእርሶ ይሁን ልበልዎታ! ከመጨረሻችን በኂላ ደግሞ አማን ያሰንብተን እንባባላለን፡፡

በመጨረሻም

ኢቲቪ

ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥ ኢቲቪ «ሃገር ጫታ ሆነ» በሚል አንድ ፕሮግራም ሲያቀርብልን ነበር፡፡ በሙሉም ባይሆን ያደረሰኝን ያህል ተከታትያለሁኝ፡፡

እስከ ዛሬ በቲቪ አባት አርበኛ እንጂ አርበኛ ግንባር የሚባል መኖሩን ሰምቼ አላውቅም ነበር፡፡ (ለነገሩ ስንት የልማት ወሬ እያለ የግንባር ወሬ ምን በወጣን እንሰማለን) ሰሞኑን ግን በተከታታይ ክፍል የግንባር ወሬ ሰማን (ለነገሩ ግንባሩን ግንባር እያሉ ከመጥራት «ሽፍታ» የሚለው አጠራር የበለጠ እንደሚገልፀው የኢቲቪ አንዳንድ የአካባቢው ሕብረተሰቦች ገልፀዋል፡፡) እንደው ይሔ ይሔ ለመንደርደሪያ ነው እንጂ ዋናው ጉዳዬ እንኳን ወዲህ ነው፡፡ ኢቲቪ ዘገባውን ሲያቀርብ በአንዱ ክፍል «የጥፋት መላክተኛ የሆነው አርበኛ ግንባር የሻዕቢያን የመበታተን ስትራቴጂ ለማስፈፀም በአርማጭሆ በኩል፣ በመተማ በኩል... ሌሎችም እኔ በረሳኂቸው ቦታዎች በኩል ገባ፡፡ ታድያ ይህ አርበኛ ግንባር ይሳካለት ይሆን? በሚቀጥለው ክፍል...» ብሎ አበቃ፡፡ የኔ ቁም ነገር እዚህ ላይ ነው፡፡ የኢቲቪ ጋዜጠኛ «አርበኛ ግንባር ይሳካለት ይሆን?» ሲል ጠይቆናል ልማት ወዳዱ ህዝባችን የት ሄዶ ነው፡፡ የማንም ሽፍታ የጥፋት መልዕክት ስኬታማ የሚሆነው? በእውነት ጋዜጠኛው ንግግሩ በጣም አብሽቆኛል፡፡ ምን ለማለት ተፈልጐ ነው «አርበኛ ግንባር ይሳካለት ይሆን?» የሚባለው ይሔ ለልማት ቆርጦ የተነሳው ሕብረተሰብ ላይ ከማሾፍ አይተናነስም እና የኢቲቪው ጋዜጠኛ ጠንቀቅ ቢሉ ጥሩ ነው፡፡ እኔ ግን ቀጣዩን ክፍል ሳላይ መልሱን ለበርካቶች መልሻለሁኝ፡፡ «ለመሆኑ

አርበኛ ግንባር ይሳካለት ይሆን?» ኢቲቪዎች አትልፉ አይሳካም! (እንዴት ማሟረት ተጀምሯል ጃል?!) እንዲህ አይነቱን ከመስማት በደህናው ጊዜ ማበድ ሳይሻል ይቀራል!?

ወዳጄ እልቅ እንሰነባበት
አማን ያሰንብተን !

# በ2002 ምርጫ ዴሞክራሲን በኢትዮጵያ ማዳን ይቻላልን?

**በአለማየሁ ገ/ማርያም (ፕ/ር)**

በአፍጋኒስታን ምርጫዎች ፉክክርና ዴሞክራሲን በማስፈን አስፈላጊነት ላይ የአሜሪካ ትኩረት ባነጣጠረበት ወቅት፣ በሌላ የዓለም ክፍል አደገኛ ውጤቶች ያስከተሉ የዴሞክራሲ እገታዎች በምርጫ ሳጥኖች ስም እየተፈጸሙ ነው:: የአፍሪካ ምርጫዎች ወደ ቀልድነት ተለውጠዋል:: ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ፣ በኬንያ፣ በናይጄሪያና በዝምባቡዌ በዴሞክራሲ ላይ የተሰነዘሩ ጥቃቶችን ተመልክተናል::

በ1997 ዓ.ም በኢትዮጵያ በተካሄደው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫዎች፣ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሚመሩት የፖለቲካ ድርጅት - የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር - ኢሕአዴግ፣ በተቃዋሚው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ (ቅንጅት) ሽንፈት ደርሶበት ነበር:: አቶ መለስ እነዚያን ምርጫዎች አስገድደው ውጤቶችን ቀለበሱ፤ ከዚያም (ድልና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በአንድ ጊዜ በማወጅ) ተቃዋሚዎችን አጠቁ:: በተከታዮቹ ወራት፣ የጸጥታ ኃይሎቻቸው 200 የሚደርሱ ሰልፈኞችን ገደሉ፤ ከ30 ሺህ የሚበልጡ ዜጎች ደግሞ ወደ ወህኒ ወረዱ::

በኬንያ እ.ኤ.አ በ2007፣ ተቃዋሚው «ኦሬንጅ ዴሞክራቲክ ሙቭመንት» የፖለቲካውን መልከዓ-ምድር አጥለቀለቀው፤ ሥልጣን ላይ የነበረውን የፕሬዝዳንት ሙዋይ ኪባኪን ካቢኔና እንዲሁም ምክትል ፕሬዝዳንታቸውን፣ የውጭና የመከላከያ ሚኒስትሮቻቸውን ጨምሮ፣ ጥገኛ ከበርቴ የፓርላማ አባላትን ከወንበሮቻቸው አስወገዷቸው:: ነገር ግን ኪባኪ ሥልጣን የሙጥኝ በማለታቸው 1500 ሰዎች የተገደሉበትና ከ250 ሺህ የሚልቁ የተሰደዱበት አመጽ ተከተለ::

እ.ኤ.አ በ2008 ዘጠኝ ወራት የፈጀ ሕጋዊ ንትርክ ከተካሄደ በኃላ፣ መጠነ-ሰፊ ማወናበድና ማጭበርበር እንደተፈጸመ ማረጋገጫ እያለ፣ የናይጄሪያ ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ሽንኀ፣ ኡማር ያራዱዋ ያወጁትን ድል አጽድቆ ነበር:: በተመሳሳይ ዓመት የሮበርት ሙጋቤ «ዛኑ-ፒ.ኤፍ.» በዚምባቡዌ በተካሄደ ብሔራዊ ምርጫ ከፍተኛ ሽንፈት ደርሶባቸው ነበር:: የተቀናቃኞቻቸው ሞርጋን ቻንጋራይን ደጋፊዎች ከተነኮሷቸው በኋላ፣

84ኛ ዕድሜያቸውን የያዙት ሙጋቤ፣ በኃይል፣ ለሁለተኛ ጊዜ የተካሄደውን ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ለብቻቸው ተወዳድረው «አሸነፉ»፡፡

በእነዚህ ሂደቶች ውስጥ ከምዕራብያውያን የተሰነዘሩ ማስጠንቀቂያዎች ውጤት የነበራቸው አልነበሩም፡፡ ለምሳሌ፣ አቶ መለስ በተቃዋሚዎች ላይ ለወሰዱት የጥቃት ምላሽ፣ የአውሮፓ ህብረት ለአገዛዙ የሚሰጠውን ዕርዳታ ለጥቂት ጊዜ ከመለገስ ሲቆጠብ፣ የአገራት ጥምረት ተቋማት ደግሞ የብድር አገልግሎት ከመስጠት ተገትተው ነበር፡፡ የዩ.ኤስ. አሜሪካ የተወካዮች ምክር ቤት («The U.S. House of Representatives») የአቶ መለስን አገዛዝ ተጠያቂ ለማድረግ ሕግ («ኤች. አር. 2003») ቢያሳልፍም፣ በሴኔቱ ባለመጽደቁ ከሽፏል፡፡ እንዲሁም በኬንያና በዝምባቡዌ፣ ኪባኪና ሙጋቤ የጥምር መንግስት እንዲመሰርቱ ምዕራቡ ግፊት ቢያደርጉም፣ አገራቱ ከመቼውም ጊዜያት የበለጠ የተከፋፈሉ እንደሆኑ አሉ፡፡

ስፔይናዊው ፈላስፋ ጆርጅ ሳንታናያ በሆነ ወቅት፣ «ያለፈውን ማስታወስ የማይቻላቸው ያንኑ ደግመው መፈጸማቸው የማይቀር ነው፡፡» ብሎ ነበር፡፡ አፍሪካ ማሻሻያዎችን ለመተግበር ያዳገታት በመሆኑ ምክንያት፣ በኢትዮጵያ በግንቦት 2002 የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ ይካሄዳል ተብሎ እንደመጠበቁ፣ ያን የድግግሞሽ (ዑደት) ለመጀመር ተዘጋጅተናል፡፡

በዚህ ወቅት አቶ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን ዴሞክራሲ ለመቀልበስ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የቆረጡ ነው የሚመስሉት፡፡ በሚያዝያ በአገሪቱ በተካሄደው የአካባቢና ሚሚያ ምርጫ፣ «ለፉክክር» ከቀረቡ 3.6 መቀመጫዎች ውስጥ፣ ተቃዋሚዎች ትርጉም የሌላቸው ሶስት መቀመጫዎችን ብቻ ማሸናፋቸውን አሳውቆ ነበር፡፡

አሁን ሁለት ዓስርት ዓመታት በሆነው በአቶ መለስ አገዛዝ ስር በኢትዮጵያ የሚካሄዱ ምርጫዎች፣ ሁለት ተደጋጋሚ አካሄዶችን እንዳሏቸው የታየ ነው፡፡ የመጀመሪያው፣ አቶ መለስ ተቃዋሚዎችን ለማስወገድ ሳይሞክሩት የተውት አንዳች ነገር አለመኖሩ ነው፡፡ ተቃዋሚዎቻቸውን ለመጠራረግ፣ ትንኮሳዎችን፣ ዛቻዎችን፣ ከፍተኛ ኃይል፣ ማጭበርበርና ማታለሎችን ተጠቅመዋል፡፡ በቅርቡ አቶ መለስ ተቃዋሚዎችን ለ2002 ምርጫ ድርድር ጋብዘዋቸው ነበር፤ ነገር ግን ወዲያው፣ ድርድር ከመካሄዱ አስቀድሞ «የሥነ-ምግባር ደንብ» መፈረም ያለባቸው መሆኑን አሳምረው አስገነዘቡ፡፡ «መድረክ» በሚል መጠሪያ የተሳባሰቡ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጥምረት መሪዎች፣ ወጥመዱን በግልጽ በመረዳታቸው፣ ድርድሩን ረግጠው ወጡ፡፡ ከዚህ በኋላ አቶ መለስ የመድረኩ አባል ከሆኑት ፓርቲዎች ውስጥ ወደ አምስት መቶ የሚደርሱ አባላትን እንዲታሰሩ በማድረግ የትንኮሳና የዛቻ ዘመቻ በማስነሳት መድረክን ተበቀሉ፡፡

ተቃዋሚዎች ከግለሰብ ጸባዮች/ ባህሪዎችና ግላዊ ቅዋሜዎች ይልቅ ለድርድሩ የሚቀርቡ ጉዳዮች መረጣ ወይም በአገዛዙ ላይ ሕዝበ-ውሳኔ ለማካሄድ እንዳይቻላቸው አድርገው ለማስተጓጎል አቶ መለስ ተሳክቶላቸዋል፡፡ በአገዛዙ ወይም በተቃዋሚ፣ አገሪቱ

እየተጋፈጠቻቸው ስላሉ እጅግ አስፈሪና አደገኛ ጉዳዮች ያለው ውይይት በጣም አነስተኛ ነው።

በምግብ እጥረት አንድ አምስተኛውን የኢትዮጵያን ሕዝብ አደጋ ተጋርጦበታል። በሚታወቁና በምስጢራዊ እስር ቤቶች ካለፍርድ ሂደት በሺህዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች ተይዘው ይገኛሉ። ጅምላ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የፈጸሙ በጠራራ ጸሐይ በነጻነት ይመላለሳሉ። የብዙሀ-ሕይወት ውድመት - የደን ጭፍጨፋን፣ የመሬት መሸርሸርን፣ የግጦሽ መሬት መራቆትን፣ የሕዝብ ብዛት መጨመርን እና ወንዞቿና ሐይቆቿ በኬሚካል መበከልን ጨምሮ - ጭራሽ ሰዎች በሕይወት መቆየታቸው ሁኔታ አደጋ ላይ የወደቀበት ሁኔታ ነው የምንመለከተው። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጋለበ ያለው የዋጋ ግሽበት የአብዛኞቹን ኢትዮጵያውያን ሕይወት አዳጋች አድርጎታል። የተንሰራፋ ሙስና የሕዝብ ተቀማጭ ገንዘብ ዘረፋ፣ አገሪቱ ያላት የውጭ ምንዛሬ ክምችት ለጥቂት ሳምንታት ብቻ የሚበቃት ሆኗል። እንዲሁም ጥንቃቄ በጎደለው የሶማሊያ የእርስ በእርስ ጦርነት በተደረገው ጣልቃ ገብነት የአገር ኃብት ባክኗል የወጣቶች ሕይወት ጠፍቷል ለዚህ ተጠያቂ የሆነ ማንም የለም።

በ2002 ምርጫ፣ ዴሞክራሲን በኢትዮጵያ ማዳን ይቻላልን? ብዙዎቻችን ማዳን እንደሚቻል እናስብ ይሆናል፤ ሆኖም ግን ያን ማድረግ የሚቻለን ተቃዋሚዎች በቅድመ 97 ምርጫ ወደ ነበሩበት ስፍራቸው መመለስ ሲችሉ ብቻ ነው። በዚያን ወቅት ጠንካራ ፉክክር እንዲያደርጉ የተፈቀደላቸው እውነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ነበሩ። በመላ ማሕበረሰቡ ውስጥ የተካሄዱ ነፃና ክፍት ክርክሮች ነበሩ። ነፃ የግል ፕሬስ በስልጣን ላይ የነበሩትን ተጋፍጧል፣ እንዲሁም ተቃዋሚውን አብጠርጥሯቸዋል። የሲቪል ማሕበራት መሪዎች ለመራጮችና ለሕዝብ መረጃ ለመስጠትና ለማስተማር ሳይታክቱ ስለዴሞክራሲና ምርጫዎች ሌተቀን ሰርተዋል። መራጮች በአገዛዙ አለመደሰታቸውን በግልፅና ካለፍራቻ በሕዝብ ስብሰባዎች አሳይተዋል። በግንቦት 7 1997 መራጮች በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ አንድ ነገር አደረጉ፡- ውሳኔያቸውን ለመስጠትም የምርጫ ሳጥኖችን ተጠቀሙ። አዎ! በ2002 ምርጫ፣ የኢትዮጵያን ዴሞክራሲ ማዳን ካለብን ማዳን የምንችለው በእንደዚህ አይነት መልኩ ብቻ ነው።

ኢትዮጵያውን ወደ ፊት እንዳይጓዙ እድላቸውን የዘረፋው ዓይነት አምባገነንነት ማክሰም የሚቻለው ወደ ሕገ መንግስታዊ የዴሞክራሲ ሽግግር ከተደረገ ብቻ ነው። የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ፣ «አፍሪካ የሚያስፈልጓት ፈርጣማ ተቋማት እንጂ ፈርጣማ ሰዎች አይደሉም።» እንዳሉት ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ በፈረሶች ላይ በተፈናጠጡ፣ በታንክ ውስጥ በመሸጉ እና በቦርድ የመሰብሰቢያ አዳራሾች የበላይ በሆኑ ፈርጣማ ሰዎች የተሞላ ነው። በዚህም ምክንያት፣ ኢትዮጵያ ደካማ የሕግ አውጭ፣ የዳኝነት አካል እና የምርጫ ተቋማት ነው ያሏት።

ኢትዮጵያንና ሌሎች የአፍሪካ አገራትን ከፈርጣማ ሰዎች መታደግ እንዴት ይቻላል ለሚለው በጅምር ላይ ከሚገኘው የጋና ዴሞክራሲ ፍንጭ ሊገኝ ይችላል። የጋና

ወታደራዊ አምባገነንነት አዲስ ሕገ መንግስት በ1992 ጸድቆ ከተቋጨበት ጊዜ አንስቶ፣ ጋናውያን በአፍሪካ ውስጥ ስኬታማ የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲን ለመተግበር የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታዎችን አሳይተዋል:: የሕግ የበላይነትን ተቋማዊ ተቋማዊ በማድረግ ሕጎቻቸው ከዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች መመዘኛዎች ጋር እንዲጣጣሙ አድርገዋል:: የጠቅላይ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መተላለፍ «ከፍተኛ ወንጀል» ካደረጉ ላዕላይ ሕገ መንግስታዊ ሥልጣኖች ያሉት ጠንካራ የዳኝነት/ ፍትህ አካል ፈጥረዋል:: ጋናውያን የመንግስት በቀልን ሳይፈሩ ራሳቸውን እንዲገልጹ የሚያስችሏቸው ጠንካራ የሲቪል ነፃነቶች ጥበቃዎችን አካተዋል::

የመራጮች ምዝገባ የማካሄድ፣ የምርጫ ቀጠናዎችን የመወሰን፣ ሁሉንም ሕዝባዊ ምርጫዎች የማስተባበርና የመቆጣጠር፣ ሕዝበ ውሳኔዎችን የማቀናጀትና መራጮችን የማስተማር ኃላፊነት ግዴታ የተጣለበት ገለልተኛ የምርጫ ኮሚሽን አቋቁመዋል:: ከሁሉም በላይ በአፍሪካ ለተከሰቱ አብዛኞቹ ግጭቶች የስር መነሻ የሆኑትን በጎሳ ወይም በብሔር መሰረትነት የፖለቲካ ፓርቲዎችን ማቋቋም ሕገ-ወጥ መሆኑን የጋና ሕገ መንግስት በማያወላዳ ቋንቋ የደነገገው ነው::

በጋንያውያን ተሞክሮ የታየው የተስፋ ጭላንጭል ነጸብራቅ፣ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያና በሌሎች የአፍሪካ አገራት ካለደም መፋሰስ በስኬታማነት መተግበር መቻሉን የሚያረጋግጥ ነው:: ዳግም እንደዚያ ማድረግ አለመቻል፣ የቪክቶር ሁጎን ምክር በጥሞና እንድናዳምጥ ያስገድደናል፤ «አምባገነንነት ተጨባጭ በሚሆንበት ወቅት፣ አብዮት የማይቀር ይሆናል::» በመጭው ምርጫ መሆን ያለበት ነገር ካልሆነ በኢትዮጵያም ይህ የማይቀር ነው::

*/አለማየሁ ገብረማሪያም፣ በካሊፎርኒያ ስቴት ዩኒቨርስቲ ሳንበርናንዲኖ የፖለቲካል ሳይንስ ፕሮፌሰርና ሎስ አንጀለስ ውስጥ በግል የህግ ኮንሰልታንት ናቸው/*

# ከሚድህ ዴሞክራሲ ለመውጣት ስንት አመት ይበቃናል?

**በውብሸት ታዬ**

***«..... የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ሆኜ በመሰየሜ ኩራት ይሰማኛል::... መጀመሪያ ላይ ትንሽ አሳስቦኝ ነበር:: ይህ ነገር ግዙፍ አገራዊ፣ ሕዝባዊ ኃላፊነት ነው:: አይከብድም ወይ? እወጣዋለሁ ወይ? ብዬ ነበር:: ነገር ግን ጥሪው ሲደርሰኝ መቀበል አለብኝ ብዬ ወሰንኩ:: ከዚያ እወጣዋለሁ ብዬ በስሜት ገባሁበት:: ... እስካሁን ውጤታማ ነኝ:: ባለፈው የአካባቢና የማሟያ ምርጫም (የሚያዝያ 2000 ዓ.ም) ውጤታማ ነኝ:: »***

በመግቢያችን ላይ ያለውን ትኩረት የሚስብ ንግግር የተናገሩት የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ የሆኑት ፕ/ር መርጋ በቃና «የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው በመሰየምዎ ምን ይሰማዎታል? ይህንን ከባድ ኃላፊነት እወጣዋለሁ ብለውስ ያስባሉ?» በሚል ከዘመን መጽሔት ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ነበር፡፡ አንድ ነፃ፣ ገለልተኛና ጠንካራ ምርጫ ቦርድ ለአንድ አገር በህዝብ የተመረጠ ዴሞክራሲያዊ መንግስት መመስረት፣ በአገሪቱ መፃኢ እድል ውስጥ ኢኮኖሚያዊ እመርታ፣ ፖለቲካዊ መቻቻልና ማሕበራዊ መረጋጋር እንዲሰፍን በማስቻል ረገድ አይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ አሁን በሥራ ላይ ያለው ምርጫ ቦርድ የተሰየመው የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሰኔ 19 ቀን 1999 ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ አማካይነት ሲሆን ምርጫውን አስመክቶ ያለው ተሞክሮም ሰብሳቢው በመግቢያችን ላይ የገለፁት / ውጤታማ ሆነኜበታለሁ ያሉት የአካባቢና የማሟያ ምርጫ ነው፡፡-ቦርዱ ባለፈው ቅዳሜ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ባደረገው ስብሰባ የምርጫ አፈጻጸም ረቂቅ የጊዜ ሰሌዳውን ይፋ አድርጓል፡፡

## የተአማኒነት አጣብቂኝ

ፕ/ር መርጋ በቃና «እስካሁን ደረስ ውጤታማ ነኝ» ካሉ በኋላ በእማኝነት የአካባቢና የማሟያ ምርጫ ስኬታቸውን ቢያቀርቡም በተቃዋሚዎች ዘንድ የሚያዝያው ምርጫ የምርጫ ክንውን ሚዛናዊነት ዋነኛ ግብአቶች ተደርገው የሚወሰዱትን የምርጫ ስርአቱን በበላይነት የሚከታተል ልዩ /ነፃ/ አካል ያልነበረበት፣ የውጭ ታዛቢዎች ያልተሳተፉበት፣ የውክልና ዴሞክራሲ ስርአትን ጥያቄ ውስጥ በከተተ ሁኔታ ገዢው ፓርቲ ሚሊዮኖችን በእጩነት በማቅረብ የወድድርን ስነ አመክንዮ ያፋለሰበት በሚል ከሂደቱ ራሳቸውን ማግለላቸውን አስታውቀዋል፡፡

ፓርላማው ዓመታዊ ሥራውን ሊያጠናቅቅ 10 ቀናት ያህል ሲቀሩት ባደረገው መደበኛ ስብሰባ የተሰየሙት የቦርድ አባላት ተቃውሞ ይቀርብባቸው የጀመረው ተቃዋሚዎች የሚያዝያውን የአካባቢና የማሟያ ምርጫ «አስገዳጅ» በሆኑ ሁኔታዎች አቋርጠው መውጣታቸውን ከገለጹ በኋላ አይደለም፡፡ ገዢው ፓርቲ «ህገ መንግስቱን የሚቀበል፣ ለህገ መንግስቱ ታማኝ የሆነ» በሚል ለዕጩዎቹ መስፈርቱን ይፋ ባደረገበት ወትት እንጂ፡፡ ከሁለት ሳምንት በፊት «ኦፌኮ» በሚል ስያሜ የቅንጅትነት ህጋዊ ሰርተፍኬት እንዲሰጣቸው አመልክተው ከስምንት ወራት በኋላ ተገቢ ምላሽ ያለማግኘ ታቸውን ለማሳወቅ ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡትት ኦፌዴንና ኦህኮ «የቦርዱን ነፃና ገለልተኝነት እንድንጠራጠር አድርጎናል» ያሏቸውን ወራት ያስቆጠሩ ችግሮች ዘርዝረዋል፡፡ «አጠራጣሪ» ያሏቸውን ክንውኖች አስታከው አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ያነሱት የሌሎች አገራት የምርጫ ቦርድ አባላት አሰያየም ተሞክሮም ጥርጣሬው የአካባቢና የማሟያ ምርጫ ማግስት ያለመሆኑን ጠቋሚ ነበር፡፡ «በሌሎች አገራት የሚሰየሙት የምርጫ ቦርድ አባላት ማሕበረሰቡ ጠንቅቆ የሚያውቃቸው፣ በመልካም ዝናቸው ወይም በእውቀታቸው አንቱ የተባሉ፣ መፃህፍትን የፃፉ፣ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት

/ዩኒቨርሲቲዎች/ የሚያስተምሩና ‹በገለልተኝነት ምርጫው እንዲከናወን ባላደርግ ሕዝቡ ምን ይለኛል?›» በማለት እንቅስቃሴያቸውን የሚገመግሙ ናቸው ብለዋል፡፡

የምርጫ ቦርድ አባላት አሰያየምን አስመልክቶ ጠ/ሚ/ሩ ለፓርላማው የሚያቀርቧቸው እጩዎች በፓርላማ መቀመጫ ያላቸው ፓርቲዎች «ነፃና ገለልተኛ» ናቸው ብለው ያመኑባቸውን የሚጠቁሙበት ሲሆን በምርጫ ህጉ አዋጅ ቁጥር 532/99 መሰረት እንደሚሆን በመመቻቸቱ አጀማመሩ አዎንታዊነትን የተላበሰ ነበር፡፡ በተለይ በተለጣፊነት ሊታማ የማይችለውና በአቶ ቡልቻ የሚመራው ኦፌዴን የቦርድ እጩ ተጠቋሚዎችን እንዲያቀርብ ውክልና አግንቶ የነበረ መሆኑ እንደ እመርታ ቢቆጠርም ለስምምነት ባልታደለው የአገራችን የፖለቲካ መድረክ የተለመደ ድብብቆሽ ድርድሩ ተደነቃቀፈ፡፡ የተወሰኑትና ሰፊ ህዝባዊ ድጋፍ እንዳላቸው የሚነገርላቸው ፓርቲዎች ድርድሩን አቋርጠው ወጡ፡፡

ባለፈው ቅዳሜ በብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት በአገሪቱ ላሉ ፓርቲዎች በሙሉ የተደረገውን የስብሰባ ጥሪ ተከትሎ የህጋዊነት ፈቃድ ካላቸው 93 ያህል አገር አቀፍና ክልላዊ ፓርቲዎች የተገኙት ግማሽ ያህሉ ብቻ ናቸው፡፡በወራት የሚቆጠሩ ጊዜያት ብቻ በቀሩት አገር አቀፍ ምርጫ ዋዜማ ላይ ይህን መሰል ክስተት ሲያጋጥም ፖለቲን ፓርቲዎቹም ሆኑ ቦርዱ ጉዳዩን ትኩረት ሰጥቶ የመመርመር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## የገለልተኝነት ክስና በመዳህ ላይ ያለ ዴሞክራሲ

የምርጫ ቦርድ አባላት አሰያየምንና ፓርቲዎች ከተቋሙ ጋር ካላቸው የቀጥታ ግንኙነት አንፃር የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች በሙሉ የገለልተኝነት ጥርጣሬ ቢያስነሱም የባሰው ችግር ያለው ግን በወረዳና በክልል የቦርዱ ሰራተኞች ላይ መሆኑን ተፎካካሪ ፓርቲዎች በአጽንኦትና በተደጋጋሚ ሲገልጹ ይስተዋላል፡፡ የገዢው ፓርቲ አባላት ናቸው በማለት ይተቻሉ፡፡ ይህ ትችትና ቅሬታ እስካሁን በተደረጉት አገር አቀፍ ምርጫዎች ሁሉ ሲንፀባረቅ ቆይቷል፡፡ በ1997 ዓ.ም የቀድሞው ቅንጅት በ299 የምርጫ ጣቢያዎች ማጣራት እንዲደረግ መጠየቁ የሁኔታውን ስፋት ያሳያል ተብሎ ይታመናል፡፡ በወቅቱ የገዢው ፓርቲ አባል ድርጅቶች ሳይቀሩ «ምርጫው ይጣራልን» ያሉበት ሁኔታ ነበር፡፡

የገለልተኝነት ክሱ በተለያዩ ጭብጦች ላይ የሚቀርብ ቢሆንም የተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅም ቦርዱን ተጨማሪ መብት በማጎናፀፍ በተቃውሞው ጐራ ሌላ የቅሬታ ነጥብ የሚያስነሳ ሆኗል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የገንዘብ ምንጫቸውን ለቦርዱ ማሳወቅ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ይህ ሕግ ገዢውን ፓርቲ ጭምር የሚመለከት ቢሆንም የገቢ ምንጫቸው በአብዛኛው በውጭ ምንጮች ላይ የተመካውን ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያዳክም መሆኑ ስለሚታወቅ ቦርዱ ለኢህአዴግ ቀኝ እጅ ሆኖ የተከሰተበትን ህግ የተጎናፀፈበት ነው ሲሉ ተቃዋሚዎች ይከሳሉ፡፡ የፖለቲካ ሳይንስ ጠበብቶች ከምርጫ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ያለመግባባቶችንና የምርጫ

ሂደቱን የሚዳኙት ወገኖች/ቦርድ ወይም ኮሚሽን/ በገለልተኝነት ጉዳይ መታማት የዴሞክራሲያዊ ስርአቱ ያለበትን ደረጃ አመልካች ነው ይላሉ::

በአገራችን ያለውን የዴሞክራሲ ደረጃ አስመልክቶ ኢህአዴግ በተደጋጋሚ «በማደግ ላይ ያለ» በሚል የሰጠው የሁነቶች ነጽሮታዊ መግለጫ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል:: «በማደግ ላይ ያለ» የሚለው አገላለጽ በፖለቲካ ሳይንስ ጠበብቶቹ «በመዳህ ላይ ያለ ዴሞክራሲ» /Crawling democracy/ የሚል ስያሜ አለው:: መግለጫዎቹም አንድ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ የሚከተላቸው የአስተዳደር ስትራቴጂዎች ናቸው:: የሚጀምረው አንድ ግዙፍና ሌሎች ሊወዳደሩት የማይችሉት ፓርቲ (Dominant Party) በመገንባት ነው:: ሰፊና ወስብስብ የፖለቲካ መዋቅሮችን በመላ አገሪቱ ይዘረጋል፣ ቁልፍ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተቋማትን በቁጥጥሩ ስር ያደርጋል፣ በመርህ ደረጃ ነፃ የኢኮኖሚ ፖሊሲን ቢያውጅም በተግባር ግን የቁጥጥር ገበያን ያራምዳል:: እንዲሁም ለዴሞክራሲያዊ መንግስት እውንነት ቁልፍ በሆነው የህግ የበላይነት ላይ የሚኖረው አቋም ጠንካራና ቀጥተኛ ያልሆነ ነው::

## «መዳህ» ለስንት ዓመት?

አንድን የዴሞክራሲ ስርአት «በመዳህ ላይ ያለ»የሚያሰኘው ሌላው መገለጫ የስርዓቱ መሰረት ተጥሏል ከሚባልበት ወቅት አንስቶ «በማደግ ላይ ያለ» እየተባለ የሚወስደው የረዥም አመታት ጉዞ ነው:: ከሰሃራ በታች ካሉና በዚህ የእድገት ጉዞ ማዕቀፍ ወስጥ ከተካተቱ አገራት የተወሰኑት ቡርኪና ፋሶ፣ ኮንጎ ኪንሻሳ፣ ጋምቢያ፣ ናይጄሪያና ኢትዮጵያ እንደሚገኙበት መረጃዎችን ያመለክታሉ:: በመዳህ ላይ ያለ ዴሞክራሲ በራሱ አሉታዊ እሳቤ የለውም:: በተነፃፃሪ ዘይቤ ልክ እንደህፃን ልጅ ሊታይ ይችላል:: ህፃኑ ይፀነሳል፣ ይወለዳል፣ መዳህ ይጀምራል:: ከዚያ እየተወውተረተረ ተነስቶ መራመድ ይጀመራል:: እንዲህ እያለ ይቀጥላል:: የተወለደው ህፃን ለአመታት የሚድህ ከሆነ ግን የጤንነት ችግር እንዳለበት ስለሚታወቅ የህክምና መፍትሔዎች ይባጁለታል:: ፖለቲካዊ ሁኔታዎችም ተመሳሳይ አንድምታ አላቸው:: የዴሞክራሲ ስርአት እድገቱን ጨርሷል የሚባልለት ጽንሰ ሃሳብ ባይሆንም ሁል ጊዜ ገና በማደግ ላይ ከሆነ ግን ችግሩ ከገዢው ፓርቲ፣ ከተቃዋሚዎች፣ ከምርጫ ቦርድ፣ ወይስ ከሚዲያ ተቋማት ዳተኛ አሰራር በሚል የመፍትሄ አማራጮች ሲባጁለት ግድ የሚል ይሆናል::

## ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም

ከሁለት ቀን በፊት በምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ከተደረገው ውይይት በኋላ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ምልክት የሚወስዱበት፣ፓርቲዎች እጩዎቻቸውን የሚያስመዘግቡበት፣የመራጮች ምዝገባ፣የቅስቀሳና የምርጫ ቀን ይፋ ሆኗል::በዚህ መሰረት ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም የምርጫ ታሪክ የሚመዘገብባት ትሆናለች ማለት ነው::ጥያቄው ምን አይነት ታሪክ?የሚል ሲሆን ገዢው ፓርቲ፣ተቃዋሚዎች፣የሜዲያ

ተቋማትና ከሁሉም በላይ ሕዝቡ ለሚመዘገበው ማንኛውም አይነት ታሪክ ባለድርሻዎች ናቸው::

# ከመሰረታዊው ፍሬ ነገር የመሸሽ አባዜ

**በመሳይ ከበደ (ፕሮፌሰር)**

"Misunderstanding Nationalism: Rejoinder to professor Messay Kebede's Response" የተሰኘው የመጨረሻው የጃዋር የመልስ ጽሁፍ ችግሩ ለኢንተርኔት ክርክራችን ዋነኛ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ፣ ማለትም የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) «ላይጠገን ተንኮታኩቷል» በማለት ያወጀበትንና በተደጋጋሚ «ያከተመለት» መሆኑን የገለፀበትን ጽሁፍ ይበልጥ እየራቀ መሄዱ ነው:: የእርሱ ጽንሰ ሀሳብ ለዚህ ክስረት ተጠያቂው የአመራር ብቃት ማነስ ነው:: የኔ ነጥብ ደግሞ የአይዲዮሎጂ (የርዕዮተ-ዓለም) አግባብ የለሽነትም ብቃት ማነስን ሊያስከትል ስለመቻሉ በይበልጥ ወይም በጥልቀት እንዲመለከት መጠየቅ ነበር:: ጃዋር የአንድ ድርጅት አይዲዮሎጂ በብቃቱ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ስለመቻሉ በፍፁም ለመቀበል ያለመፍቀዱ ምክንያት ግልጽ አልሆነልኝም::

ጃዋር ከሌሎች የኦሮሞ ብሔረተኞች ከፍተኛ ግፊት እየተደረገበት ሳይሆን አይቀርም ብዬ እሰጋለሁ:: በዚህም ምክንያት መገልበጥን አሳይቷል፤ እርሱ የድርጅቱን ስኬቶች እጅጉን የሚያደናንቁ ቃላቶችን መጠቀም ሲጀምር፣ እኔ የኦነግ ጠላት ሆንኩኝ:: የቡድን ውስጥ አንድነትን (መደጋገፍን) የማስቀደም የብሔር ፖለቲካ ጠባይ የመጨረሻ ውጤቱ ወሳኝ አቋሞችን፣ ተቀባይነት ቢኖራቸውም እንኳ ዝም ማሰኘት ስለሆነ ይህ የሚያስገርም  አይሆንም::

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ የኦሮሞ ማንነትን እና ፍላጐትን በተመለከተ በአግባቡ እንድናጤን በጠየቀን በጃዋር የመልስ ጽሁፍ የመጨረሻ አንቀጽ እስማማለሁ፤ የአንድ ወገን የማንነት ማረጋገጫ ለብሔራዊ አንድነት ወሳኝ የሆኑትን የፓን-ኢትዮጵያ ጠባዮች ማስተዋወቅ ከማስፈለጉ ጋር እንዴት ሊስማማ እንደሚችል ሊነግረን ይገባ የነበረ ቢሆንም:: ክርክሬ የአንድን ማንነት ማረጋገጥን መቃወም አይደለም፤  ክርክሬ  በግልጽ ተገንጣይ የሆኑትን መግለጽ ሳያስፈልግ ማንነትን ከማረጋገጡ በተጓዳኝ የፓን-ኢትዮጵያ ጠባዮችን ማጐልበት አስፈላጊ መሆኑን የማይመለከቱትን መቃወም ነው:: የቀስተ ደመና አገር እሳቤን፣ ማለትም ለብሔር ጥያቄዎች ከገደብ የለሽ ማንነት ጋር የፖለቲካና የባህል መፍትሔ የሆነውን እሳቤ ያስተዋወኩባቸውን ጽሁፎች እንዲያነብ ጃዋርን በዚህ አጋጣሚ እጋብዘዋለሁ::

የመልስ ጽሁፉን ዝርዝር ዳሰሳ በተመለከተ የሚከተሉትን ነጥቦች አስቀምጣለሁ::

1. መሳይ «ድርጅታዊ ብቃት በቀዳሚነት የስትራቴጂ እና የቁርጠኝነት ውጤት ስለመሆኑ ለመቀበል አልፈቀደም» ሲል ጃዋር ጽፏል፡፡ የኔ ምላሽም፡- አንድ ሰው የድርጅትን ብቃት፣ ስትራቴጂ እና የቁርጠኝነት መጠን አይዲዮሎጂውን ከቁጥር ሳያስገባ እንዴት ሊገመግም ይቻለዋል? የሚል ነው፡፡ እዚህ ላይ የአይዲዮሎጂ ወስብስብ ትርጓሜን ማምጣት አያስፈልግም፤ አንድ የኢንተርኔት መዝገበ ቃላት «የአንድን ግቦች፣ ተስፋዎች እና ተግባሮች የሚመሩ ዓላማዎች እና እሳቤዎች ስብስብ» በማለት አይዲዮሎጂን ይተረጉመዋል፡፡ እናም ጃዋር «አንድ ድርጅት በተዘረዘሩ ዓላማዎቹ መሠረት ሊገመገም ይገባል» ሲል በይበልጥ እንደነገረን ግቦችን፣ ተስፋዎችን እና ተግባሮችን የሚወስን ጉዳይ ከብቃት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም ብሎ መከራከር ምክንያታዊ ነውን? ግልጽ በሆነ መልኩ፣ የተሳሳቱ ዓላማዎች አንድን ድርጅት ብቃት የለሽ ያደርጉታል፡፡

2. ጃዋር «ገለልተኛነት» እንደሚጐድለኝ ይገልፃል፤ ለዚህም ነው እኔ (እና እንደኔ ዓይነት ሰዎች) ጋር «ለብሔርተኝነት ንቅናቄዎችን ያነሰ ግምት መስጠት፣ በተሳሳተ መንገድ መረዳት እና በተሳሳተ መልኩ መመልከት» እንዳለ የተገለፀው፡፡ ፖለቲካ የተለያዩ ፍላጐቶች ፍትጊያ መሆኑን ሁላችንም እያወቅን ይህ የገለልተኛነት አቤቱታ ከባድ ነው፡፡ የፖለቲካ ግጭቶችን የምንፈታበት ትክክለኛው መንገድ አንዱን ወገን ገለልተኛ እንዲሆን በመጠየቅ አይደለም፡፡ ይህ አካሄድ ፖለቲካ የድርድር (የመስማማት) ጥበብ መሆኑን መዘንጋቱ ብቻ ሳይሆን አለመመጣጠንንም (imbalance) ጭምር ይፈጥራል፡፡ አንደኛው ተቀናቃኝ መፍጠር ስለሚፈልገው አገር በመናገር ግላዊ የመሆን መብት ሲኖረው እኔ ግን መጠበቅ ስለምፈልገው አገር የስሜቴን እንዳልገልጽ ተጠይቂያለሁ፡፡ ከገለልተኛነት ይልቅ ትክክለኛው አመለካከት የጋራ ማዕቀፍ ላይ የመድረስ ጥረት ነው፡፡

3. እንደ ጃዋር ከሆነ «የኦነግ አይዲዮሎጂ ቢከሽፍ ኖሮ በሀገሪቱ ኦሮሚያ የሚባል ቦታ ባልኖር ነበር፡፡» ምናልባት ሀሳባዊ ታሪክን እየጠቀስኩኝ ይሆናል፣ ነገር ግን ኦሮሚያ ሌላ ብሔርን የሚወክለው የሕወሓት ስጦት እንደነበረች የቅርብ ጊዜ ክንውኖች አረጋግጠዋል፡፡ እውቅና ሊሰጥ የሚገባው እውቅና ለሚገባው ነው፤ ምንም እንኳን ይህ የሆነው መልካም ላልሆነ ፕሮጀክት ቢሆንም፡፡ በየትኛውም መልኩ ኦሮሚያ ከራሷ በፈለቁ ድል አድራጊ ኃይሎች አልተመሰረተችም፡፡ እናም የኦሮሞ ህዝብ ለኦሮሚያ መፈጠር ለትግራይ ወራሪዎች ምስጉን እንዲሆን ከተጋበዘ ከአፄ ምንልክ በቀር ባይኖርም እውቅና መስጠቱ ቀደምት ጠቃሚዎችን የማያካትትበት ምክንያት ያስደንቀኛል፡፡ አፄ ምንልክ የኦሮሞ ህዝብን በኢትዮጵያ መንግስት ስር አንድ በማደረግ፣ ብሎም በተለያዩ ቅኝ ገዥዎች ስር ሆነው ከመበታተን በማትረፋቸው ሊመሰገኑ ይገባል፤ ከሁሉም በላይ

እንዳሁኑ ጊዜ ሁሉ በራስ ጉበና ድርሳን እንደተመሰከረው በትግሉ ላይ የኦሮሞ ህዝቦች ሙሉ ለሙሉ ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡

4. ጃዋር ለኦሮሞ ብሔረተኝነት ኃይል ያነሰ ግምት ስለመስጠቴ ሲወቅሰኝ ምላሼ የሚሆነው «የኦሮሞ ህዝብ ከተቀረው የሀገሪቱ ክፍል የመለየት ጥልቅ ፍላጐት ቢኖረው ኖሮ የትኛው በምድር ላይ ያለ ኃይል ሊያቆመው አይቻለውም ነበር» በማለት የገለጽኩበትን ያለፈውን ጽሁፌን ጃዋር በተሳሳተ መልኩ ማንበቡን መግለጽ ነው፡፡ ሆኖም ችግሩ ያለው ሌላ ቦታ ነው፡፡ ጃዋር የኦሮሞ ህዝብ ለኦሮሚያ የከፈሉትን መስዕዋትነት አስታውሶኛል፡፡ ይሁንና አንድ ወሳኝ ነገር ዘንግቷል፤ ይኸውም ለኦሮሚያ ከሞተው ለኢትዮጵያ አንድነት የተሰዋው የኦሮሞ ህዝብ  ይበልጣል፡፡ የደርግ ሰራዊትን የብሔር ስብስብ በቀላሉ መመልከት የኦሮሞን ህዝብ ግዙፍ መስዕዋትነት ለማሳየት በቂ ነው፡፡ ከአንድ ወገን ማረጋገጫ ይልቅ ስለሁለትዮሽ ቁርጠኝነት እናውራ፤ ማለትም የራስን ብሔር ከማመገሱ በተጨማሪ ዜግነትን ወይም ግዛትን መሠረት በማድረግ ወደ አንድ አገር ያነጣጠረና ከሌሎች የብሔር ቡድኖች ጋር የጋር ስለሆነ ህልም ፡፡

5. ስለመድረክ ሲያነሳ ጃዋር ድርጅቱን የፈጠሩት «የኦሮምኛ ቋንቋ ብሔራዊ ቋንቋ እንዲሆን በመቀበል እውነታውን በመከተላቸው ጉልህ ለውጥ አስመዝግበዋል» ብሏል፡፡ ሆኖም ይህንን ማድረጋቸው መገንጠልን እንደማይደግፉ በመግለጽ ለኢትዮጵያ አንድነት ባላቸው ቅድመ ሁኔታ የለሽ ቁርጠኝነት አማካኝነት እንደነበር ጃዋር ሳይጠቅስ አልፎታል፡፡ በከዚህ ቀደም ጽሁፌ ለጋራ ስምምነቶች መሠረቱ ለአንድነት የሚደረግ ቁርጠኝነት ስለመሆኑ አስገንዝቤያለሁ፤ ይህንንም የጋራ መኖሪያ ቤት በመገንባት መልኩ ገልጨዋለሁ፡፡ ተገንጣይነትን የሚያራምዱ ወገኖች ሊረዱት ያልፈቀዱት ነገር የራስን እድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል አንድ ቡድን የሚፈልገውን ሁሉ እስካላገኘ ድረስ በአገነጠላለሁ ዛቻ ፖለቲካዊ ማስገደድን እንዲተገብር በመፍቀዱ ለዴሞክራሲያዊ ውሳኔዎች እንቅፋት የሚሆን ልዩነት መፍጠሩን ነው፡፡

6. ለጃዋር የኦሮሞ ብሔርተኝነት መጐልበት ዋናው አሽጋጋሪ የሆነ ኃይል ነው፤ «ግዙፉ ባይነሳ በደቡብ የሚገኙት አነስተኛ ቁጥር ያላቸውና የተጨቆኑት ሁሉ እስካሁንም በድሮ ስያሜያቸው በተጠሩ ነበር፡፡» በማለት ጃዋር ያብራራዋል፡፡ የኦሮሞ የማንነት ግፊት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ዋናውን ኃይል እንደሚወክል አልክድም፡፡ ነገር ግን አሁንም በድጋሚ እውቅና ለሚገባው እውቅና እንዲሰጥ እጠይቃለሁ፡፡ ከዚህ ቀደም ለብሔሮች የሚሰጡ ስያሜዎች የቀሩት በአንድ የብሔር ፖለቲካ ፓርቲ ሳይሆን ሁለቱም የብዙሃነ-ብሔር አመለካከት በነበራቸው በኢትዮጵያ የተማሪዎች ንቅናቄ እና በደርግ ነበር፡፡ የህዝቦች ባህል እና እምነቶች በእኩል ዓይን እንዲታዩ ለመታገል የአንድ የብሔር ፓርቲ አባል መሆን አይጠበቅብህም፡፡ በአሜሪካ የብሔር ፓርቲዎች የሉም፤ ሆኖም ህዝቦች

በስብጥርነታቸው ጥበቃ ይደረግላቸዋል። ከብሔር ፖለቲካ በስተጀርባ ሚገኘው ዋነኛ ዓላማ ህዝቦች ፍትህ ማግኘታቸውና በእኩል ዓይነት መታየታቸው አይዳለም፤ ይልቁንም ሀብቶችን በብቸኝነት ለመያዝ በሚታገሉ ስልጡን የማህበረሰቡ አባላት የመንግስት ስልጣንን መቆጣጠር ነው።

7. «ኢትዮጵያ ያለተቋጨች ፕሮጀክት ነች» በሚለው ነጥብ ከጃዋር ጋር እስማማለሁ። እንደውም ያልተሳካች ፕሮጀክት ብዬ እስከመግለጽ ደረጃም እደርሳለሁ። ላለመሳካቱ ምክንያቱ እኛን እዚህ ሊያስጨንቀን የሚገባ አይደለም። ያም ተባለ ይህ፣ እየሰማሁት ያለው አይነት የዘውጌ ብሄርተኝነት ውይይት ፕሮጀክቱን የሚያስቀጥል ነው የሚለውን አምኜ ለመቀበል ከብዶኛል። ጠቅላላው ጉዳይ ነባር (ውስጣዊ) ቁርኝትን (የጋራ ስሜትን) ከየበላይ ማንነት ጋር ለማጋባት ከሆነ፣ የተለየ አይነት ብሄርተኝነት የተቀበልነው ፕሮጀክቱን ለማሳካት አይደለም - ፕሮጀክቱን ሆን ብሎ ለማፍረስ እንጂ።

8. ለብሔርተኝነት ኃይል አጽንኦት ለመስጠት ጃዋር «የብሔር ንቅናቄዎች ከመደብ ትግል ይልቅ ለምን እስካሁን ቆዩ?» ሲል ይጠይቃል። በሌላ አገላለጽ በኢትዮጵያ የሕወሓት እና የሻዕቢያ የብሔር ንቅናቄዎች የህብረተሰባዊ አብዮት ጠባቂዎችን በምን ምክንያት ነበር ያሸነፉት? ደም ከፍላጐት የመወፈሩ እሳቤ በትክክልም በስልጡኑ ማህበረሰብ ለመቀስቀስ የሚጠቀሙበት መበዝበዢያ ክርክር ነው። «መበዝበዢያ» ያልኩበት ምክንያት ከአምሳየነት ጋር በመዳመር እነዚህ ስልጡን የማህበረሰቡ አባላት የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ዓላማ ተፈጥሯዊ ስሜቶችን በመገደቡ ነው። የሌኒኒስት ሶሻሊዝምም ሆነ የፋሺስት ሥርዓቶች መውደቅ የተገለፀ ዓለማቸው ምንም ይሁን ምን - የመደብ ጥቅም ወይም የዘር ሀረግ - ለመንግስትና ለስልጡን የማህበረሰቡ አባላት የበለጠ ሥልጣን መስጠት ነፃ የመውጫ መንገድ አለመሆኑን ያስተምረናል፤ ነፃነት የሚከሰተው የሥልጣን መወሰን ሲኖር ነው። ፖለቲካዊ ነፃ መውጣት የቤተሰብ ጉዳይ አይደለም። ህዘቦች ነፃ የሚሆኑት የመንግስትን ሥልጣን ሲገድቡና ሲከፋፍሉ እንጂ ተገቢውን ግብ የሚሳካት የተሳሳተ ግንዛቤ ወስደው ገደብ የለሽ እነዲሆን ሲፈቅዱ አይደለም። በሥነ-ምግባር (Ethics) ረገድ እውነት የሆነው በፖለቲካም እውነት ነው፡- ውጤት መቼም ቢሆን ምክንያትን አያረጋግጥም።

9. በዚህ ምክንያትም ነው የግለሰብ እና የሁል-አቀፍ መብቶች ቀዳሚነት ከደም፣ ከመደብ ጥቅም፣ ከሀይማኖትና ከመሳሰሉትን መስፈርቶች በላይ የሚሆንበት የፖለቲካ ሥርዓት መመስረት የሚገባን። ከሌሎቹ መስፈርቶች በተቃራኒ የግለሰብ እና ሁል-አቀፍ መብቶች ግለሰብን መልካም ካልሆኑና መልካም ለመሆን ከሚያስመስሉ ኃይሎች በመጠበቅ የመንግስትን ሥልጣን ወደመገደቡ ያመራሉ። ነፃ ስለማውጣት ከማውራት በቀር ሕወሓትም ሆነ ሻዕቢያ ለሚወክሏቸው የብሔር ቡድኖች ዴሞክራሲያዊ

አስተዳደርን የሚመስል ነገር እንኳን አላቀረቡም። እዚህ ላይ አሳዛኙ ነገር የጃዋር እርስበራሱ መጋጨት ነው፤ የኦሮሞን አፈና የማባባስ ውጤት ብቻ ያለውን ሽንፈታቸውን እያወቀ ሕወሓት እና ሻዕቢያ እንደ ነፃ አውጪ ንቅናቄዎች ሞዴሎች አድጐ መግለፁ። በወለጋ የስታሊኒስት የፖለቲካ ሥርዓት ትግበራን የሚገልፀውን የዶክተር ነጋሶ ጊዳዳን ጽሁፍ ያነበ ዘንድ ጃዋርን እማፀናለሁ። የኦሮሞ ማህበረሰብ ስልጡን አባላትን ነፃ በማውጣት ስም የኦሮሞ ህዝብን የመጫናቸው ሁኔታ የብሔር ፖለቲካ አደጋን እና ግለሰባዊ መብቶች የትግሉ ማዕከል የማድረግ አስፈላጊነትን በግዴታ ያመላክታል። የወለጋ ህዝቦች የሚያስፈልጋቸው ለግለሰባዊ መብቶቻቸው የፌደራል ጥበቃ ነው። ከሁሉም በላይ ከኦሮሞ ህዝብ ባልተናነሰ የትግራይ ህዝብንም ጨምሮ ሌሎች የብሔር ቡድኖችም ብሔር-ዘለል የሆነ መንግስት ሊታደጋቸው ያስፈልጋል። ይህም ምን ለማለት ነው፣ ኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት ብሔር-ዘለል ወይም ብሔራዊ የፌደራል ኃይል በማቆም የሚከሰት ከብሔር መንግስት ይልቅ ግለሰባዊ መብቶችን ቀዳሚ ማድረግ እንጂ ሌላ አይደለም።

10. የብሔር ንቅናቄዎች ከመደብ ትግል ይልቅ ለምን እስካሁን ቆዩ ለሚለው ጥያቄ መሠረታዊ ምላሽ ኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት በሶሻሊስት አይዲዮሎጂ ክሽፈቶች እጅጉን በመሸርሸሩ ነው። ሽንፈቱን የሚያስረዳው የብሔር ንቅናቄዎች ጥንካሬ አይደለም፤ ነገር ግን ታላቁ ኢትዮጵያዊ የታሪክ ተመራማሪ ገብሩ ታረቀ በቅረቡ ባሳተሙት "The Ethiopian Revolution: War in the Horn of Africa" በተሰኘ እጅግ ጠቃሚ መጽሐፋቸው እንዳስቀመጡት «አብዮታዊው መንግስት በመጨረሻ ተሸንፏል፣ ምክንያቱም ትላልቅ ቃል-ኪዳኖቹን ለማሳካት ስላልቻለ - ነፃነት፣ እኩልነት እና ብልጽግና።» በርግጥ የደርግ አምባገነናዊ ትግበራ፣ የመከፋፈል ግቦች፣ እና ኢኮኖሚያዊ ውድቀት በአንድነት ተደምረው የወታደራዊ ኃይሎቹን ብቃት ደምስሰውታል። ጃዋር ከሚለው በተቃራኒ በሚሟሟ አይዲዮሎጂ አማካኝነት የተከሰተ የብሔርተኝነት ሽንፈት ወሳኝ ምሳሌ ይሄ ነው። ጀዋር ደርግ «ለፌዴሬሽን ቢደራደር» ኖሮ የኤርትራ ጉዳይ መፍትሔ ሊያገኝ ይችል እንደነበር እንደመቀበሉ የምሳሌውን ወሳኝነት ሊመለከት ይገባው ነበር። በትክክልም ኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት ማዕከላዊነትን እና አምባገነናዊነትን በሚያራምድ አይዲዮሎጂ ልፍስፍስ እንዲሆን ያደረገው የመደራደር ብቃት ማነስ ነው።

11. ጃዋር «ለብሔር ብሔረተኝነት፣ ለመገንጠል ጥያቄና ለትጥቅ ትግል መስፋፋት ተጠያቂው ግራ-ዘመም አይዲዮሎጂ ነው» እንዳልኩኝ ይገልጽና ግራ-ዘመም ያልሆኑ ነፃ አውጪ ንቅናቃዎችን በመጥቀስ አልክ የተባልኩትን ዓረፍተ ነገር ውድቅ ያደርጋል። ይሁንና ግራ-ዘመም አይዲዮሎጂን መጥቀሴ ኦነግን የገደበውን ትውፊት በተመለከተ የፃፈውን የራሱን ትንታኔ ማስተጋባቴ ብቻ ነበር። የእርሱን ትንታኔ ለማስታወስ ያክል፡- «ኦነግ አብዮቱን ያስከተለው የተማሪዎች ንቅናቄ የጉዲፈቻ ልጅ ነው፤ በዚህም ምክንያት

ከዚያ ዘመን ከፈለቁ እንደ ኢሕአፓ፣ ሕወሓት እና ሻዕቢያ ካሉ ሌሎች ድረጅቶች ጋር የተወሰኑ ተመሳሳይ ድርጅታዊ ጠባዮችን እና መለያዎችን ይጋራል»፤ «ከተማሪዎች ንቅናቄ የፈለቁት የፖለቲካ ኃይሎች ይመሩ የነበረው ማዖ ዘዱንግ እና ስታሊንን በሚያመልኩ ግለሰቦች ነበር፤ እናም ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ፣ ግትር እና ተቆጣጣሪ የሆነ ዓይነት ድርጅታዊ ሞዴልን ተከተሉ፡፡» ትክክል፣ ግራ-ዘመም ያልሆኑ የብሔረተኝነት ንቅናቄዎች አሉ፤ ነገር ግን የኢትዮጵያን ጉዳይ በተመለከተ የጎሳ-ብሔረተኝነት ንቅናቄዎች የመነጨት ጽንፈኝነትን እና በዜሮ ድምር ጨዋታ የተነደፈ የፖለቲካ ትግል ራዕይን ከሚጋሩት ከተማሪዎች ንቅናቄ መከፈል ነው፡፡ ከ1966 አንስቶ የተከሰቱት ሁሉም ክንውኖች እና አሳዛኝ ሁኔታዎች ሀብቶችን ለመጠቀም ያመቻቸው ዘንድ የመንግስት ሥልጣንን በብቸኝነት መቆጣጠርን የሚያራምዱ አይዲዮሎጂዎችን ያነገቡ ልሂቆች ለመነሳታቸው አያሌ ማሳያዎች ናቸው፡፡ ልሂቃን የባህል ውስንነትን (ቋንቋ፣ ሀይማኖት፣ የጋራ የዘር ግንድ፣ የመሳሰሉትን) በማንሳት በመንግስትና በባህል መካከል ላለው ተፈጥሯዊ ግንኙነት የሚከራከሩበት መንገድ እንደመሆኑ ተገንጣይነት ወይም የጎሳ-ብሔረተኝነት ከእንዲያ ያሉ ማሳያዎች አንዱ ነው፡፡ በዚህ መንገድ ተቀናቃኞቻቸውን እንደሌላ ፍጡር በማግለል ብቸኛ የሥልጣን መብትን ይመሰርታሉ፡፡

/ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ፣ በኦሐዮ ዴይተን ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና መምህር ሲሆኑ ከአምስት ያላነሱ መጻህፍት ደራሲም ናቸው፡፡ ከመጽሐፎቻቸው ውስጥ Radicalism and Cultural Dislocation in Ethiopia; እንዲሁም Africa's quest for a Philosophical Decolonization ተጠቃሾች ናቸው/

# ብሔርተኝነትን አጣርሶ መገንዘብ

ጃዋር ሲራጅ ሞሃመድ

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) የተከተለው ራስን በራስ የማስተዳደር ርዕዮተ-ዓለም፣ በባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ስኬታማነቱን አሳጥቶታል በሚለው የፕ/ር መሳይ ከበደ ግንዛቤ ምክንያት ይህ ክርክር ቢጀመርም፣ ፕሮፌሰሩ ድምዳሜውን የሚደግፍለት አንድም ማስረጃ አላቀረበም፡፡ «ትክክለኛ» ርዕዮተ-ዓለም ስኬት ማምጣቱን እና «መጥፎ» ርዕዮተ-ዓለም የትጥቅ ትግልን ለውድቀት መዳረጉን በተጨባጭ የሚያስረዳለት አንድም ምሳሌ እንኳን አልጠቀሰም፡፡ እንዲሁም፣ ኦነግ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ማቀንቀኑ እንዴት ደካማ እንዳደረገው አያብራራውም፡፡ ተመሳሳይ ርዕዮተ ዓለም ያቀነቀኑ ድርጅቶች የተለያዩ ውጤቶች ማስከተላቸውን ምሳሌዎችን በማንሳት ያቀረብኩ ቢሆንም፣ ድርጅታዊ ውጤታማነት /ብቃት/ በቀዳሚነት የስትራቴጂ እና የቆራጥ አመራር ውጤት መሆኑን አልተቀበለም፡፡ ከዚያ ይልቅ፣ የመሳይ ሁለት ጽሁፎች ትኩረት የሰጡት፣ እንደ ርዕዮተ-ዓለም ራስን በራስ የማስተዳደር ድክመት ነው ብሎ ያመነውን ነቅሶ በማውጣት ላይ ነውና ወደዚህ ርዕዮት ዓለማዊ ክርክር ለመግባት

እየሞከረ ነው የሚመስለው:: ሆኖም በእንደዚያ ዓይነት ክርክር ላይ ተሳትፎ ለማድረግ አልፈቀድኩም ምክንያቱም ፕ/ር መሳይ ምላሽ የሰጠበት ጽሁፌ እየተካሄደ በሚገኘው የርዕዮተ-ዓለማዊ ክርክር ወገንተኝነት የለበትምና ነው:: የደመደምኩት ርዕዮተ-ዓለም የድርጅቱን ውጤታማነት ካደናቀፉ ዋና ዋና አላባውያን መካከል የማይካተት ነው ብዬ ነው::

የፕ/ር መሳይ ከበደ ሁለት ጽሁፎችን በጥሞና በማንበብ የተገነዘብኩት ምንድነው ያነሳቸው አብዛኛዎቹ ነጥቦች ምንጫቸው በአጠቃላይ ለ«ብሔር ፖለቲካ» እና በተለይ ደግሞ ለኦነግ ካለው ጥላቻ እንደሆነ ነው:: እንደኔ እምነት፣ ድርጅታዊ ውጤታማነትን በርዕዮተ-ዓለም ምርጫችን ላይ በመመስረት መገምገም ገለልተኝነታችንን ያሳጣዋልና አይረዳንም:: እንደእኔ ምልከታዎች፣ ይህ የገለልተኝነት መታጣት ነው በርካታ ግለሰቦችና ቡድኖች ብሔርተኛ ንቅናቄዎችን ዝቅ አድርገው እንዲመለከቱ /እንዲንቁ/ ፣ አጣርሰው እንዲገነዘቡትና በስኬት እንዳይወጡት ወደማድረግ የሚመራቸው:: በዚህ ጽሁፌ ጉዳዩን በአጭሩ እቃኛለሁ::

## ብሔርተኝነትን መናቅ

## የኦነግ ርዕዮተ-ዓለም ከተጠበቀው በላይ ስኬት ወይስ ክስረት?

የኦነግ ርዕዮተ-ዓለም ከስሯል በሚለው የፕ/ር መሳይ የተደጋገመ እወጃ አልስማማም:: እንደማስበው እንዲያ ያለ ግምት ከእውነታው በጣል የራቀ ነው:: ፕ/ሩ እየጠቀመ ያለው ርዕዮተ-ዓለም የ«ብሔርተኝነት አጀንዳ»ን ነው ብለን ብንገምት፣ የኦሮሞ ብሔርተኝነት የወደፊቷን አገር ኢትዮጵያን ሊወስን የሚያስችል በጣም ጠንካራ የፖለቲካ አደራጅ ኃይል ባይሆን ኖሮ እኔም ሆንኩኝ ፕሮፌሰሩ ይህን ጉዳይ ለመቃኘት ፍላጎት አይኖረንም ነበር:: የኦነግ ርዕዮተ-ዓለም የተኮላሸ ቢሆን ኖሮ፣ በሆነ ወቅት ኦሮሞነትህን ይፋ ማውጣት አሳፋሪ በነበረበት አገር ውስጥ ኦሮሚያ የምትባል ምድር አትኖርም ነበር:: ይህ ርዕዮተ-ዓለም የከሰረ ቢሆን ኖሮ፣ በፊት አፋን ኦሮሞ መናገር አስነዋሪና የኋላ-ቀርነት ምልክት በነበረበት አገር ውስጥ 20 ሚሊዩን ሕፃናት በቋንቋው አይማሩም ነበር::

እንደእኔ አመለካከት፣ ፖለቲካዊ ርዕዮተ-ዓለም ከስሯል የሚባለው፣ ደጋፊዎችን መሳብ ከተሳነው ነው:: የኦነግን የ«ብሔርተኝነት አጀንዳ» ስንመለከት፣ የድርጅቱ እጅግ ደካማ ውጤታማነት ቢኖርም፣ ከጠቅላላው የኦሮሞ ሕዝብ ያለው የድጋፍ ደረጃ አስደናቂ ነው:: እርግጥ፣ ከተጸነሰበት ጊዜ ጀምሮ የኦነግ ትልቅ ድል («ድሎች») የኦሮሞ ብሔርተኝነትን በጥበባዊ አካሄድ ማቀጣጠልና ማጎልበቱ /ማፋፋቱ/ ነው:: ለዚህ እውነታ ማስረጃ የሚሆነው የኦሮሞ የፖለቲካ ኃይሎች ያስቀመጡን ግብ ለመቀዳጀት በሚከተሉት አካሄዶችና መንገዶች የተለያዩ ቢሆኑም፣ ሁሉም የባሕል መደፍጠጥን፣ ፖለካዊ ጭቆናን፣ ማሕበራዊ መገለልን እና ኢኮኖሚያዊ ብዝበዛን መፋለም ሙሉ በሙሉ የሚጋሯቸው መሆናቸው ነው:: ለዚያም ነው የኦሮሞ ብሔርተኞች ላለፉት

ሁለት አስርት ዓመታት ለወቅቱ ሥርዓት ቁጥር አንድ ስጋት የሆኑት እና በዚህም ምክንያት፣ በርካታ ኢትዮጵያውያን እማኝነት እንደሰጡት፣ የአገሪቱን 95 በመቶ የፖለቲካ እስረኞች እነርሱ የሆኑት። የሥርዓቱ የአገዛዝ መመሪያ በማንነት ላይ የተመሰረተ ኢ-ፍትሀዊነት እስከሆነ ድረስ ይህ እውነታ ወደፊትም የሚቀጥል ነው። እናም፣ ለመከራከር ሲባል ብቻ ሰው ራሱን ካላታለለ ወይም ራሷን ካላታለለች በስተቀር፣ የኦነግ ርዕዮተ-ዓለም ስኬታማነት ከተጠበቀው በላይ ነው። ይህን ርዕዮተ-ዓለም ለስኬት ያበቃው ምን እንደሆነ ግልጽ ነው፡- የተገላቢጦሽ ውጤት ያስከተሉ፣ የኦሮሞ መነጠልን ያገዘፉና ብሔርተኝነትን በማጠናከር ስርጭቱን ያፋፋሙ በተከታታይ ፈላጭ ቆራጮች የተፈጸመ ከፍተኛ ባሕላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ጭቆናዎች ናቸው።

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ተጨባጭነት ያለው ተጽዕኖ ለማምጣት ፍላጎት ያለው ማንኛውም ግለሰብ፣ ይህ ኃይል ሳይጠየን ወቅታዊውን ሁኔታ ማስቀጠል ወይም መለወጥ ከረዥም ጊዜ በፊት የማይቻል መሆኑን የሚያውቀው ነው። ለዚያም ነው የኦሮሞ ጥያቄዎችን የሚቃወሙ፣ ገዢው ግንባርም ሆነ ተቃዋሚ ቡድኖች፣ የብሔርተኝነትን ተቀባይነት ለማዳከም እና የእነርሱን ጥምረት ለማግኘት ቀስ በቀስ ሳይወዱ በግድ እየተቀበሏቸው የሚገኙት። አገዛዙ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ እየተባባሰ በሄደው ሕዝባዊ ቁጣ ስጋት ስለገባው ነው ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል የራስ ገዝነት ሥልጣንን የሚጨምሩ ማሻሻያዎችንና *አፋን ኦሮሞ* በትምህርትና በሚዲያም እንዲስፋፋ የሚያስችሉ ማሻሻያዎችን እየተገበረ የሚገኘው። ባለፉት ዓመታት እነዚህ ጥያቄዎች ይመለሱ ዘንድ በመቶዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች መገደላቸው ሊታወስ የሚገባ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ጉዳዩን ችላ ለማለት ወይም የኦሮሞ ንቅናቄ ያገኛቸውን ውጤቶች ተቃውመው ለመሰለፍ ሲሉ በ1997 «የብሔር ፖለቲካ አያስፈልግም» የሚል ሰበብ የተጠቀሙ ተቃዋሚ ቡድኖች፣ አሁን *አፋን ኦሮሞ* እንደ ብሔራዊ ቋንቋ በድንገት በመቀበላቸው እንደታየው፣ እውነታውን እንዳለ በመቀበል በአሁኑ ወቅት ፍጹም /የፖሊሲ፣ እርምጃ፣ አቋም ... / ለውጥ አድርገዋል። ከጥቂት ዓመታ በፊት በአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ የ*አፋን ኦሮሞ* የስርጭት ሰዓት መራዘሙን በመቃወም የተወሰኑት እነዚያ ሰዎች የተቃውሞ ሰልፍ በዋሽንግተን ዲሲ አደራጅተው የነበረ መሆኑ ሲታወስ፣ ወቅታዊው እርምጃቸው በኦሮሞ ብሔርተኞች ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ የሚያበረታታ ለውጥ ነው።

ኃይሉ እየተጠናከረ በሄደው የኦሮሞ ማዕበል ሰዎች የፍርሀት ጉልላታቸውን ደርምሰው ይህ ንቅናቄ ለመላ ኢትዮጵያውያን በጠቅላላ ያመጣቸውን አያሌ አስተዋጽኦዎች እንዲቀበሉ አበረታታለሁ። ተከታታይ ሥርዓቶች በደቡብ፣ በመንግስት ድጋፊነት፣ የጫኑትን ባሕላዊና የቋንቋ ጭቆና ፖሊሲ እንዲያስወግዱ ያስገደዳቸው የአብላጫው መንቃት ነው። አብላጫው ባይነቃ ኖሮ፣ ምንም እንኳን የኃብታቸው ምንጭ ቢሆኑም፣ ጭቁን የደቡብ አናሳዎች አሁን ድረስ «ባሪያ»፣ «ሻንቂላ»፣ «ወላሞ» እና ወዘተርፈ እየተባሉ በመንግስት ሚዲያ እየተዋረዱ ይጠሩ ነበር።

ስለኦሮሞ ብሔርተኝነትና ስለጥያቄዎቹ በምንናገርበት ወቅት፣ ፕ/ሩ ለመቃኘት የሚፈልገው «ራስን በራስ መጉዳት /ማቁሰል» በተጨማሪ ከታሪክ አንፃር መተንተን አለበት:: ኦሮሞ በሕዝብ ብዛት አብላጫ ቢሆንም ሁሌም በፖለቲካዊና ማህበራዊ መድረኮች አናሳ ነው:: በቅርበ ከ35 ዓመታት በፊት አብላጫ «ኢትዮጵያውያን» «ኦሮሞ» ተብሎ የሚጠራ ሕዝብ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል የሚኖርና ክብርና የማይገሰሱ መብቶች ያሏቸው የሰብአዊ ፍጡር አካል መሆኑን በጭራሽ አይቀበሉም ነበር:: ለኦሮሞ ብሔርተኞች፣ ለኢትዮጵያ የተማሪዎች ንቀናቄና እንዲሁም በተጨማሪ ለግራው ምስጋና ይድረስና፣ «ግማታም ጋላ» አሁን የተከበረ «ኦሮሞ» ሆኖ ተቀባይነት አግኝቷል:: የወያኔ ደህንነቶችን ጨምሮ በፊንፊኔ ለጸረ-ኦሮሞ የእዛው በዛው ኮሜዲ ግፊት የሚያደርጉ የያኔዎቹ ቅሪቶች አሁን ድረስ ያሉ ቢሆንም፣ ቀናቸው እየጨለመባቸው ነው:: አሁን፣ በሀስተኛው ሚሊኒየም፣ ከትግሉ የሚታዩ ስኬቶች በኋላ፣ ኢትዮጵያውያን የኦሮሞ ብሔርተኞች ወደ መሀል ሄደው የአገሪቱን ዴሞክራሲ ለማጎልበትና አንድነት ለማጠናከር አመራርነቱን ይረከቡ ብለው የሚያቀርቡት ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ግን መሻት ብቻ ነው:: ነገር ግን፣ በአሁኑ ወቅት ራሱን ባገኘበት ታላቅ ስፍራ ያደረሰውን የኦሮሞ ብሔርተኝነት አንዱ ለማሳነስና ለማጥፋት የሚጣጣር ከሆነ ይህ «አመራርነቱን ይረከቡ» ጥያቄ ተዓማኒነት ኖሮት የሚያስተጋባ አይሆንም:: የኦሮሞ ብሔርተኞች «ወደመሃል ግቡ» ለሚለው ጥሪ አጽንኦት ሰጥተው የሚያዳምጡት፣ ያ «ጥሪ» እስከዚህ ነጥብ ድረስ ያደረጉትን መስዋዕትነት ስሜት በመጋራትና በመረዳት የተደገፈ ከሆነ ብቻና ብቻ ነው:: ከዚህ በስተቀር ተዓማኒነት የሌለው የ«አራዳ» ጥሪ ነው የሚሆነው::

ፕሮፌሰር መሳይ እኔን ካለአንዳች ማስረጃ የአማራ ጠላት አድርጎ እየወነጀለ የሚያቀርበው ጥሪ የተሳሳተ አካሄድ ለመሆኑ ሌላኛው ምክንያት ያ ነው:: የባላባትነት የበላይነት በነገሰበት የፈላጭ ቆራጭ ባህል ትክክለኛ መገለጫን በተከተለ አካሄድ፣ «አንተን /እናንተን/ ያስናሰለችሁ በአማራ፣ በአቢሲኒያውያን እና በኢትዮጵያ ኦሮሞ በጉልበት ከመግዛቱ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጭብጦች ላይ ያላችሁ ጥላቻ ነው::» ይለኛ ል:: ፕሮፌሰሩ የራሱን «ርዕዮተ-ዓለም» ለመከላከል እውነታውን እና እግረ መንገዱንም ክብሩን መስዋእት ለማድረግ ፍቃደኛ በመሆኑ፣ በህይወት እያለሁ እኔን አጣርሶ ለማስቀመጥ የተገደደ ይመስላል:: አማራን አልጠላምም፣ በቅኝ አገዛዝ ንድፈ-ሃሳብም ላይ አልተንጠለጠልኩኝም:: እነዚህ ፕሮፌሰሩ ብቸኛው የኢትዮጵያ አንድነት ተቆርቋሪ ለመምሰል እንዲሁ አእምሮው የፈጠራዎች ናቸው::

ሆነም ቀረ ልለው የምፈልገው፣ ኢትዮጵያ ያልተቋጨች ፕሮጀክት መሆኗን ነው:: በምትይዘው የመጨረሻ ቅርጽ ሁላችንም አስተዋጽኦ አለን:: ሆኖም ለዚህ ስኬታማነት የሚጠበቅብን ዝቅተኛው የስነምግባር ደንብ እርስ በእርስ መደማመጥ፣ አንዳችን የሌላኛችንን ህመም ማድመጥና እውነታዎችን ሳናጣርሳቸው እንዳሉ ማስቀመጥ ነው:: የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄና ከዚያ በኋላ የተከተሉትን ሁሉንም የፖለቲካ ንቅናቄዎች ፍሬ አልባ ያደረጉ ታክቲኮች ሁላችንም በሽንፈታችን

ያጣጣምናቸውና ጊዜው ያለፈባው ናቸው። አዲስ መንገድን፣ አዲስ ጅማሮን መሞከር አለብን።

## የብሔርተኝነት መንስዔዎችን አጣርሶ መረዳት

## የጥቂት ጉልበተኞች ማወናበድ ወይስ የተቃውሞ መገለጫዎች

እውነተኛውን የብሔርተኝነት መንስኤን - በማንነቱ ላይ የተመሰረተ ኢ-ፍትሃዊነትን - አበክሮ ውድቅ በማድረግ «ብሔርተኛ» ጥቂት ጉልበተኞች ሕዝባቸውን በዝብዘዋል በማለት ፐ/ር መሳይ በመደጋገም ይወነጅሏቸዋል። ስለኦሮሞ ብሔርተኝነት ሲያወራ፣ «ጃዋር እውነታው ነው ብሎ የሚያቀርበው ገና እውን የሆነ አይደለም፤ እውነታው ያለፉ በደሎችን ለመከፋፈል ምክንያታዊነት ለመስጠት የተጠቀመ የጥቂቶች ማወናበድ ነው።» በማለት ይደመድማል። እኔ የማይገባኝ፣ ስለምን በመንግስት የተደገፈው፣ ተቋማዊ የነበረውና «ብሔርተኞ» ጥቂት ጉልበተኞችን በሚቃመሙ የተፈጸሙት አብዛኛውን ጊዜ ኃይል የተቀላቀለባቸው «የመልስ ማወናበድ» አይወራም? በአብዛኛው የ20ኛው ክ/ዘ «አንድነት ወይም ሞት» በሚያቀነቅን ቡድን አጠቃላዩ የትምህርትና የመንግስት ተቋማት በብቸኝነት በቁጥጥራቸው ስር አልነበረም ወይ? አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የኮሌጅ ልጆች የገበሬውን ተቃውሞ በብሔርተኝነት ወደተሞላ አብዮታዊ ኃይል ለመለወጥና «ትክክለኛ» ሀሳብና ምርጥ ሰራዊት የነበራቸውን ለመድርመስ እንዴት ተቻላቸው የሚለውን ፐ/ሩ ጭራሽ አስቦታል? የ«ብሔር» ንቅናቄዎች ስለምን ከቡድን ትግል የበለጠ እድሜ ሊኖራቸው ቻለ? ብሔርተኝነትን «የቁንጮዎች ማወናበድ» በማለት ወድቅ ማድረግ በጣም ቀላል ነው። ሆኖም ግን፣ ባለፉት አርባ ዓመታት መሰል አካሄድ አለመርዳቱን የምናውቀው ነው።

«በማንኛውም መንገድ አንድነትን» የሚያቀነቅኑ ለመገንዘብ የሚያዳግታቸው፣ ተቃውሞን ለመደምሰስ ጉልበት፣ ንቀትና በአብዛኛው ጠባጫሪ አካሄድ ብሔርተኝነትን ከማጥፋት ይልቅ የሚያቀጣጥለው መሆኑን ነው። በብሔር ላይ የተመሰረተ ሕዝባዊ ተቃውሞን የወለደው የሆነ ውስብስብ ርዕዮተ-ዓለማዊ መሻት አይደለም፤ ማንነት ላይ የተመሰረተ ፖለቲካዊ ጭቆና፣ ኢኮኖሚያዊ ብዝበዛና ባህልን መደፍጠጥ እንጂ በማለት ተከራክሬያለሁ። በመሆኑም ኤርትራውያን፣ የትግሬ ህዝብ፣ የኦሮሞ ሕዝብና ሌሎች የየራሳቸውን ነፃ አውጪ ግንባሮች የደገፏቸው በአመራርነት ስፍራ የተቀመጡ ጥቂቶች ገበሬው የስታሊንን ስራዎች በማስተማር በጣም ውጤታማ በመሆናቸው ሳይሆን ሕዝቡ በማንኛውም መንገድ ጭቆናው እንዲያበቀለት ከፍተኛ ጉጉት ስለነበረው ነው።

ፕሮፌሰሩ ለብሔርተኝነት መጠናከር እጅግ ትልቅ ቦታ ለስታሊን እንዲሰጡ የሚያደርገው ይህን የብሔርተኝነትን መንስኤ አጣርሶ መረዳት ነው። ለምሳሌ፣ «እንደስታሊኒስታዊ ራዕይ፣ የብሔር ቡድን ነፃ መውጣት፣ ከሌሎች ቡደኖች ጋር አንድነት ከመመስረት ውጥን የሚቀድም ነው።» ይላል። የስታሊን ተማሪ አይደለሁም፣ ነገር ግን ስታሊንን የብሔርተኞች መልካም ወዳጅ አድርጎ የሚያስቀምጥ ምንም ጥናት አላጋጠመኝም። በተራኒው፣ የጆርጅያ ብሔርተኞች፣ የሰራተኞች ጥምረት ከቡርዥዋ

ብሔርተኛ ፍላጎቶች ቀዳሚነት አለው ብለው በጽኑ በማመናቸው ምክንያት የራሱን «ጆርጅያውያን» በመጨፍጨፍ በጣም ይታወቃል:: ፕሬፌሰሩ አንጋፋ የስታሊን ተማሪ እንደመሆኑ፣ እንዴት ይህን እውነታ አጣው? እውነታና አመክንዩ በመስኮት ሲወረወሩ፣ መመለሻ የሌላቸው ይመስላሉ:: ነገር ግን በተጨማሪ፣ ሌሎችን አጣርሶ መግለጽ ተቀባይነት አለው ምክንያቱም «አንድነተን በማንኛውም አማራጭ» የማስጠበቅ «ታላቅ ግብን» ያስጠብቃልና ነው:: እምነት ለማሸነፍ ሲባል ብቻ መስዋእት ሲሆን፣ ራሳችንን የተለየ አይነት ሁለተኛው መለስ ዜናዊ እናደርጋለን::

ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ ፕሮፌሰሩ ደጋግሞ የሚያነሳውና ግን በማስረጃ ለማስደገፍ ያልቻለው ሌላው ጉዳይ በግራ ዘመመ፣ በብሔርተኝነት፣ በየመገንጠል አቀንቃኝነት እና በትጥቅ ትግል መካከል ያለው ተጠማጅነት ነው:: ግራ ዘመመ ርዕዮተ-ዓለም «ለብሔር» በሔርተኝነት፣ ለመገንጠል ጥያቄና ለትጥቅ ትግል ማደግ ተጠያቂ ነው በማለት ይደመድማል:: ክርክር በግምቶች ብቻ ይካሄድ በነበረበት የዛሬ አርባ ዓመት በፊት ቢሆን ኖሮ፣ ይህ ንድፈ ሀሳባዊ ክርክር አሳማኝ ይሆን ነበር:: ነገር ግን አሁን እነዛ ጠቅላላ ግምቶችና ንድፈ-ሃሳቦች የተፈተኑ ናቸው:: አሁን ተጨባጭነት የሌላቸው ንድፈ-ሃሳቦችን መገንባት አላስፈላጊ መሆናቸውን ያሳዩ የተከሰቱ ጥናቶችን የመመልከት እድል አለን:: በዓለም የሌኒንን ፖለቲካ ያላቀነቀኑ ተገንጣይ ንቅናቄዎች ብዙ ናቸው:: ተገንጣይ ያልሆኑ ግራ ዘመም ንቅናቄዎች ነበሩ:: ያልታጠቁ በርካታ ተገንጣይ ትግሎች ነበሩ:: የተባለውን ተጣማጅነት የሚያስረዱ የተወሰኑ ምሳሌዎችን ልጥቀስ :-

- የቲቤትያውያን ንቅናቄ ሌኒስታዊም ሆኖ ወታደራዊ ያልሆነ ተገንጣይነት አራማጅ ነው:: በተመሳሳይ የካናዳ ኩቤክያውያን ተገንጣይ ንቅናቄ ሌላው አብሮ የሚጠቀስ ነው::
- የኮሎምቢያዊ «ፋርክ» ግራ-ዘመም የትጥቅ ትግል የሚያካሂድ ቡደን ቢሆንም መገንጠልን አያራምድም:: ለኔፓል ማኦይስት ንቅናቄም ይህ እውነታይሰራል::
- የሒንዱ «ቢጄፒ» ጽንፈኛ ቀኝ ክንፍ ብሔርተኛ ንቅናቄ ነው:: ቡድኑ አልታጠቀም፣ ግራ-ዘመምም አይደለም::
- አክራሪ ግራ-ዘመም ንቅናቄዎች የትጥቅ ትግል ሳያካሂዱ በበርካታ የላቲን አሜሪካ አገራት ስልጣን ለመያዝ ችለዋል::
- በአገር ውስጥ፣ ኢዲዩ ሶሻሊዝምን በመቃወም በትጥቅ ትግል የተሰማራ ፊውዳላዊ ፓርቲ ነበር:: ኢሕአፓ ግራ-ዘመም የትጥቅ ትግል ንቅናቄ ያካሂድ የነበረ ቢሆንም «የጎሳ» ብሔርተኝነትን አይቀነቅንም ነበር::

ብዙ መሰል ጉዳዮች ሊዘረዘሩ ይችላል:: በመሆኑም እውነታው ንቅናቄዎች፣ ተገንጣዮችም ሆኑ ወይም ያለውን መንግስት ለማሻሻል የሚፈልጉ፣ መሳሪያዎቻቸውን የሚያነሱት ጥያቄያቸውን ለማራመድ የሚያስችሏቸው መንገዶች ወይም መድረኮች የሉም ብለው በሚያስቡበት ወቅት ነው ወይም የትጥቅ ትግል ከማካሄድ የሚታቀቡት

ከትጥቅ ትግል ንጽጽሮሻዊ ስትራቴጂካዊ ብልጫ በማይመለከቱበት ወቀት ነው:: እናም፣ ፕ/ር መሳይ በጣም የወጣ ድምዳሜ ነው የሰጠው::

ወታደራዊ ትግልን ሕዝብን /አገርን/ በጉልበት ለመቆጣጠር ግድ ነው የሚል መርህ የለም:: ዝምባቡዌያውያንና ደቡብ አፍሪካውያን በኢትዮጵያ ወታደራዊ ሥልጠና አግኝተው የነበረ ቢሆንም አገሮቹን በኢትዮጵያ የበላይነት አላስገዛቸውም:: ሻዕቢያ በምዕራቡ ይደገፍ ነበር ሆኖም በጭራሽ ለፍላጎተቸው አልተንበረከከም:: የማኦ ቻይና በስታሊን ሶቭየት ሕብረት ትደገፍ ነበር:: እናም በትጥቅ ትግል ወቅት የውጭ እርዳታ ማግኘት በእጅ አዙር ወደ መያዝ ያደርሳል የሚለው የፕሮፌሰር መሳይ መከራከሪያ በህይወትና ተሞክሮ የተደገፈ አይደለም:: ኦነግ ከኤርትራ ጋር ስላለው ግንኙነት የሰጠሁት ትችት የተመሰረተው ከፊልሚያው አውድማ ካለው ርቀት የተነሳ የሚገኝ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታና ተጨባጭ የገንዘብና ሎጅስቲካዊ ድጋፈ የሌለ በመሆኑ ላይ መሆኑ ሊጠት የሚገባው ነው::

## ብሔርተኝነትን በአግባቡ አለመጠቀም
## መፍትሄ ወይስ ተቃውሞን ማፈን

ብሔርተኝነት እንደሚንተከተክ ውሃ ነው:: ማንቆርቆሪያው የአፈና ሥርዓትን፣ ሙቀቱ አፈናን እና ትነቱ ደግሞ ተቃውሞን ይወክላሉ:: እንዲያ ላለ ችግር መፍትሄ ለመስጠት ንቅናቄው ባለበት ደረጃ ወይም ማንቆርቆሪያው ምን ያህል የሞቀ ነው በሚለው ላይ ይወሰናል:: ለምሳሌ ገና ውሀው ተጥዶ መፍላት ሲጀምር፣ ሙቀትን በመቀነስ ወጥረቱን በማለዘብ የትነት መፈጠርን መከላከል ይቻላል:: የመጀመሪያው ደረጃ ካመለጠና ትነት መፈጠር ከጀመረ፣ ሙቀቱን ለመቀነስ ቀዝቃዛ ውሃ መጨመርንና ክዳኑን ክፍት ማድረግን ሊያካትት የሚችል የስትራቴጂዎች ጥምረትን መጠቀም ግድ ይላል:: ያን ደረጃ ካለፈ፣ ማንቆርቆሪያው ሊፈነዳ ወይ ክዳኑ ሊፈናጠር ስለሚችል ሁኔታውን መቆጣጠር አደጋች ይሆናል::

እንደአለመታደል፣ ብሄርተኝነትን የሚቃወሙ እንዲያ ያለውን ውጥረት በተቀናጀ ሥርዓት ከማስወገድ ይልቅ አብዛኛውን ጊዜ ግፊቱን ይጨምራሉ:: በእያንዳንዱ ደረጃ አፈናን በመጫን ግፊቱን ያባብሱታል:: ይህም ተቃውሞንና ጭቁኖችን የበለጠ ወደጽንፍ እንዲያመሩ ያደርጋቸዋል:: ይህ አብዛኛውን ጊዜ የሚከሰተው የቅዋሜን እምቅ አደጋና ኃይል ዝቅ አድርጎ ከመገመት ነው:: መሪዎች የደጋፊዎቻቸውን ትክክለኛ ችግር ገጸታ በሚያውቁበት ወቅት ውጤቱን ለመቆጣጠር በጭራሽ አይቻላቸውም::

ለምሳሌ ኤርትራን የኢትዮጵያ አካል አድርጎ ለማስቀጠል በጣም ከፍተኛ ኃብትና መስዋዕትነት ቢከፈልም ጥረቱ ፍሬ አልባ ነበር:: ንቅናቄውን ለመስበር የተካሄደው እያንዳንዱ ጥረት ተቃራኒ ውጤት ነበረው:: የኤርትራን ብሔርተኝነት ወደ ጉምነት ለመለወጥና የአገሪቱን የግዛት ወሰን ለማስጠበት መንግስቱ ኃ/ማርያምና የመንግስቱ «አብዮታዊት ኢትዮጵያ ወይንም ሞት» ደጋፊዎች ለ«ፌዴሬሽን» ሊደራደሩ ይቻላቸው

ነበር፡፡ እና ያም ፕሮፌሰር እንዳለው እንደ«ሽንፈት» የሚወሰድ አልነበረም የሚሆነው፡፡ ሊሆን የሚችለው የማንኛውም ወገን ያልተሸነፈበትና ያላሸነፈበት ሁኔታ ነበር፡፡ እርግጥ፣ በ1981 ሻዕቢያ ለእንደዚያ ያለ ድርድር አንድ እቅድ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ሻዕቢያ «የሕዝብ ውሳኔ» ድርድር እያነሳ ያለበት ምክንያት ወታደራዊ አቅሙ በመዳከሙ ነው በሚል በደርግ ተቀባይነት አልነበረውም፡፡ ፖለቲካ የእከከኝ ልከክህ (የመቻቻል) አርት እንጂ ደምቀው የሚሰሙ መፈክሮች ስፍራ እንዳይደል ፕሮፌሰሩ በደርግ አገዛዝ ከቆየባቸው ዓመታት ሊገነዘብ በተገው ነበር፡፡

# ኢትዮጵያ ዳግም ከፍተኛ የምግብ እጥረት ተጋርጦባታል

***በማይክ ዉልድሪጅ***

አንድ ሚሊዮን የሚገመቱ ሰዎችን ሕይወት ቀጥፏል ተብሎ የተገመተው የ77ቱ ድርቅ ከተከሰተ ከ25 ዓመታ በኋላ በአሁኑ ወቅት ምርት ያልሰጡ ሰብሎች ኢትዮጵያ የህዝቧ ለረሀብ ያለውን ተጋላጭነት ለመቀነስ እያደረገች ባለው ትግል ላይ ከፍተኛ ግፊት እያሳደረበት ይገኛል፡፡

በቀጠናው ከሚገኙ ሌሎች አገሮች ጋር ኢትዮጵያ የምትጋራው የወቅቱ የምግብ እጥረት፣ በተጨማሪ ኑሮአቸውን በግብርና ላይ የመሰረቱ ቤተሰቦች ሊደርስባቸው ከሚችለው ረሀብ ለመታደግ ሊሰጥ የሚገባው ትኩረትና ኃብት ለሌላ አላማ እንዲውል የማስደረግ አደጋም የጋረጠ ነው፡፡

በዚህ በደቡብ ኢትዮጵያ በሚገኘው ወላይታ 12 ወረዳዎች፣ በሁለቱ ያለፈው የበቆሎ ሰብል ሙሉ በሙሉ ፍሬ እንዳልሰጠ ባለስልጣናት ይናገራሉ፡፡ እንደባለስልጣናቱ፣ የተቀሩት ወረዳዎች በአንፃሩ የሚሻሉ ናቸው፡፡ ሆኖም 1.6 ሚሊዮን ሕዝብ ባላት ወላይታ ውስጥ የሚከሰት የትኛውም ዓይነት የምግብ እጥረት ከሕዝቡ ብዛት አንፃር ሲታይ ሊያደርስ የሚችለው አደጋ ከፍተኛ ነው፡፡

የወላይታ ዋና ከተማ ከሆነችው ሶዶ እምብዛም ከማይርቀው ከፍተኛ ጉዳት በደረሰባት ዱጉና ፋንጎ ወረዳ ውስጥ ያሉት አቶ ያንጋጉ ቡንጃ፣ ፍሬ ያለፈራውና የደረቀበት በቆሎ ለቤተሰባቸው ምን ማለት እንደሆነ ያናገራሉ፡፡

አርባኛ ዓመቱን የያዘው ያንጋጉ የእድሜ ክልላቸው ከአራት ወር እስከ 18 ዓመት ያሉ ስምንት ልጆች አሉት፡፡ «ምንም ነገር የለንም፡፡ ትልቅ ችግር ነው ያለብን፡፡» የሚለው ያንጋጉ፣ ያለፉት ሶስት አመታት ተመሳሳይ እንደነበሩ ይናገራል፡፡ ቅጥር የጉልበት ሰራተኛ በመሆን ሌሎች ስፍራዎች በመስራት ቤተሰቦቹን ለመርዳት ቢሞክርም እንዳልተሳካለት ይናገራል፡፡ ልጆቹም ክብደታቸው እየቀነሰ ነው፡፡ ሁለቱ ታመው ነበር፡፡ በልጆች ላይ የሚደርሰው ህመም የጠቅላላው የማሕበረሰቡ ችግር እንደሆነም ይገልፃል፡፡

እህል ሊያገኝ የሚችልበት ብቸኛው ሌላ መንገድ ከሌሎች መበደር ቢሆንም አበዳሪዎች ወለድ ይፈልጋሉ፡፡ «በዚህ ሁሉ ጊዜ እግዚአብሔር ነበር ሲመግበን የቆየው፡፡» ይላል ያንጋጐ፡፡

ወደ ወላይታ በሚወስደው መንገድ፣ በረዥም ጊዜ ድርቅና አልፎ አልፎ በሚዘንብ ዝናብ ምክንያት ምርት ያልሰጡ ሌሎች በጣም ብዙ የእርሻ መሬቶች ይታያሉ፡፡ ሊገርም በሚችል መልኩ ጎን ለጎን በሚገኙ ማሳዎች በአንዱ የበቆሎ ሰብል ጥሩ ምርት የሚሰጥ ይመስላል፡፡ የሰብሎች ምርት አለመስጠትና ለከብቶች ግጦሽ የሚሆን በቂ መኖ አለመኖር የኢትዮጵያ መንግስት 6.2 ሚሊዮን ሕዝቡን ለመመገብ እንዲቻለው የተጠበቀውን የአስቸኳይ የምግብ እርዳታ ጥሪ እንዲያደርግ በቂው ነበሩ፡፡

ይህ የኢትዮጵያ መንግስት ጥሪ የተደረገው የተ.መ.ድ የምግብ ኤጀንሲ በመላው ዓለም በርካታ የተራቡ ሰዎች መኖራቸውንና ከመቼውም ጊዜም በበለጠ አነስተኛ የምግብ እርዳታ መኖሩን ባሳወጀበት ወቅት ነው፡፡

በ70ዎቹ በኢትዮጵያ የተከሰተው አስከፊ ድርቅ የአገሪቱ ታሪክ መሆኑን የአገሪቱ ባለስልጣናት ቢቀበሉም፣ ከዚያ ወቅት የተቀረጸው የድርቅ ገጽታ የወደፊቷ ኢትዮጵያ የምትታይበት መስታወት ግን መሆን የለበትም በሚል ይከራከራሉ፡፡

የመንግስት ቃል አቀባይ የሆኑት አቶ በረከት ስምኦን የግብርና ምርታማነትን ለማሻሻል፣ ውሃና አፈር በመጠበቅና በአጠቃላይ የአየር ንብረት ለውጥ ወጤት አካል የሆኑትን በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ድርቆችን በይበልጥ መቋቋም ይቻላቸው ዘንድ እየተደረጉ ስላሉት ጥረቶች ይናገራሉ፡፡ በርካታ ገበሬዎች ከመስኖ የሚገኝ ትርፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል የጥረቶቹ አካል ነው፡፡

ከፍተኛ ጉዳት በደረሰበት የወላይታ አካባቢ የሚገኘው አቶ ያንጋጐ የተወሰኑ አርሶ አደሮች አሁን ማሳዎቻቸውን በመስኖ ለማልማት የውሃ መሳብያ ማሽኖች ቢኖራቸውም እርሱ ግን አቅሙ እንዳልፈቀደለት ይናገራል፡፡ እና የበቀሎ ሰብሉ ምርታማ ያለመሆኑ ሲታይ ወደፊትም የማሽኑን የመግዛት አቅም የሚኖረው አይመስልም፡፡

ሰብላቸው ምርታማ የሆኑትን ገበሬዎች ለመደገፍ በሚቀጥሉት ሳምንታት የሚተገበሩት የተቀመጡ ስትራቴጂዎች ብቻ ሳይሆኑ በተመጣጠነ የምግብ እጥረት አስከፊ ጉዳት የደረሰባቸውንም ሕፃናት ሕይወት ለመታደግ አዳዲስ አካሄዳችንም ጭምር ነው፡፡ የአበበች አዳቦ የአንድ ዓመት ዕድሜ ወንድ ልጇ በዚህ መልኩ እንክብካቤ እየተደረገለት ይገኛል፡፡ የህክምና ሰራተኛ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ውጤት ነው ያለው ጠበሳ በልጁ ጭንቅላት ላይ ይገኛል፡፡ አበበች ተስፋዬ ደግሞ የአራት ዓመት ልጇን በእጆቿ አቅፋ ይዛዋለች፡፡ ቀጫጭን እግሮቹ እንዳሉ ቢሆኑም እየተሻሻለ ነው የሚል ስሜት አላት፡፡ ሁለቱንም ልጆች አቅመ ቢስ ያደረጋቸው የምግብ እጥረት መሆኑን ወላጅ እናቶቻቸው ይናገራሉ፡፡

*/ማይክ ዉልድሪጅ በቢቢሲ የዓለም አቀፍ ጉዳዮች ዘጋቢ ነው፡፡ /*

# የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት በይርጋ ቀሪ አይሆንም!

## - መርሆው ይኼው ነው! -

ማርክ ትዌይን ምን አለ፣ «there is no end to the laws, and no beginning to the execution of them»:: ምን ማለቱ መሰላችሁ ይህ ሰው፡- «ሕጉስ አለ፤ (የህግ ችግር የለብንም)፤ ችግራችን ሕግን ሥራ ላይ ማዋል ነው» ማለቱ ነው:: አንድ ሌላ የአሜሪካ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ጉዳዩን በአንክሮ አጢኖ በበኩሉ፡- «የመጨረሻ ፍርድ ቤት ዳኛ ማለት የበላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ማለት እንጅ የበላይ አዋቂ ማለት አይደለም» ማለቱንም በተባራሪ ሰምቻለሁ:: ዳኛው ትህትና ያለውና ጉዳዩን በአግባቡ አስተውሎ ልኩን በትክክል ለመናገር የደፈረ ነው:: ጌታ አምላክ የዚህን ዳኛ ትህትና ያላብሰን! ብለን ይህንን መጣጥፍ እንቀበላለን:: ፈጣሪ አምላክ ትህትና ካላጎናፀፈን ግን ላንቀበለው እንችላለን::

እንደምታስታውሱት በዚህ አምድ ስለዳኛና የዳኝነት ሥራም የገባንን ስንገልጥ ቆይተናል:: ይህንን በዚህ ጉዳይ ሲጻፍ የነበረውን የተመለከታችሁ ሁሉ ታስተውሉታላችሁ:: ለምሳሌ አንዱን ጉዳይ ለማስታወስ ያህል፡- ዳኛ በባለጉዳይ የቀረበለትን ፈተና ራሱ የሚያርም የሕግ ተማሪ መሆኑን ጠቅሰን ነበር:: ምን ማለት ነው፣ ከሳሽ፡- ይህንን ችግር (ፈተና) ለርስዎ ለተከበሩ ዳኛ አቅርቤያለሁና ክቡርነትዎ እኔ የምሻውን መልስ በመምረጥ ያርሙልኝ ሲል ፈተናውን ያቀርባል:: ዳኛው በበኩላቸው «ለቀረበልኝ ፈተና እርማት ከመስጠቴ በፊት ባለጋራህን ልጥራና የሱንም ምርጫና አስተያየት ልስማ» ይላሉ:: አብዛኛውን ጊዜ ግራ ቀኙ በዚህ ዓይነት ሂደት መፍትሔው (መልሱ) ይሄ ሊሆን ይገባል፣ የለም ይሄ ነው ሊሆን የሚገባው! ሲሉ ይፋለሙና በመጨረሻ ክቡር ዳኛ መልሳቸውን ይመርጣሉ:: ከዚያም የመረጡትን መልስ ፍርድ ሲሉ ያውጃሉ:: በቃ ዳኝነት ማለት በመሠረቱ ይሄ ነው:: ይሄና ይሄ ነው በማለትም ልታጎሉት ትችላላችሁ::

ስለዚህ ዳኛ ፈተና ሲመልስ በግራ ቀኙ ተሟጋች እየታገዘና እየተመከረ ስለሆነ የዳኝነት ፈተና በመሠረቱ ቀላል ፈተና ነው ማለት ይቻላል:: ፈተና ከከበደም ይከብዳል የሚባለው በሕግ ት/ቤት እንጅ በፍርድ ቤት አይደለም:: ምክንያቱም በሕግ ት/ቤት አማካሪህ አንተና አንተ ብቻ ስለሆንክ እዚያ ቦታ ጣር ይኖረው ይሆናል:: በገሀዱ ዓለም የፍርድ ሂደት ግን ታግዘህ ስለምትመልስ ፈተና ይከብዳል አይባልም:: ስለዚህ በገሀዱ የፍርድ ሂደት ዳኛ ማለት «መልስ ቀማሽ» ነው ማለትም ይቻላል:: ከተቀመጡ መለኪያዎች አንጻር ይኼኛው መልስ የሚመረጥ ነው በማለት የጣመውን መብል (መብት) ለባለጉዳዩ የሚያቀዳጅ (personnel) ነው - ዳኛ::

በዚህ በመልስ ቀመሳ ሂደት ታዲያ ብዙ ጊዜ የቅምሻ ማጣጣም ባላጋራዎች አሉ፡፡ ይህም የኔ መልስ ይመረጥልኝ የሚል የመደለያ ባላጋራ ቀማሹን ዳኛ የተሳሳተ መልስ እንዲሰጥ ያስገድዳሉ፡፡ ሌሎች ባላጋራዎች ያሉ ቢሆንም እነሱን ሁሉ ለመዘርዘር አሁን ጊዜ የለንም፡፡ በነገራችን ላይ ዳኛን በቀመሳ ምርጫው ከሚያገለግሉት መሣሪያዎች መካከል የሕግ ሥነ-ጽሁፎችም ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ዳኛው ለተመደበበት የፍርድ ችሎት የሚመጥን ንባብና ጠቅላላ ዕውቀት ከሌለውም የደከመ የምርጫ አካሄድ ውስጥ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ዕወቀቱ የሌለው ግን ጮሌ ጠበቃ ሁሉ ንግግሩን በማሳመር ዳኛውን ሊያወዛውዘው ይችላል ማለት ነው፡፡፡፡

አምና ቤተሰብ ችሎት ሰርቷል፤ ዘንድሮ ደግሞ የወንጀሉን ችሎት ይሞክር የሚል አመዳደብም ፍትህ እንዲዛባ መዋጮው ከፍ ያለ ነው፡፡ ለዚህም ነው የዳኝነት «specialization»አግባብነቱ የላቀ የሚሆነው፡፡

ከርዕሳችን ወጣ ያልን በመምሰል የደከምነው አንድ ነገር ለማየት በመፈለግ ነው፡፡ በማይንቀሳቀስ ንብረት ጉዳይ ይርጋ አለ! የሚለው አቋም በዚህ ጽሁፍ የአማካሪነት ሚና ሊታረም ይገባል የሚለውን በአጭሩ ለማሳሰብ ነው በብርቱ የደከምነው አሁን ግን ቀጥታ ወደ ሕጉ፡-

በሥራ ላይ ባለው የአገሪቱ የፍትሀ ብሔር ሕግ ከቁጥር 1188-1192 ድረስ ሀብትነት ስለሚቀርበት ሁኔታዎች በግልጽ ተደንግጓል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች በፍትሀ ብሔር ሕግ ስለንብረቶች በተደነገገው በአንቀጽ (Title) 7 በክፍል 3 ስር የተደነገገ ነው፡፡ አንቀጽ (Title) 7 ሀብት ስለሚገኝበት፣ ሀብትነት ስለሚተላለፍበት ባለሀብትነት ስለሚቀርበት ሁኔታና ስለሀብትነት ማስረጃ ሁኔታ የተደነገገበት ከባለሀብትነት ጋር በተያያዘ እጅግ አስፈላጊ አንቀጽ ነው፡፡

ይህ አንቀጽ ወይም (Title) 7 የተባለው የሕጉ ክፍል ሀብትነት እንዴት ነው ቀሪ የሚሆነው ስለሚለው መጠይቅ ግልጽ ምላሾች የደነገገ ክፍል አለው፡፡ ይህም ከፍ ሲል እንደጠቀስነው በክፍል 3 ከቁጥር 1188-1192 ድረስ የተደነገገውን የያዘ ነው፡፡ በዚህ ክፍል በቁጥር 1188 ላይ የአንድ ንብረት ህልውናው ሲጠፋ ሀብትነት እንደሚቀር ተደንግጓል፡፡ ይኸውም ለምሳሌ ቤት ኖሮ ያ ቤት በተለያየ ምክንያት ቢወድም ሀብትነት ይቀራል ማለት ነው፡፡ ሌላው ሀብትነት የሚቀርበት ምክንያት በፍ/ሕ/ቁ 1189 መሠረት ሀብትነቱ ለሌላ ሲተላለፍ ወይም ለሌላ ሰው ሲሆን ነው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለሌላ እንዴት ነው የሚተላለፈው? የሚለውን ስንመለከት በውል ወይም በኑዛዜ መሠረት መሆኑን «ሀብትነትን ስለማስተላለፍ» በሚለው የዚሁ ሕግ ክፍል 2 አንቀጽ 1185 ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ተላለፈ ለማለት በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ መመዝገቡ አስፈላጊ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ውሉን በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ማስመዝገብ ለሕጋዊነቱ አስፈላጊ መመዘኛ መሆኑንና ይህ ካልተሟላ ተላለፈ ማለት አለመቻሉን ይህ ቁጥር በአጽንኦት የሚደነግግ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በውል ወይም በኑዛዜ ማስተላለፍ ይህን የመሰለ ገጽታ (ፎርም)

ሊኖረው የሚገባ ሲሆን፣ ቁጥር 1189 በሕግ መሠረት ሲገኝ («acquired» ሲደረግም) የሚል ነገር አለው::

የማይንቀሳቀስ ንብረት በሕግ ሊገኝ የሚችለው እንዴትነው? ብለን ስንጠይቅ ለምሳሌ ንብረቱ ለህዘብ አገልግሎት ቢፈለግ በሕግ መሠረት ሀብትነቱ ይቀራል:: ሌላው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት የሚቀረው በፍ/ሕ/ቁጥር 1168 መሠረት ለ15 ተከታታይ ዓመታት ለአንድ መሬት ባለይዞታነት ግብር ይከፍሉ የኖሩ እንደሆነ ነው:: ይህም በእንግሊዝኛ «usucaption» (መሬት በመያዝ መብት ማግኘት ዓይነት) የሚባለው ነው::

ይህንን የፍ/ሕ/ቁጥር 1168 የአማርኛ ቅጅ ከእንግሊዝኛው ቅጂ ጋር አገናዝበው ሲያነቡት የሚሰጠው ግንዛቤ «ዩዙካፕሽን» መሬትን የተመለከተ ድንጋጌ ስለሚሆን ድንጋጌው መሬት በግል ሀብትነት በሚያዝበት ዘመን የተደነገገ በመሆኑና አሁን መሬት የግል ሀብት መሆኑ በማቆሙ ምክንያት ድንጋጌው ዋጋ ያጣ መሆኑን ነው መመልከት የሚቻለው:: በግልጽ ሳይሆን በዝምታ (በውስጠ ታዋቂ) የተሻለ ድንጋጌ ይመስለናል:: አሁን በመንግስት መሬት ላይ ግብር በመገበር ባለሀብት የሚኮንበት አግባብ አለ ማለት አይቻልም:: ይኼ የዩዛካፕሽን ድንጋጌ ሀብትነት ስለሚገኝበት ክፍል ላይ የተደነገገ ስለሆነ በዩዛካፕሽን መሬት ይገኛል ማለት ባለንበት ጊዜ ያበቃለት ጉዳይ እንደሆነ ነው የገባኝ::

ስለዚህ ሀብትነት በውል ወይም በሕግ መሠረት ከሚተላለፍበት አግባብ ውጭ የማይንቀሳቀስ ንበረት ሀብትነት የሚቀርበት ሌላው አግባብ ከርስት መዝገብ (register of immovable property) መሰረዝ ነው:: የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ከመዝገበ ሲሰረዝ ሀብትነቱ ይቀራል:: ይህ እንግዲህ በቁጥር 1190 የተደነገገ ነው::

በቁጥር 1191 ላይ በሚንቀሳቀስ ንብረት ጉዳይ በማያጠራጥር ሁኔታ «ይህንን ንብረት አልፈልገውም» በማለት ሀብትነት ሊቀር መቻሉ ተደንግጓል:: ይኼ ግን ለሚንቀሳቀስ እንጅ ለማይነቀሳቀስ ንበረት ጉዳይ የሚሰራ አይደለም:: ስለሆነም ለምሳሌ በየካ ክ/ከተማ፣ በቀበሌ ይኼን ያህል ያለውን የቤት ቁጥር ይኼን ያህል ቤት አልፈልግም በማለትህ ባለሀብትነትህ አይቀርም:: አልፈልግም ውሰዱልኝ ብለህ ብታውክ እንኳ ምናልባት መንግስት ከሚያስርህ በቀር ሀብትነቱ አይቀርብህም::

ሀብትነት የሚቀርበት የመጨረሻው ምክንያት የይርጋ ዘመን ሲሆን፣ ይህም በፍ/ሕ/ቁጥር 1192 ላይ ተደንግጓል:: ታዲያ በዚህ ቁጥር ላይ ይርጋ በግልጽ የተደነገገው ለተንቀሳቃሽ ንብረት እንጅ ለማይንቀሳቀስ ንብረት አይደለም:: በዚህም ላይ እንደተደነገገው አንድ የሚንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት ሀብት የሚገኝበትን ወይም ሀብት መሆኑን ባለማወቅ 10 ዓመት ያልተገለገለበት ከሆነ ሀብትነቱን የሚያጣ መሆኑ ተደንግጓል::

ከዚህ ሌላ «Special» የሆነው የንብረት ሕግ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት በይርጋ ቀሪ ይሆነ ዘነድ አልደነገገም:: በመሠረቱ ሕግ አውጭው እንደዚህ መደንገግም አይችልም:: ሕግ አውጭው ከሕግ መሠረታዊ ጽንሰ ሀሳብ ተነስቶ መደንገግ የሚገባው

ቢሆን ኖሮ የተንቀሳቃሽ ንብረትን ባለሀብትነት በተደነገገበት አግባብ የማይንቀሳቀሰውንም ንብረት ባለሀብትነት በደነገገ ነበር:: ከፍ/ሕ/ቁጥር 1192 በፊት ወይንም በኋላ ወይም ምናልባት ባንድነት ለማይንቀሳቀስ ንብረትም ይርጋን ከመደንገግ የሚከለክለው ነገር ባልነበረ:: ስቶም ከሆነ ዘግይቶ በማሻሻያ የሚደነገግበት አግባብ ይኖር ነበር:: ግን ይኼ አልተደረገም፤ ያልተደረገውም ሆን ተብሎ ይመስለናል:: በንብረት ሕግ ባለቤትነትና ሀብትነት የመቅረት አግባብ ይርጋ ሆን ተብሎ የተወገደ መሆኑ ሊስተዋል ይገባል::

ሕጉ በባለሀብትነት መቅረት ጉዳይ ግልጽ ያለውን የሕግ አውጭ አቋም እያንፀባረቀ በአሰራር ግን በፍ/ሕ/ቁጥር 1845 የተደነገገውን ይርጋ በካቦ በመጎተት ዓይነት ከቁጥር 1192 በኋላ ሲሰፉት ይታያል:: በበኩሌ ይኼ ጉተታ አግባብ አለመሆኑን ከላይ አስረድቻለሁ:: አሁንም ሌላ ነገር ላክል እችላለሁ::

1845 ስለይርጋ ጊዜ የሚደነግግ ሲሆን ይህ ሕግ እንደዚህ ሲል ይጀምራል፡- «ሕግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር ...»:: ድንጋጌው እንዲህ መጀመሩ ምን ለማለት ፈልጎ ነው፡- ሕግ በሌላ አኳኋን ከደነገገ ቁጥር 1845 ተፈጻሚ አይሆንበትም ማለቱ ነው:: ከላይ እንዳየነው የንብረት ሕግ በሌላ አኳኋን «ለማይንቀሳቀስ ንብረት ይርጋ አልተፈለገም» ብሎ በዝምታ ስለደነገገ ቁጥር 1845 የንብረት ሕግን በተመለከተ ሥራ ላይ መዋል አልችልም ብሎ በንብረት ሕግ ጉዳይ «ድምጽ አይሰጥም!» ማለት መሆኑ ነው::

የማይንቀሳቀስ ንብረት በመሠረቱ በይርጋ የማይታገድበት የሕግ ንድፈ ሀሳብ (Theory) ምንድን ነው? ብሎ መጠየቅ በማይንቀሳቀስ ንበረት ይርጋ አግባብ አለመሆኑን ያሳየናል:: እንደሚታወቀው የማይንቀሳቀስ ንብረት በእንግሊዝኛው «Real property» ወይም «Real estate» ነው የሚባለው:: «Real» ማለት ለህዝብ አገልግሎት ዓላማ ካልሆነ በቀር ከፈቃድ ውጭ ከእጅህ የማይወሰድ ሀብት ማለት ነው:: የዜግነት መሠረት ከሚገለጥባቸው መታያዎች አንዱ የማይንቀሳቀስ ንብረት ነው:: በአንድ አገር የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዝ ማለት አገሩን ካቋቋመው የመሬት ክፍል ተጋሪ መሆን ማለት ነው:: ይህ መብት በመሠረቱ ለዜጋ እንጂ ለእንግዳ የተፈቀደ አይደለም:: የአንድን አገር መሬት በመሰረቱ ዜጋው ካልተቆጣጠረው በውጤቱ አገሬ ነው የሚል አስተሳሰብን የሚያጠፋ ይሆናል:: ስለዚህ «Real property» በመሰረቱ በበጎ ፈቃድ በባለሀብቱ የሚተላለፍ እንጅ አደራ ጠባቂ ሁሉ 10 ዓመት ቆይቼበታለሁ በሚል የሚወርሰው አይደለም:: በማይነቀሳቀስ ንብረት ይርጋ ጉዳይ የብዙ አገራትን አስተሳሰብም መረዳት ይበጃል:: ደህና ቆዩን::

# ተጠየቅ

ይህ ዓምድ የህብረተሰብን እሮሮ መነሻ በማድረግ የተለያዩ ተቋማት የስራ እንቅስቃሴን ይዳስሳል

# «የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ሪፖርት የኢትዮጵያን የሙስና ገጽታ አያሳይም»

አቶ ጌታቸው ጨርቆስ
በፌዴራል የስነምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን
የህዝብ ግንኙነት ጊዜያዊ ኃላፊ

*በኤልያስ ገብሩ*

ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የተሰኘው አለም አቀፍ ተቋም በ2008/9 ባወጣው ሪፖርት መሰረት አገራችን ሙስናን በመዋጋት በዓለም አቀፍ ደረጃ በ126ኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧታል:: በዚህ መነሻነት በፌዴራል የስነምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የህዝብ ግንኙነት ጊዜያዊ ኃላፊ የሆኑት አቶ ጌታቸው ጨርቆስ ስለ ኮሚሽኑ ስራዎች፣ ስለ ሙስና ወንጀሎች የክስና የፍ/ቤት ሂደት እንዲሁም በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ከአውራምባ ታይምስ ጋር ቃል ምልልስ አካሂደዋል:: እኛም የአቶ ጌታቸውን ቃለ ምልልስ ከአንዳንድ መረጃዎች ጋር በማጣቀስ እንዲህ አቅርበነዋል::

## የሙስና ወንጀሎች በአጠቃላይ ምን ይመስላሉ?

በሀገራችን ዘርፈ ብዙ የፀረ ሙስና እንቅስቃሴዎች እየተካሄዱ ይገኛሉ:: ከዚህ አንፃር በተሻሻለው የሀገሪቱ የወንጀል ህግ ውስጥ የሙስና ወንጀሎች ከዚህ በፊት በተለየ ሁኔታ ግልጽነት ባለው መልኩ መካተታቸው ተጠቃሽ ነው:: ከዚህ ቀደም በነበሩ የአገሪቱ የወንጀል ህጐች የሙስና ወንጀሎች ያልተሟላ፣ የነበሩትም ተበታትነው የሚገኙ ና የሚጥሉት ቅጣትም ለአንዳንዶቹ ወንጀሎች የሚመጥን አልነበረም:: በተሻሻለው የወንጀል ህግ ቁጥር 414/96 አንቀጽ 404 የሙስና ወንጀል ምን ማለት እንደሆነ በግልጽ የተመለከተ ሲሆን የሙስና ወንጀሎችም በተቻለ መጠን የተሟሉ እንዲሆኑና በአንድ አካባቢ እንዲሰባሰቡ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል:: በወንጀል ህጉ የተደነገጉት የሙስና ወንጀሎች ከብዙ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው:: በስልጣን ያለአግባብ መገልገልና በስልጣን መነገድ የመንግስትን ሥራ በማያመች አኳኋን መምራት (የጥቅም ግጭት)፣ ከባድ የዕምነት ማጉደል ወንጀል፣ በስራ ተግባር ላይ የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል፣ አደራ በተሰጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ፣ በህገ ወጥ መንገድ መሰብሰብ ወይም ማስረከብ፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልና መስጠት፣ ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት፣ በሌላው ስልጣን መጠቀም፣ ዋጋ ያለውን ነገር ያለ ክፍያ ማግኘት፣ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብና ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀል መርዳትና ማቀባበል ናቸው::

## የፌዴራል የፀረ ሙስና ኮሚሽን የሚከታተላቸው ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?

እንደ አቶ ጌታቸው ገለፃ ከሆነ ኮሚሽኑ በዋነኝነት ትኩረት ሰጥቶ የሚከታተላቸው የሙስና ጉዳዮች ሦስት አይነቶች ናቸው፡፡ ፒቲ፣ ግራንድና ፖለቲካል ኮራፕሽን (Corruption) ሲሆኑ ፒቲ ኮራብሽን ጥቃቅን የሙስና ወንጀሎች ናቸው፡፡ ሀገራዊ ጉዳታቸውም አነስተኛ ነው፡፡ ግራንድ ኮራፕሽን ሀገራዊ ጉዳቱ ትልቅና ከፍተኛ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡ ፖለቲካል ኮራብሽን ከፖለቲካ ጉዳዮች ጋር የተያያዙትን ሲይዝ ምርጫንም ያጠቃልላል፡፡ ኮሚሽኑ ግን ይበልጥ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራበት የሚገኘውና የሚከታተለው ግራንድ ኮራፕሽንን ነው፡፡ የመጀመሪያውን አይነት የሙስና ወንጀሎች በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት ይመለከቷቸዋል፡፡

አቶ ጌታቸው አክለውም በሀገር፣ በመንግስትና በህብረተሰብ ውስጥ ከባድ ተጽዕኖን በሚፈጥሩ የሙስና ጉዳዮች ላይ በንቃት እየተከታተሉ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ በጉቦ፣ በስልጣን ያለአግባብ መጠቀምና ብልሹ አሰራር የሚፈፀሙ ወንጀሎች ተደራራቢ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡ ለምሳሌ ያህልም በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን መ/ቤት ውስጥ ከጨረታ ጋር በተያያዙ ጥቆማ ደርሶን የጨረታ አወጣጡን ስናየው ክፍተት ስለተገኘበት አካሄዱ እንዲስተካከል በማድረግ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር እንዲድን አድርገናል በማለት በአንዳንድ የአሰራር ዘዴዎች፣ (ሲስተሞች) ለሙስና እንደሚያጋልጡ ገልፀዋል፡፡ ኮሚሽኑ አንደዚህ አይነት ነገሮች ሲገጥሙ ብልሹ አሰራርን ማስወገድ፣ ሙስና ተፈጽሞበታል የተባለበትን ቦታ መርምሮ መክሰስና ለውሳኔ ማብቃት በሙስና የተገኘ ሀብት ካለም ማስመለስ እንደሚጠበቅበት አብራርተዋል፡፡ ለዚህም ድጋፍ እንዲሆን በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ውስጥ የስነ ምግባር ክበባትና በፌዴራል መ/ቤቶች ውስጥ የስነምግባር መኮንኖች እንዳሉም አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

## የጥቆማ አቀራረቡ ምን ይመስላል? ኮሚሽኑስ ጥቆማዎችን እንዴት ይመዝናቸዋል?

የሙስና ድርጊት ተፈጽሟል ወይም ሊፈፀም ታቅዷል ተብሎ ሲታሰብ ስም ገልጾ ወይም ሳይገልፁ በተለያዩ ዘዴዎች መጠቀም የሚቻል ሲሆን ለኮሚሽኑ ጥቆማ ለማቅረብ የሚፈልጉ ጥቆማ አቅራቢዎች በጉዳዩ ላይ ያላቸውን መረጃ በተቻለ አቅም ብዙ ነገርን ሊገልጽ በሚችል መንገድ አደራጅተው ቢያቀርቡ ይመረጣል፡፡ ማንኛውም የሙስና ድርጊት፣ ከባድ የስነምግባር መጣስንና ብልሹ አሰራርን የተመለከተ መረጃ የሚሰጥ ሰው ወይም ደርጅት ጠቋሚ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ እንዲሁም ጠቋሚው ጥቆማውን በአካል በመገኘት፣ በጽሁፍ ወይም በቃል፣ በፖስታ፣ በስልክ፣ በፋክስ ወይም በኢ-ሜይል ለኮሚሽኑ በተጨማሪም በአዲስ አበባ አስተዳደር ስር በሚገኙ ክፍለ ከተሞች በተቀመጡ የጥቆማ መስጫ ሳጥኖችና እንደአስፈላጊነቱ በሌሎችም ኮሚሽኑ በሚያዘጋጃቸው ሳጥኖች ወይም ተመሳሳይ ዘዴዎች መጠቀም ይችላል፡፡ ጥቆማዎችም በትክክለኛ የጥቆማ አቀራረብና መረጃ እንደሚመዘኑ አቶ ጌታቸው ይገልፃሉ፡፡

# በኮሚሽኑ በኩል የተጠናቀቁ የምርመራና ቅጣት የተላለፈባቸው መዝገቦች እና ውሳኔ የሚጠባበቁ ትልልቅ ጉዳዮች

ምርመራቸው በ1999 በጀት ዓመት ተጀምሮ በ2000 በጀት ዓመት የተጠናቀቁ ፋይሎች በሚል የፌደራል የስነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የ2000 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በስልጣን ያላግባብ መገልገል፡፡ የመንግስት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት፣ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ እምነት ማጉደል፣ ምዝበራ፣ ጉቦና ቂም በቀል በሚሉ የወንጀል አይነቶች የፋይል ብዛት 58 ሲሆን የተጠርጣሪዎች ብዛት 259 ነው ያልተገባ ጥቅም /ከመንግስት የተመዘበረ የገንዘብ መጠን 462,270,631 ነው፡፡ በ2000 በጀት አመት ምርመራቸው ተጀምሮ የተጠናቀቁ ፋይሎች ብዛት 63 ሲሆኑ 296 ተጠርጣሪዎችን በመያዝ 2,180,311,361 የብር መጠንን ከመንግስት መዝብረዋል፡፡ የስራ ዘርፎችም ገቢዎችና ፋይናንስ፣ መሰረተ ልማት፣ መሬት አስተደደርና ልማት፣ ጤና፣ አገልግሎት አሰጣጥ፣ ትምህርት የፍትህ አካላትና ሌሎችም ናቸው፡፡ በዚሁ በጀት ዓመት ቅጣት የተላለፈባቸው 41 መዝገቦች ሲሆኑ 105 ግለሰቦች ላይ ከ1 ዓመት ቀላል እስራት እስከ 18 ዓመት ጽኑ እስራትና ከ200-20000 ብር የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ተወስኖባቸዋል፡ እንዲሁም ውሳኔ ከሚጠባበቁት ከፍተኛ የሙስና ወንጀሎች መካከል በቴሌኮሚኒኬሽን ላይ ከሳተላይት ጋር በተገናኘ በተከሰሰው ደቡብ ኮሪያዊ ላይ ያለው የፍርድ ሂደት፣ የወርቅ ማጭበርበርና ከኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ህገ ወጥ የመሬት ወረራና ሽንሽና የሙስና ወንጀሎች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ጉዳይም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን ሳንቀበል ቀርተን በጠቅላይ ፍ/ቤት ወሳኔ አግኝተናል፡፡

ከ2002 ዓ.ም ተንከባለው ወደ 2001 የመጡ ጉዳዮች 33 ሲሆኑ በመደበኛ ክርክር ሂደት ላይ 122 ፋይሎች ሲገኙ ከነዚህ ውስጥ 44ቱ ብይን አግኝተዋል፡፡ እንዲሁም 131 አዲስ የተከፈቱ ፋይሎች አሉ፡፡ በነዚህም ላይ 647 የአቃቤ ህግ ምስክሮችና 236 የመከላከያ ምስክሮች ፍ/ቤት ቀርበው ቃላቸውን አስረድተዋል፡፡ ኮሚሽኑም ተጠርጣሪዎችን ጥፋተኛ የማስባል ደረጃ (conviction Rate) ወደ 89.6 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡

# የመሬት ግዥና ሽያጭ ያስከተለው ጉዳት

በበጀት አመቱ በአዲስ አበባ ከተማ መሬት አስተዳደር ጋር በተያያዝ ተንሰራፍቶ የቆየውን የሙስና ድርጊት ለመቆጣጠር በርካታ ተግባራት ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡ በዚህ መሠረት በ46 የምርመራ ውዝግቦች 624765 ካሬ ሜትር የከተማ ቦታ ታግዷል፡፡ ከዚህ ወስጥ 411,854 ካሬ ሜትር የከተማ ቦታ የዋጋ ግምቱ ብር 771,045,721 ሲሆን የቀሪው ቦታ የዋጋ ግምት እየተሰራለት መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ ከመሬት ጉዳይ ጋር በተያያዘም 38 ተጠርጣሪዎች ባንክ ያለ በድምሩ ብር 35,846,030.77 እንዲታገድ ሲደረግ ብዛት ያላቸው ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረትም ሊታገድባቸው ችሏል፡፡ አቶ ጌታቸው በገለጹልን መሰረት ጥቂት መኪኖችም በኮሚሽኑ ግቢ ውስጥ ቆመው ተመልክተናል፡፡

## ኮሚሽኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ መስራት የሚገባውን ሰርቷል ወይ?

አቶ ጌታቸው «ኮሚሽኑ ባለው ስልጣን፣ አቅምና የሰው ሀይል መስራት የሚገባውን እየሰራ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ሁሉንም ነገር አከናውነናል ማለት አይደለም፡፡ በቀጣይ ብዙ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ የሙስና ቅኝት (Survey) በሀገሪቷ ውስጥ ምን እንደሚመስል ከአለም ባንክ ጋር ኮስት ኢፊሴንቲቭ በሆነ መንገድ እየሰራን ነው» ብለዋል፡፡ በሀገራችን ትልልቅ ኢንቨስትመንቶች ላይ በመንገድ፣ በውሃ፣ በት/ቤትና ዩኒቨርስቲ ግንባታና ከፍተኛ የመንግስት በጀት በሚመደብላቸው ተቋማት ላይ የሙስና ዲያግኖስቲክ ጥናት እየተደረገ ነው ነገር ግን በነዚህ ተቋማት ላይ ያለው የሙስና ግምት ትልቅ ሲሆን እውነታው ግን ትንሽ ሆኖ መገኘቱ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንጻር አቶ ጌታቸው ኮሚሽኑ ከተቋቋመ 10 ዓመት እንኳን እንዳልሞላው በማስታወስ፡፡ የበጀት ችግር ባይኖርበትም ኮሚሽኑ የተመደበለትን በጀት በአግባቡ እየተጠቀምንበት እንዳልሆነና በሰው ሀይል ደረጃ በህግ ሙያ የሰለጠኑ ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች እጥረት እንዳለ አልሸሸጉም፡፡

## ለፀረ ሙስና ሌላ ፀረ ሙስና ያስፈልገዋል?

ይህ አይነቱ አገላለጽ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለያየ አጋጣሚ ይደመጣል፡፡ ከዚህ አንጻር ኮሚሽኑ ኃላፊነቱን በአግባቡ እየተወጣሁ ነው ብሎ ያምናል? ይህ ከአውራምባ ታይምስ ለአቶ ጌታቸው የሰነዘርነው ጥያቄ ነበር፡፡ አቶ ጌታቸው የሚከተለውን ብለዋል፡፡ «እንግዲህ ይህንን የሚናገሩ መነሻዎቻቸው የተለያዩ ሊሆን ይችላሉ፡፡ ጥቆማ ይቀርባል፡፡ ጥቆማው በአየር ላይ አይጠናም፡፡ ኮሚሽኑን የሚመለከት ጉዳይ ከሆነ በቀጥታ ሰነድና መረጃ አለ ወይ? ወይስ የለም? ድርጊቱ በትክክል ተፈጽሟል? ወይስ አልተፈፀመም? የሚሉትን ጥያቄዎች እንመልሳለን፡፡ በጥቆማው መሠረት መረጃና ሰነድ ሰብስበን ለማጣራት በምንቀሳቀስበት ወቅት በሙስናው የሚጠረጠረው ሰው ቀድሞ ሊነቃ ስለሚችል ምርመራው ሳይጠናቀቅ ከአካባቢው ሊሰወር፣ ሊጠፋና ከሀገር ሊወጣ ይችላል፡ በዚህ ጊዜ የኮሚሽኑ ሰራተኞች ለግለሰቡ ነግረውት እንዲሰወር ወይ እንዲጠፋ አድርገውታል ተብሎ ይወራል ወይም ይነገራል፡፡ ይሄ ትክክል አይደለም፡፡ አንዳንዴ የኮሚሽኑን ስራ በውል ካለመረዳትና ካለማወቅ የሚመጣ ችግር ነው፡፡» የሚሉት የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው አክለውም «አንድ የኮሚሽኑ የምርመራ ሰራተኛ በሙስና ክስ ላይ የነበረን የግል የጫማ ድርጅት ፋይል እንዲዘጋ ለማድረግ በፈፀሙት የሙስና ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው በፍ/ቤት ቅጣት

ተወስኖባቸዋል፡፡ ሌላው እንደዚህ አይነት ነገር አይኖርም ብሎ መናገር ባይቻልም እርግጠኝነቱንም ያለመረጃ መናገር ይከብዳል» ብለዋል፡፡

ከጊዜው ጋር አብረን መጓዝ አለብን፡፡ አለበለዚያ እንወድቃለን፡፡ ኮሚሽኑ ይህንን ተገንዝቦ ሰራተኞች በተለይም መርማሪዎች የተለያዩ ወቅቱን የጠበቁ ስልጠናዎችን ያገኛሉ፡፡ ከውጪ ሀገር የተለያዩ የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች ጋር የልምድ ልውውጥ የሚደረግ ሲሆን ሀላፊዎችም በተለያዩ አጋጣሚዎች የወጪ ስብሰባ ላይ በመካፈል የልምድ ልውውጥ ያደርጋሉ፡፡ ከብሔራዊ የመረጃ ደህንነት ጋርም ተባብረው በመስራት ሙያዊ ዕገዛ የምናገኝበትና ተባብረን የምንሰራበት መንገድ አለ፡፡ በተጨማሪም ከኢንተርኔት የተለያዩ ጠቃሚ መረጃዎችን እናገኛለን ሲሉ ተናግረዋል፡፡

## ሀገራችን በሙስና ያላት ደረጃ ምን ይመስላል?

የተለያዩ አለም አቀፍ ተቋማት ኢትዮጵያን ሙስና ከተንሰራፋባቸው አገሮች ተርታ ይመድቧታል፡፡ የኮሚሽኑ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ግን የሀገራችንን ደረጃ አስመልክተው በሰጡን ምላሽ «የኛ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ ሙስና ከተንሰራፋባቸው አገሮች ወደ መጨረሻው ላይ እንገኛለን፡፡ በየአመቱ የሚወጣ የኮራፕሽን ኢንዴክስ (Corruption index) አለ፡፡ በየአመቱም ለውጥ አለን፡፡ የሙስና ምዝና መስፈርቱም በተለያዩ መንገዶች ይገለፃል፡፡ ከሀገር ሀገርም እንደዚያው ይለያያል፡፡ በኬኒያ ከቦታ ቦታ ለመሄድና ለመንቀሳቀስ ሙስና አለ፡፡ በሀገራችን ግን ህብረተሰቡ ሙስናን እንደባህል አልወሰደውም፡፡ በፈረንጆቹ 2008/9 በሀገራችን በአለም አቀፍ ደረጃ 126ኛ ደረጃ ተሰጥቷታል፡፡ ይህንን አጥብቀን ተቃውመናል፡፡ ትክክለኛ የኢትዮጵያ የሙስና ገጽታ የሚገልጽ አይደለም፡፡ ይህንን ደረጃ የሰጡን ከበጀት ሪፖርት ጋር በተያያዘ የበጀት እጥረት ተገልጾ እንደ ትልቅ ነገር የመውሰድ index rate ላይ ችግር አምጥቷል፡፡ ይሔ አለም አቀፍ ትራንስፓይረንሲ በእንግሊዝ ሀገር የሚገኝ ሲሆን ቅሬታችንን ለእንግሊዝ ኤምባሲ አስታውቀናል፡፡ በተረፈ በአፍሪካ የፀረ ሙስና ኮሚሽንና በኢትዮጵያ ትራንስፓረንሲ ተቋም መለኪያ ሀገራችን በሙስና አነስተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡»

ብለዋል፡፡ የተቋሙ እንቅስቃሴና ስኬት በጥቆማ ላይ የተመሰረተ ብቻ መሆን የለበትም የሚለውን አስመልክተው የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው ሲመልሱ በጥቆማ ላይ ብቻ ተወስነን መቆም የለብንም፡፡ ጥቆማ ከሌለ ስራ መቆም አለበት? ጥቆማስ ከሌለ የሙስና ወንጀል በሀገራችን የለም ብሎ መደምደም ይቻላል? ስለዚህ በራሳችን ሰራተኞች መረጃዎችን ዳሰሳ (survey) ማድረግ አለብን፡፡ መረጃችንም ትክክል ከሆነ ክስ መመስረት አለብን ለዚህም በዝግጅት ላይ ነን፡፡» ብለውናል፡፡

# ሞቲቬሽን

# የፀጥታ ውጤት

# The Calming Effect

**በባንቺወሰን ወልደየሱስ**

*ሁሉም አንድ ቦታ ውስጥ ነው ያሉት ወይም ያጋጠማቸው ሁኔታ ለሁሉም አንድ ዓይነት ነው:: ያጋጠማቸውን ችግር ለመፍታት ሁሉም በመረባረብ ላይ ናቸው:: በድንገት ስለሆነ ይህ ችግር ያጋጠማቸው ሁሉም ግራ ተጋብተዋል፤ እናም ቶሎ ችግሩን የሚፈታ ሰው ሊገኝ አልቻልም:: እንደውም ግማሹ ለምን ችግሩ ራሱ አጋጠመን እያለ መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ እዛ ላይ እያተኮረ ነው:: እዛ ቦታ ውስጥ ያለው ሌላውም ቢሆን በራሱ መንገድ ችግሩን ለመጋፈጥ እየሞከረ ነው:: ግን የሁሉም ጥረት ላይ አንድ ዓይነት ነገር ይታያል:: ከሩቅ ለሚያይ ሰው ሰዎቹ ያጋጠማቸውን ችግር ለምፍታት የሚጣጣሩት በተመሳሳይ ዘዴና መንገድ ይመስላል:: በሁኔታው ውስጥ ያሉት ሰዎች ሁሉ በየስራ ድርሻቸው፣ በልምዳቸው፣ በባህሪያቸው እና በመሳሰሉት እጅግ የተለያዩ ቢሆኑም ድንገት ያጋጠማቸው ችግር እያዩበት የሚገኝ ዓይን ግን አንድ ዓይነት ነው:: ሁሉም ከየት መጣ ይሄ ችግር እያለ እዛ ችግር ላይ እያነጣጠረ ነው:: ችግሩ ማንኛውም ዓይነት ሊሆን ይችላል:: እየተጠበቀ ያለ ችግር ወይም ያልታሰበም ሊሆን ይችላል:: ራሱን ችግሩን ረስተን እስኪ እዛ ችግሩ የተፈጠረበት ሁኔታ ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች እናስተውላቸው:: ለምሳሌ አንድ ስብሰባ አዳራሽ ውስጥ አንድ ላይ የሚሰሩ ሰዎች ተሰባስበዋል:: የዛን ቀን የስብሰባ ዓላማ ወይም አጀንዳ አዲስ የታሰበ ፕሮጀክት ላይ ለመነጋገር እና ሃሳብ ለመለዋወጥ ነው:: ስብሰባውም የራሱ የተወሰነ ጊዜ ተይዞለታል:: ስብሰባውም ተጀመረ:: ግን ችግር አጋጠመ:: መጀመሪያ አካባቢ ይሁን ወይም መሀል አካባቢ ከስብሰባው ከተገኙት ውስጥ መች ችግሩ እንዳጋጠመ ሊነግር የሚችል ሰው አልተገኘም:: ስብሰባው እንደተጀመረ ሁሉም ያለውንና ያዘጋጀውን ማቅረብ ጀመረ:: አንዱ በእንደዚህ ምክንያቶች አዲሱ ፕሮጀክት ሊያስቸግረን ይችላል ሲል ሌላው ደግሞ አሁን እየሰራን ያለውን ስራችንን ሳንጨርስ እንዴት ሌላ አዲስ ስራ እንደመራለን አለ፣ ሁሉም የየራሱን የግል ሀሳብ ጠረጴዛው ዙሪያ ማቅረብ ጀመረ:: በዚህ መሀል ግን መሀከላቸው እየተፈጠረ ያለውን ነገር እያስተዋሉት አይመስልም:: ከሩቅ ለሚያያቸው እርስ በራሳቸው በንግግራቸው መግባባት ማቆማቸውን ከእነሱ መሀል ያስተዋለ የለም:: የስብሰባው ዋና ዓላማ አዲስ ላሰብነው ስራችን ምን ምን ዝግጅት ያስፈልገናል ሆኖ ሳለ በንግግራቸው እየተጣለ መሆኑን ከመሀከላቸው ያየ የለም:: አዲሱ ፕሮጀክታችን ምን ምን ችግር ያጋጥመዋል፣ እኛስ ምን ምን ብናደርግ የተሳካ ስራ እንሰራለን ሲሆን ዋና የመነጋገሪያ አጀንዳቸው አሁን ግን ከዓላማቸው ርቀዋል:: አሁን የተያዘው ዋና ዓላማ አንዱ የሚናገረውን አንዱ ማፍረስ ነው፣ አንዱ የሚሰጠውን አስተያየት ሌላው በምን መንገድ ይሄ አስተያየት አይሰራም ብሎ ማሰብ እና መናገር ላይ ነው:: በዚህ ሁሉ ምክንያት እዛ ቤት ውስጥ መናገር ብቻ እንጂ የሚያደምጥ ጠፋ::*

**የተረሳው ሰው**

ከመሀከላቸው አንድ ሰው ግን የስብሰባው ተካፋይ አይመስልም፡፡ እዛ ቤት ውስጥ ያለውን ሁኔታ ላየ ሰው ይሄ ሰው ያለቦታው አዳራሹ ውስጥ የተገኘ ይመስላል፡፡ ሰው ሁሉ እርስ በእርሱ ሲነጋገር እና ሲወቃቀስ እሱ ቃል አልወጣውም፡፡ የሚናገረው ነገር ስለሌለው አይደለም ወይም ለስብሰባው የሚያቀርበው አንዳች ሀሳብ ስላልያዘ አይደለም፡፡ እንደውም ለታሰበበት አዲስ ስራ ግሩም የሆኑ ሀሳቦችንና ለሚያጋጥሙም ችግሮች መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን ጭምር ይዞ ነው ወደ ስብሰባው የሄደው፡፡ ግን እስካሁን አንዱንም ሀሳቡን አልተናገረም፡፡ የመናገር እድል አጥቶም አይደለም፡፡ ሌሎቹ ሰዎች እርስ በራሳቸው ላይ ስራ ሲያበዙ እሱ ግን በሁኔታው ተገርሞ እነሱን እያያቸው ነው፡፡ እዛ ሁሉ ጩኸት ውስጥ እሱ ፀጥ ብሏል፡፡ አዎ እሱም የስብሰባው አካል ነው፣ እሱም ጉዳዩ በሚገባ ይመለከተዋል፣ እሱም የሚያካፍለው ሀሳብ አለው፣ ይሄ ሁሉ ሆኖ ሳለ ግን ክፍሉ ውስጥ የተፈጠረው አለመግባባት ውስጥ አልገባም ይሄ ሰው፡፡

የሚችለውን ያህል ከታገሰ በኋላ ግን እጁን አወጣ፡፡ እስከሚያዩትም ጠበቀ፡፡ እስካሁን መሀከላቸው የነበረ ቢሆንም አስተያየት ስላልሰጠ የሚናገረው ነገር የለም ብለው ትተውታል፡፡ አሁን እጁን ማውጣቱን ሲያዩ ግን ለሰከንዶችም ቢሆን ፀጥታ ሰፈነ፡፡ መናገርም ጀመረ፡፡ እየጠበቁ ያሉትን ነገር ግን አይደለም መናገር የጀመረው፡፡ መጨረሻ ላይ ለተናገረው ሰው ምላሽ ይሰጣል ብለው ሲጠብቁ እሱ የሚናገረው ግን ሌላ ነው፡፡ «ስብሰባችንን ከጀመርን ከአርባ ደቂቃ በላይ ሆኖናል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ግን ይሄ እስካሁን እያደመጥኩ ነው፡፡ነገር ግን እየተሰጠ ያለን ማንኛውም አስተያየት በክርክር መልክ ሌላው ሲቃወም ነው የሚታየው፡፡ አንድ ሰው እንደዚህ ማድረግ ጀመረ ሌላውም ተከተለ፡፡ አሁን ማቆሚያ የሌለበት ቦታ ላይ ደርሰናል፡፡ እናም ዋናው አጀንዳችንን ረስተነዋል፡፡ ይሄው አሁንም ድረስ አዲሱ ስራችንን እንደምንሰራ እና እንደማንሰራ አናውቅም፡፡ መደማመጥ ከማቆማችን የተነሳ ዋናውን ከስራችን ጋር የተያያዘን ችግር ረስተን እርስ በራሳችን የፈጠርነው አለመግባበት ችግር ላይ እያተኮርን ነው፡፡ ስለዚህ በተቀሩን ደቂቃዎች ውስጥ ስብሰባችንን በአዲስ መልክ ለምን አንጀምርም? »

አዎ በፀጥታ ነገሮችን ማስተዋል ብልሀትን ይጠይቃል፡፡ ጉብዝናንም እንዲሁ፡፡ ምክንያቱም የሚያጋጥም ሁኔታዎችን፣ ውስጡም ሆኖ ልክ ሩቅ ሆኖ እንደሚያይ ሰው ካየን ሁኔታውን በተለየ ማዕዘን ማየት ይችላልና፡፡

# ስፖርት

## ጉዳት ከአትሌቲክስ ያራቀው

## "The City Boy"

በሲድኒ ኦሎምፒክ የወርቅ፣ በኤድመንተን የዓለም ሻምፒዮና የብር ሜዳሊያ ካጠለቀ በኋላ ሚሊዮን ወልዴ ከአትሌቲክሱ መድረክ ስሙ ርቋል፡፡ «ለምን ጠፋህ?» ሲል አትሌቱን ፈልጎ ያገኘው የአውራምባ ታይምስ የስፖርት ዴስክ ኤዲተር አቤል ዓለማየሁ «የመጥፋቴ ምክንያት» ሲል የነገረውን በተከታዩ ጽሁፍ ላይ አስፍሮታል፡፡

በሲድኒ ኦሎምፒክ በ5 ሺህ ሜትር አሸንፎ ከገባ በኋላ ያሳየው ቡረቃ፣ ደስታና መፍለቅለቅ ለጋ እድሜ ላይ ያለ አዳጊ ታላቅ ታሪክ ሲፅፍ ሊያደርገው የሚችል ዓይነት ነው፡፡ ያ የልጅነት ወዝ አሁን ከፊቱ ላይ ተሟጦ አልቆ ጎልማሳ ለመባል እየተንደረደረ ነው፡፡ ችኮላና ፈጠን ፈጠን እያሉ መናገርን እርጋታ መንትፎ ወስዶበታል፡፡ ሲናገር ቁጥብነቱንና ጥንቃቄውን ያየ ሚሊዮን ወልዴ የጨመረው ዕድሜ ብቻ ሳይሆን ብስለትም መሆኑን ይረዳል፡፡ «ሲድኒ ላይ ዘጠኝ ዓመት መጨመሬን አትርሳ» ሲል ጊዜ ብዙ እንዳስተማረው ይናገራል፡፡

ልጅ እያለ እቴጌ መነን ት/ቤት አቅራቢያ ከሚገኘው መኖሪያ ሰፈሩ አጠገብ ከነበረ ሜዳ ላይ ከጓደኞቹ ጋር ቅሪላ መግፋት የዘወትር ተግባራቸው ነበር፡፡ ጥሩ አንከባላይም ነበር፡፡ ለልማት ስራዎች በሚል ሰበብ የስፖርት ሜዳዎችን እያደኑ የማጥፋት አባዜ የእነ ሚሊዮንን የቅሪላ ሱስ ማስታገሻ ሜዳንም ሰለባ አደረገውና አዳራሽ ይሰራበታል፡፡ ሁኔታው በእነ ሚሊዮን የኳስ ፍቅር ላይ ውሐ ቢቸልስበትም ስሜታቸውን ለማርካት ወደ ጉስቋም ማርያም ማቅናትና መጫወትን የግዴታ ምርጫቸው አደረጉት፡፡ ወደ ጉስቋም ጉዞ በሩጫ ሲሆን ደጋግሞ ቀድሞ በመገኘት ከሚሊዮን የተሻለ ማንም አልነበረም፡፡ በፍጥነቱ የሚገረሙት ጓደኞቹ የውይይት አጀንዳ ያደርጉታል፡፡ የስፖርት ሜዳውን ለሩጫ ለልምምድ የሚያቋርጡ አትሌቶችን ሲመለከቱም «ያስቸገረን ሰው አለ፤ አልቻልነውም፤ ከእናንተ ጋር ቀላቅሉልን» ሲሉ ያሳብቃሉ፡፡

አንድ ቀን መሀመድ ናስርና አስማረ ገበያው የተባሉ የሚሊዮን ሰፈር ልጆች የሆኑ ሯጮች ልምምድ ለመስራት እነ ሚሊዮን ኳስ በሚያንሸራሽሩበት ሜዳ ሲያቋርጡ የተለመደውን የሚሊዮን ጓደኞች በቀልድ የተዋዛ ንግግር ይሰማሉ፡፡ ተዋወቁትናም አብሯቸው ልምምድ እንዲሰራ ጋበዙት፡፡ አስማረ አትሌቶች ማለዳ ላይ ወደ ሚርመሰመሱበት መስቀል አደባባይ በማቅናት ለአንድ ሰዓት አብሮት ልምምድ እንዲሰራ አደረገው፡፡ በአስማረ ፍጥነት ሚሊዮን መንዝ ባይችልም ፍላጐትና ጥረቱ ያመረቃ ነበር፡፡ እምነታቸውን የጣሉበት ሁለቱ አትሌቶች ከሩጫ እንዳይቦዝን መላልሰው ቢመክሩትም ልምምድ ላይ «ፎርፌ» ያበዛ ነበር፡፡ በተከታታይ ቀናት አብሯቸው ይሰራና ድካም ሲሰማው ይቀራል፡፡ የሁለቱ አትሌቶች ጉትጐታ ገን አያቆምም፡፡ «ጥሩ እያመጣህ እንዴት ትቆማለህ (ትቀራለህ)» ሲሉ በሌሊት ቤቱ ድረስ መጥተው ያበረታቱታል፡፡ እነሱን ለማስደሰት አውልቆ የጣለውን ጫማ ፈላልጐ ዳግመኛ ለልምምድ ይወጣል፡፡ በሂደት ግን የልምምድ ዑደቱን እየተለማመደው መጣ፡፡ መሀመድና አስማረ ከጓደኞቻቸው ጋር ከሚሰባሰቡት ሻይ ቤት እየቀጠሩት የሚያወሩት «ሰሞነኛ» የሩጫ ወሬ ይበልጥ እንዲባንን አደረገው፡፡ አፉን ከፍቶ የሚሰማቸው «አሸነፈ/ች፣ ይህን ያህል

ብር አገኝ/ች፣ ምርጥ ሰዓት አስመዘገበ/ች፣ ማኒማ አመጣ/ች» ሙሉ ትኩረቱን ሩጫ ላይ እንዲያደርግና እስከ ት/ቤት ቡድን ከዘለቀው የእግር ኳስ ህይወቱ ጋር እንዲሰነባበት አደረገው::

## ያብባል አበበ ቢቂላ

በ1987 ዓ.ም የመጀመሪያ ላይ የመሀመድና አስማረ ክለብ ወደ ሆነው ያብባል ስፖርት ክለብ ተቀላቀለ:: መቻሬ ሜዳ ላይ ክለቡን ወክለው በኢትዮጵያ ሻምፒዮና የሚወክሉ አትሌቶች ሲመረጡ በ1500 ሜትር ተወዳድሮ 3ኛ ወጣ:: አዲስ አበባ ስታዲየም ላይ በሚደረገው የሀገሪቷ ሻምፒዮና ውድደር ላይ ግን መቋቋም ተሳነውና ከማጣሪያው ማለፍ ተሳነው:: ጓደኞቹ በቀጣይ የአገር አቋራጭ ውድድር ስላለ ተግቶ እንዲሰራ አሳሰቡት:: በወቅቱ የእቴጌ መነን የ12ኛ ክፍል ተማሪ ነበር:: ከልምምድ መልስ ስለሆነ ት/ቤት የሚገባው ክፍል ውስጥ እያለ እንቅልፍ በዐይኑ ይሞላል:: አትሌቲክስ ህይወቱ መሆኑ ፍንጭ ስለሰጠው ከትምህርት የቀደመ ትኩረትን ይለግሰው ነበር:: አዲስ አበባ ውስጥ በተዘጋጀው የአገር አቋራጭ ውድድር የተሻለ ውጤት አስመዝግቦ እንግሊዝ ዱርሀም ላይ ለሚካሄደው የወጣቶች ሻምፒዮና አባል ሆኖ ወደ ቦታው አቀና:: በ8 ኪ.ሜ. ተወዳድሮ 22ኛ ደረጃን ይዞ አጠናቀቀ:: አትሌት አሰፋ መዝገቡ የውድድሩ አሸናፊ ነበር:: ወደ ሀገር ቤት ሲመለሱ ባንክ ሁለቱን አትሌቶች ያለ ማጣሪያ የክለቡ አባል አደረጋቸው:: በዓመቱ በተደረገ አገር አቋራጭ ውድድር አሰፋ መዝገቡ አንደኛ፣ በቅርቡ ህይወቱ ያለፈው ሚዛን ተፈሪ ሁለተኛ፣ ሚሊዮን ወልዴ ሦስተኛ ወጡና (ሦስቱም ከኢትዮጵያ ባንኮች) ደ/አፍሪካ ላይ ለሚካሄደው የዓለም ወጣቶች አገር አቋራጭ ውድድር ላይ ተካፈሉ:: ሚሊዮን 8ኛ ወጣ:: ኢትዮጵያ በቡድን ሁለተኛ በመሆኗ ከታላቁ የቀድሞ የደ/አፍሪካ ፕሬዚዳንት ኔልሰን ማንዴላ እጅ ሜዳሊያ ተሸለሙ:: «ከታላቅ ሰው እጅ ሽልማት በመቀበላችን ደስታችን ወደር አልነበረውም» ይላል ሚሊዮን ደስታው ዛሬም እንዳለቀቀው በሚመስል አኳኋን::

## መሰናክል ሯጭ ሆነ

ከ1500 ወደ 3ሺህ ሜትር ተወዳዳሪነተ ከፍ አለ:: ባንክን ከመቀላቀሉ በፊት ልምምድ ያሰራው የነበረው ሻምበል እሸቱ ቱራ በኦሎምፒክ የነሐስ ሜዳሊያ ወዳጠለቀበት 3 ሺህ መሰናክል እንዲመጣ ገፋፋው:: ስታዲየም ውስጥ የቆሙት ከእንጨት የተሰሩ ግንዲላ መሰናክሎች እግሩን ካገኙ ለጉዳት ከመዳረግ ወደኋላ የማይሉ ናቸው:: ይህም ሚሊዮንን ቢያስፈራውም እሸቱን ስለሚፈራ ቴክኒኮችን በደንብ መለማመድ ተያያዘ:: ለተከታታይ ዓመት የአዲስ አበባ የ2ኛ ዲቪዚዮን ሻምፒዮን ሆነ:: ወደ ከፍተኛ ዲቪዚዮንም አምርቶ ስም ያላቸውን አትሌቶች በማስከተል አሸናፊ ሆነ:: አልጄሪያ ላይ ለውድድር ሄደና ሶስተኛ ወጣ:: የገባበት ሰዓት ለአትላንታ ኦሎምፒክ ሚኒማ ማሟላት ባያስችለው ለዓለም ወጣቶች ሻምፒዮና ተካፋይ እንዲሆን አደረገው::

እ.ኤ.አ በ1996 ሲድኒ ላይ በተካሄደው የዓለም ወጣቶች ሻምፒዮና በ3 ሺህ መሰናክል ተካፊይ ሆነ በማጣሪያ ሁለተኛ ወጣ:: በፍፃሜው ውድድር እርሱና ሁት

ኬኒያውያኖች ለአሸናፊነት አክሊሉን ለመድፋት ከፊት ይመራሉ፡፡ 200 ሜትረ ሲቀረው ኬኒያውያኖቹን አምልጦ ለመሄድ ሲሞክር መሰናክሉ መሰናክል ሆነበት፡፡ ወደቀና ጉዳት ደረሰበት፡፡ (እግሩ ተጋጋጠ) ከኋላ የነበሩ ሦስት አትሌቶችም ቀድመው እንደምንም 6ኛ ሆኖ ጨረሰ፡፡ የመሰናክል ሩጫ በቃኝ አለም፡፡ ማናጀር ጆስ ሄረማንስ ኃይሌ ገ/ስላሴ ደጋግሞ ሪከርድ በሰበረበት ሆላንድ፣ ሄንግሎ ከተማ ውስጥ «አንድ ሞክር» ይለዋል፡፡ ገባና አልቻለም፡፡ የተሻለ ሩጫ ቢሮጥም መሰናክለን የመዝለል ቴክኒክ ደካማ መሆኑን አመነና «እርም 3 ሺህ መሰናክል» አለ፡፡

## «5 ሺህ ይሻልሀል»

ዶ/ር ወ/መስቀል ኮስትሬ አግኝተወት «3 ሺህ መሰናክል ከብዶሀል፡፡ ወደ 5 ሺህ ብትመጣ ይሻልሃል» ሲሉ ይመክሩታል፡፡ እሱም ሆድ ብሶት ነበርና ጥሪውን በእሺታ ተቀበላቸው፡፡ ልምምዱንም ከእነ ኃይሌ ገ/ስላሴ ጋር አጧጧፈው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በ5 ሺህ ሜትር ቤልጂየም ላይ ውድድር አድርጐ 13:28 በመሮጥ አበረታች ውጤት አመጣ፡፡

በተከታታይ ባደረጋቸው የአገር አቋራጭና የ5 ሺህ ሜትር ውድድሮች ከቀዳሚ አትሌቶች ዝርዝር ውስጥ ስሙ ነበር፡፡

ኃይሌ የብቃቱ ጫፍ ላይ በደረሰበት በ1998 (እ.ኤ.አ) በኬኒያዊያኖቹ ዳንኤል ኩመንና ፖል ቴርጋት በ5 ሺህ እና በ10 ሺህ ሜትር የተነጠቀውን ሪከርድ ሄልሲንኪና ሄንግሎ ላይ በቀናት ልዩነት ሲያስመልስ ሚሊዮን በአሯሯጭነት ጉልህ ሚና ነበረው፡፡ ብቃቱን የተመለከተው ኃይሌም «ፊኒሺንግ ላይ ጠብቀህ ከሄድክ በአሸናፊ መንገድ ደጋግመህ የማትረማመድበት ምንም ምክንያት የለም» ሲል ዘወትር ይመክረው ነበር፡፡

## የሲድኒ ክስተት

ወደ ሲድኒ ኦሎምፒክ ከመጓዙ በፊት ጥሩ ብቃት ላይ ይገኝ ነበር፡፡ በሲድኒ በ5 ሺህ ሜትር ወርቅ ያጠልቃል ተብሎ ትልቅ ግምት ላይ የነበረውን አልጄሪያዊው ሳይድ ሳይፍን ስቱትጋርት ላይ ሚሊዮን ቀድሞት ገብቷል፡፡ ፓሪስ ላይ ዳግመኛ በ3 ሺህ ሜትር ተገናኙ ሳይድ ብድሩን መለሰና አሸነፈ፡፡ ሚሊዮን 3ኛ በመውጣት በ3 ሺህ ሜትር የእስከዛሬ ምርጥ ሰዓቱን 7:32 አስመዘገበ፡፡ በሳምንቱ ለ3ኛ ጊዜ ሮም ላይ በ5 ሺህ ሜትር ሁለቱ አፍሪቃዊያን ተገናኙ፡፡ ሳይድ በድጋሚ አሸነፈው ሚሊዮን 5ኛ ቢወጣም ለኦሎምፒክ ሚኒማ በውድድሩ ላይ አሟላ፡፡ በአልጀሪያዊው በተከታታይ መረታቱ ቢያስቆጣውም ትምህርት አገኘበት፡፡ «የቱጋ እንደምነሳና ፍጥነቴን እንደምጨምር መዝግቤ ያዝኩ» የሚለው ሚሊዮን ከሳይድ ጋር ሲድኒ ላይ ለመገናኘት ቀጠሮ ተለዋወጠ፡፡

በኦሎምፒክ መንደሩ አየር ለመቀበል ሲንቀሳቀሱ ከአልጀሪያውያን ከፍተኛ የቡድን አመራር አባላትና አሰልጣኞች ጋር ይገናኛሉ፡፡ ከሚሊዮን አጠገብ የነበረውን አትሌት ኃይሌ ገ/ሥላሴን ጠሩትና «10 ሺህ የእናንተ ነው፤ 5 ሺህ ግን አትጠራጠር የእኛ ነው» ሲሉ ሚሊዮን ጆሮ ገባ፡፡ ቁጭት አደረበት፡፡ ሳይድ ሳይፍ ጋር ከውድድር

በፊት ተገናኝተው ሁለቱም በጥሩ ብቃት ላይ መሆናቸውን በመግለፅ ማስጠንቀቂያ አዘል ሀሳብ ተለዋወጡ፡፡

ሳይድ «ወገቤን» (ሰበብ) ማለት ጀምሯል፡፡ እግሬን፣ ተፋዬን፣ ጡንቻዬን እያለ የህክምና ርዳታ ደጋግሞ በልምምድ ወቅት ይማፀናል፡፡ ይህንን የተመለከቱ የአቢሲኒያ አትሌቶች ለሚሊዮን ሹክ ይሉታል፡፡ ማጣሪያ ላይ በተለያየ ጉራ ተመደቡ፡፡ ሚሊዮን የሳይድን ስሜት ሲቃኝ ጓደኞቹ የነገሩት ተደምሮበት «በአትሌቲክስኛ» ጥሩ መንፈስ ላይ እንዳልሆነ ተረዳ፡፡ ሜዳሊያ ውስጥ እንደሚገባ ለራሱ ነገረው፡፡ ወርቅ አመጣለሁ ብሎ ግን አላሰበም፡፡ በፍፃሜው ቀን የሩጫ ውድድሩ ተመችቶታል፡፡ በ180 ሜትር ሲቀር ሳይድን ጥሎት ሄደ፡፡ በብዙ ኢትዮጵያዊያን ስፖርት አፍቃሪያን ዘንድ ከድሉ በፊት ማን እንደሆነ እንኳን የማይታወቀው ቅልጥማሙ ልጅ በድል ብስራት ትውውቅ ፈጠረ፡፡ ብዙዎች ሊያሳኩት የሚቸገሩበትን የኦሎምፒክ አሸናፊነት በመጀመሪያ ተሳትፎው አገኘ፡፡ ደስታው ወደር አጣ እየተሽከረከረ ሁለት እጆቹን አፉ ላይ ወርወር መለስ እየደረገ ስታዲየም ውስጥ የታደሙትንና በቲቪ ስክሪን የሚመለከቱትን ሁሉ የ«እወዳችኋለሁ» ምልክት አሳየ፡፡ ድሉንም ስታነሱበት ቢደግመው እየተመኘ «ሆህ... ምርጥ ጊዜ ነው» ሊል ምላሽ ይሰጥበታል፡፡

በዓመቱ በኤድመንተን በተደረገ የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና የተወትር ተፎካካሪውን ሳይድ ሳይፍን ተከትሎ ሦስተኛ ይወጣል፡፡ በዶፒንግ ምርመራ ተቀናቃኙ አልጄሪያዊ «ፖዘቲቭ» ሆኖ በመገኘቱ የብር ሜዳሊያውን ለሚሊዮን እንዲያስረክብ ተደረጓል፡፡ ከኤድመንተን በኋላ ግን ሚሊዮን ጠፋ፡፡ ለምን?

## «ጉዳት ከረመብኝ»

ለኤድመንተን የዓለም ሻምፒዮና ዝግጅት ላይ እያለ በሁለት እግሩ ላይ ጉዳት ደረሰበት፡፡ ጉዳቱንም ተቋቁሞ ኤድመንተን ላይ ሜዳሊያ ይዞ ቢመጣም «ከዚያ በኋላ ለመጥፋቴ ምክንያቱ ጉዳት ነው» የሚለው ሚሊዮን «እስከ 2003 ድረስ ከጉዳት ጋር ሆኜ መለስ ቀለስ እያልኩ ውድድሮችን ባደርግም ከዚያ በኋላ ግን አልቻልኩም፤ በይበልጥ አገረሸብኝ» ይላል፡፡

ሂልሲንኪ ላይ ኃይሌንና ገዛኸኝ አበራን ኦፕራሲዮን ያደረጉት ዶክተሮች አዲስ አበባ መጥተው በጉዳቱ በመገረም መለስተኛ ጥናት አደረጉበት፡፡ «እግርህ መርገጫ ፊት አካባቢ ደም አላዘዋውር ያለ ነገር ስላለ ኦፕራሲዮን እናደርግህና መሮጥ ባትችል እንኳን መራመድ አይከብድህም» አሉት፡፡ «እሺ» ብሎ ሐኪም ቤት ቀጠሮ ካስያዘ በኋላ አልጣመውም፡፡ «ይለፈኝ» አለ፡፡ ሆላንድ፣ አሜሪካና ሳውዲ ዓረቢያ በህክምና አሳልፏል፡፡ በጤናው ላይ ትንሽ ለውጥ ያየው በ2007 ዓ.ም. ከሳውዲ ዓረቢያው ህክምና በኋላ ነው፡፡ «የህመምህ ምክንያት ከጀርባህ ላይ ተነስቶ ወደ እግርህ የሚወርድ ጅማት በመደራረቡ ሳቢያ ነው» በማለት ባደረጉለት የቀዶ ጥገና ህክምና ወደ መም (ትራክ) ተመልሶ ታሪኩን ማደስ ባያስችለውም እንኳን በጤንነቱ ላይ መሻሻል እንዲመጣ አድርጎታል፡፡

ማናጀሩ ጆስ ሄርመንስ፣ አወዳዳሪ አካላትና ኮሜንታተሮች የከተማ ልጅ ሆኖ በኦሎምፒክ እስከ ማሸነፍ መድረሱን በመመልከት «City Boy» እያሉ የሚጠሩት ሚሊዮን ወልዴ በ2004 የአቴንስ ኦሎምፒክ ሲካሄድ አሜሪካ ውስጥ ሆኖ ህክምናውን ሲከታተል ሁለት ተቃራኒ ስሜቶችን እያስተናገደ ነበር:: ሲድኒን እያሰበ ሀሴት ሲያደርግ አቴንሰ ላይ ባመገኘቱ ውስጡ ጽልመት ወርሶት ነበር:: በወቅቱ ከልምምድ ርቆ ስለነበር 20 ኪሎ ግራም በጨምሮ 79 ኪሎ ግራም መዝኖ ነበር::

## የሚሊዮን «አሁን»

ሚሊዮንን «አሁንስ ጤንነትህ እንዴት ነው?» ብትሉት ከአፉ «ሙሉ ጤነኛ ነኝ» የሚል መልስ አታገኙም:: የከረመበት ጉዳት ከ «City Boy» ፍቅሩን አሁንም አልጨረሰም:: «ሳውዲ ዓረቢያ ላይ ህክምና ካደረኩ በኋላ ጤንነቴ መለስ ቢልም ልምምድ ስሰራ (በተለይ ጠንካራ ልምምድ) የህመሙ ሰሜት ያገረሽብኛል::» የሚለው ሚሊዮን የመም ጫማ (Truck Spike) አድርጐ ልምምድ ከጀመረ ከፍተኛ ህመም ስለሚሰማው ዳግም ወደ መም ሩጫ መመለሱን ይጠራጠራል::

የቀድሞ አቋሙን ለመመለስ እንደሚከብደው ቢያውቅም መታተሩን ግን አላቆመም:: ከልምምድ አልታቀበም:: ውድድርም እየሞከረ ነው:: ባለፈው ዓመት የ5 ኪሎ ሜትር የጐዳና ላይ ሩጫ በኖርዌይ አድርጐ ሁለተኛ ሲወጣ ዘንድሮ ደግሞ በዚሁ ውድድር ሦስተኛ ሆኗል:: በዱባይ ግማሽ ማራቶን ተወዳድሮ ሮጦ ውድድሩን ለማጠናቀቅ 1ሰዓት ከ11 ደቂቃ ፈጅቶበታል:: የገባበት ሰዓት ባያመረቃም ከጉዳት መምጣቱን፣ ከህመም ስሜት ጋር ታግሎ 21 ኪሎ ሜትሩን ማጠናቀቁን፣ ለውድድሩ አዲስ መሆኑን ከግምት ከትቶ «ውጤቱ አስከፊ አይደለም» ይላል::

## አለህ እንዴ?

በቀጣይ ጊዜት ታሪክ ራሱን ደግሞ ሚሊዮን ታላቅነቱን ዳግመኛ ማስመስከር ስለመቻሉ ስጠይቀው ጥርጣሬ በአነገተ ስሜት «የእኔም ዋና ፍላጐት እሱ ነው:: ስለ ሁሉም የሚያውቀው እግዜአብሔር ነው» ሲል መልሶልኛል:: ይህን ማሳካት ባይቻለው እንኳን የአትሌቲክስ አሰልጣኝነት ስልጠና ወስዶ አሰልጣኝነት በመሆን ራሱን ከስፖርት ክበብ አለማውጣትን ያስባል:: በአሁን ሰዓት «ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ» የቦርድ አባል ሆኖ ድጋፍ ይሰጣል:: ኖርዌይ ውስጥ ካለ «ክራኒክሚላ» ከሚሰኝ ዓመታዊ ውድድር አዘጋጆች ጋር በጥምረት የሚሰሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት በጋር እየተነጋገሩ ነው:: ታላቁ ሩጫ ህፃናቶችን ለመርዳት ለሚየደርገው የገንዘብ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም 10 ሺህ ዶላር በኖርዌይ አሰባስበዋል::

ከሲድኒ ኦሎምፒክ በኋላ ወደ ትዳር ገብቶ አራት ልጆች ያፈራው አትሌት ሚሊዮን ወልዴን ብዙዎች በመንገድ ሲያገኙት የሚያቀርቡለት ተመሳሳይ ጥያቄ አለ:: «ምነው ጠፋህ?» የሚል:: «በቅርብ የሚያውቁኝ ለምን እንደጠፋሁ ያውቃሉ» የሚለው አትሌቱ «ጉዳት ሲደጋገምብህና ረጅም እረፍት ስትወስድ አቋምህ ይወርዳል» ሲል ያጠቁትን ጥቁር አጋጣሚዎች ይደረድራል::

ሩጫን ርግፍ አድርጐ አቁሞ ሙያ የቀየረ የሚመስላቸውም ያጋጥሙታል፡፡ «ለምን ሩጫ አቆምክ?» ለሚሉት ሳይታክት ሩጫ አለማቆሙንና ጉዳት ከመም እንደራቀው ያስረዳል፡፡ «ሲድኒ ላይ እድል ከእሱ ገጥሞ ወርቅ አጠለቀ እንጂ ወጥ ብቃት ያለው ልጅ አልነበረም ማለት ነው?» መሰል ጥያቄና አስተያየቶችን ቢሰማም አይስማማባቸውም፡፡ «ከሲድኒ በፊት በተለይ በወጣቶች ሻምፒዮናዎች ላይ የነበረኝ ውጤት ጥሩ ነው፡፡ ከሲድኒ በኋላም በኤድመንተን የዓለም ሻምፒዮና የብር ሜዳሊያ አምጥቻለሁ (በ5 ሺህ ሜትር መሆኑን ልብ ይሏል) ይህም ከአስተያየቱ ጋር ይጣረሳል» ይላል አክሎም «ኃይሌ እኔን ይተካል ብሎ መግለጫ ሰጥቶ እንደነበር መረሳት የለበትም» ሲል የጀግናው አትሌት አስተያየት ስለነበረው ብቃት ዋቢ ምስክር መሆኑን አስቀምጧል፡፡ «ያጠፋኝ የጉዳት መዳራረብ ነው፡፡ ውጤት አስመዝግቤ በቴሌቪዥን ስክሪን ላይ አልምጣ እንጂ የምችለውን ያህል መንቀሳቀሴ አይቀርም፡፡ ከሩጫ ውስጥ ህይወቴን በሙሉ ልወጣ አልፈልግም፡፡» የሚለው «City Boy»ን በቀጣይ አትሌት ወይስ አሰልጣኝ «ሚሊዮን» እያልን እንጠራው ይሆን?